# ወጣትነት

ዓብዱራህማን ሰዒድ (ሜጢ)

## ማውጫ


መግቢያ ....................................................................................4

1 ....................................................................................7

ሳይመሽ በጊዜ ....................................................................................7

ኢስላም እና ማፍራት የሚሻው ትውልድ ....................................................................................15

በወጣትነት እና እርጅና መሀል ....................................................................................16

**2** ....................................................................................20

**ለምጡቅ ማህበረሰብ ግንባታ** ....................................................................................20

***በመንፈሳዊው ዘርፍ*** ....................................................................................21

በማህበራዊ ዘርፍ ....................................................................................43

***በትምህርት ዘርፍ*** ....................................................................................47

***በኢኮኖሚው ዘርፍ*** ....................................................................................48

3 ....................................................................................51

**በትግል ሜዳ ውስጥ** ....................................................................................51

ወጣቶች ነበሩ ....................................................................................54

ረኸሙ እንቅልፍ ....................................................................................60

4 ....................................................................................73

አዎንታዊ የኋሊት ጉዞ ....................................................................................73

መሰረታዊ እሴቶች ....................................................................................85

5 ........................................................................................................ 91

ላለመድረስ........................................................................................................ 91

6 ........................................................................................................ 95

አዳኞቹ ........................................................................................................ 95

# መግቢያ

ወጣትነት በሁለት ድክመቶች መሐል የሚገኝ ብርታት ነው። ስለሆነም ለብዙ ፈተናዎች የተጋለጠ እርከን ነው። በማንኛውም ህብረተሰብ ወጣቱ የአፍላ ጉልበት፣የብሩህ አእምሮና ዕምቅ ኃይል ባለቤት ነው። ወጣቶች በሁለት ዓለም ውስጥ መኖር የሚያስችል አቅምና ዕድሜ አላቸው። ከዚህ አንፃር ታዲያ ድርብና ውስብስብ ትውልዳዊ ኃላፊነት አለባቸው። አብረውት እየኖሩት ያለው ማህበረሰብ የሚፈልግባቸው አስተዋፅዖ አለ። የነገውን ትውልድም የተሻለ ሆኖ ማግኘት የሚቻላቸው በራሳቸው ብርቱ ስራና እሳቤ ነው። ለዚህም ታዲያ ራሳቸውን ማዘጋጀት ያለባቸው ዛሬ ነው። ወጣቱ ለውጥን ለመቀበልና ለመፍጠር ዝግጁ የሆነ አዕምሮ ባለቤት ነው። ኢስላም ኣቻ የለሽ የህይወት ስርዓተ-መርህ አለው። ስርዓተ-መርህ የሚገነባው በሰዎች ረዥም የህይወት ጉዞ ላይ ነው። ኢስላም ደግሞ አስተማማኝና ሊሰበር የማይችል ምድራዊ ህይወትን ከወዲያኛው ዓለም የሚያገናኝ መንፈሳዊ ድልድይ ነው። ከሰዎችም ውስጥ ስርኣቱን መኖር የጀመረውና ሰንደቁን በልቦናው ካስማ ላይ የተከለው ልዩ ተልእኮ አለበት።

ዶክተር ኢሳም በሺር በአንድ መልእክታቸው ሙስሊም ወጣቶችን አስመልክተው እንዲህ ብለው ነበር፡- «አላህ መልካም ፍቃዱ ከሆነ አንተ የኡማህ ተስፋ ነህ። ታውቃለህ! በአንተና መሰሎችህ ውስጥ ብዙ እምቅ መልካም ነገር አለ። ሁሌም ቢሆን ነፃና ክብር ያለው ሰው ሊኖር የማይወደውን የውርደት፣የመሸማቀቅ፣አስለቃሽና መራራ የኡማችንን ነባራዊ ሁኔታ እንይ። ካለንበት የወንጀል ተግባር ወደ አላህ በተውበት አለመመለሳችን፣ ለእውነት ጠበቃና ዘብ ሆነን አለመቆማችን፣ወደ መልካም ለመጥራትና በጥሩ ለማዘዝ እንዲሁም ለኢስላማዊ ተሃድሶ ያለንን አቅም አለመጠቀማችን ለህዝባችን ከአላህ ለሚመጣው ግዙፍ እርዳታ(ነስር) መዘግየት ሰበብ ሆነናል። ምክንያቱም አላህ(ሱወ) የበላይነትን ሊያጎናፅፈንና እርዳታውን ሊቸረን ቃል የገባው ትዕዛዛቱን ከፈፀምንና ድንጋጌዎቹን አጥብቀን ከያዝን ብቻ እንደሆነ ነው።

*«እናንተ ያመናችሁ ሆይ ! አላህን (ሃይማኖቱን) ብትረዱ ይረዳችኋል፤ ጫማዎቻችሁንም ያደላድላል፡፡»*

*ሙሐመድ፣ 7*

አንተ የኢስላም ወጣት ሆይ ! የቅርቢቱ ዓለምም ይሁን የወዲያኛው ዓለም ደስታ ያለው የፅናትን ጎዳና በመጓዝ፣ወደ አላህ መንገድ በመጣራት፣ በኡማው ውስጥ የመልካምነትና የብርሃን ምንጭ ከሆኑ ትጉህ ተጣሪዎችና ታማኝ ልሂቃን እንዲሁም እውነተኛ ወንድሞች ጋር ባለ ጥብቅ የሆነና ከዓለም ባሻገር ያለ ግንኙነት ውስጥ ነው፡፡

አንተ ወጣት ሆይ ! በኡማህና ሀገርህ ላይ ተፅዕኖ አሳዳሪ ስብዕና ያለው መሆንህ ቅሮት የሌለው ሓላፊነትህ ነው፡፡ አሳማሚ የሆነውን ነባራዊ ሁኔታ አላህ መልዕክተኛውና አማኞች ወደሚወዱት ሁኔታ ለመቀየር አዎንታዊ የሆነ ድርሻ ሊኖርህ ግድ ይላል፡፡ *«ወጣቶች ሆይ ! ስራ በወጣትነት እድሜ ክልል ላይ ነው፡፡»* ያለው ሰው እውነትን በእርግጥ ተናገረ፡፡

የኡማው ወጣት ሆይ ! ዛሬ ላይ ነፍስህን፣ስሜትህንና ከጃሎትህን ካልታገልክ መቼን እየጠበቅክ ነው? ስለ እምነትህና አካባቢህ እንዲሁም ስለ ኡማህ መጪ ጊዜ ስትል ዛሬን የዕድሜህን ፅጌሬዳ ክፍል መስዋዕት ካላደረክ መች ልታደርገው ነው?

ወጣቱ ሆይ ! በል አሁን አንድ ላይ ሆነን አዲስ ንጋትን እንፍጠር፡፡ ኡማችን ያጣውን ክብር ዳግም እንመልስ፡፡»

እነሆ የወጣትነትን ዕድሜ ተሰናብተው ወደ ቀጣዩ የህይወታቸው እርከን የተሻገሩትን ታላላቆቻችንን ስላለፈው እንጠይቃቸው፡፡ ስላሉበት ሽምግልና መልሳቸው ሊሆን የሚችለው

***ቢመጣ ምናለ አንዴ ወጣትነት***

***ስለ ሽምግልና ሁሉን በነገርኩት***

ነው፡፡

ቁጭትና ህሊናን በፀፀት መጉዳት ምድራዊ ቅጣት ነው፡፡ ስለሆነም የዛሬው ሙስሊም ወጣት ላይ ግዴታዎች ብዙ ናቸው፡፡ አደራን በትከሻው ጭኗል፡፡ ሩቅ ማሰብ፣ብዙ መስራት መዳረሻን ማስመርና ለተፈፃሚነቱም ቆርጦ መነሳት ከግዴታዎቻችን ነው፡፡

ውድ አንባቢ አስተያየትዎን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ፡፡ ይህን ፅሁፍ ሳዘጋጅ በብዙ መልኩ የተባበሩኝን  ኡስታዞችና ወንድሞች  በሙሉ አመሰግንኩ፡፡

# 1

# ሳይመሽ በጊዜ

የወጣትነት ዕድሜ ክልል አካላዊ ጥንካሬ እና ትኩስነት የሚስተዋልበት እርከን ነው፡፡ ወጣት የሚያምር መስህብ ያለው አበባ ነው፡፡ ለማህበረሰብ ሁለንተናዊ ጌጥ እና ውበት ብሎም የጥንካሬው ሚስጥር ነው፡፡ በማንኛውም ህብረተሰብ ወጣቱ የአፍላ ጉልበት፣የብሩህ አዕምሮና ዕምቅ ኃይል ባለቤት ነው፡፡ ስለሆነም ለወጣቱ ትኩረት የማይሰጥ ስርዓት የወደፊት ህልውናው ለአደጋ የተጋለጠ ነው፡፡ ማንኛውም አስተሳሰብ ብቅ ሲል ተልዕኮውንና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የወጣትን ዕርዳታ ይሻል፡፡ ለዚህም ሲባል አስተሳሰቡ እንዲራመድ ወጣቶችን ያስጠጋል፡፡ ከሰንደቁ ስር ያስጠልላቸዋል፡ ፡

ኢስላም የህይወት መንገድ ነው፡፡ ለአማኝ ሰዎች ምቹ እና የመንፈስ መርጊያ አፀድም ጭምር ነው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንን ዲን ለማስተማር እና ለማስፋፋት ከአላህ ዕርዳታ በተጨማሪ የወጣቱ ሚና የጎላ እንደነበር ክቡር ሀዲሳቸው ይነግረናል፡፡

*‹‹አባቶች አዋረዱኝ (አስተባበሉኝ) ወጣቶች ረዱኝ፡፡››*

አዎ! በዚያ የስቃይ እና እንግልት የመካ ዘመን ከዙሪያቸው ሆነው የረዷቸው አብዛኞቹ አዛውንቶች ሳይሆኑ ለጋ ወጣቶች ነበሩ፡፡ የጃሂልያን ጥቁር ጨለማ ሸሽተውት ወደ ብርሀናዊው ጎዳና ኢስላም ጉያ ስር በነብያዊው የእዝነት ክንፍ ተጠለሉ፡፡

እምነት ወንጀል ተደርጎ ተቆጠረ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከትውልድ ቀያቸው ተሰደዱ፡፡ እነኚህ ረዳት ወጣቶች አብረው ነጎዱ፡፡ ብሩህ ህሊናቸውን

ለራዕያዊው አንደበት ሙሉ ለሙሉ አስገዙ፡፡ መያዝ የሚገባውን አምላካዊ ምሪት ጨበጡ፡፡ በጊዜ ሂደት ለሌሎችም መሪ ለመሆን በቁ፡፡ ወደተለያዩ የዓለም ክፍሎች በመጓዝ ኢስላምን አስተማሩ፡፡ የእምነትን የበላይነት በሁሉም የሰው ዘር ዘንድ አስመሰከሩ፡፡ በእርግጥ ከዚያ በፊት የዚህን ኡማ ምርጥነት ቁርአን መስክሯል፡፡ የምስክርነቱ ተግባራዊ እማኞች ለመሆን በቁ፡፡

كُنتُمْ خَيْرَ أُمَّةٍ أُخْرِجَتْ لِلنَّاسِ تَأْمُرُونَ بِالْمَعْرُوفِ وَتَنْهَوْنَ عَنِ الْمُنكَرِ وَتُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ وَلَوْ آمَنَ أَهْلُ الْكِتَابِ لَكَانَ خَيْرًا لَّهُم مِّنْهُمُ الْمُؤْمِنُونَ وَأَكْثَرُهُمُ الْفَاسِقُونَ آل عمران: ١١٠

*«ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ኾናችሁ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ፤ ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ፤ በአላህም (አንድነት) ታምናላችሁ፡፡ የመጽሐፉም ሰዎች ባመኑ ኖሮ ለነርሱ የተሻለ በኾነ ነበር፡፡ ከነርሱ አማኞች አሉ፡፡ አብዛኞቻቸው ግን አመጸኞች ናቸው፡፡>>*[1]

ሁለንተናዊ ባህሪና ይዘት ያለው ኢስላም በወጣቶች ትከሻ ላይ በመሆን የምድርን ገላ ከእድፍ አፀዳው።

## ሙዓዝ ኢብኑ ጀበል(ረ.ዐ)

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ትልቅ ሶሀባ ነው፡፡ መልዕክተኛው እጅግ ይወዱታል፡፡ እርሱም ለርሳቸው ከህይወቱ ይበልጥ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡ ዑመር(ረ.ዐ) በአንድ ወቅት «ሙዓዝ ሆይ! በአላህ እምላለሁ እኔ እጅግ ወድሀለሁ» ብለውታል፡፡ ይህ እንቁ ሶሀባ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ሀገረ-የመን ተልዕኮ ተሰጠው፡፡

[1]አል-ዒምራን 110

እነሆ እርሱም ለተልዕኮው ራሱን አዘጋጀ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) «ሙዓዝ ሆይ! አሁን አንተ ከመጽሐፉ ባለቤቶች የሆኑ ህዝቦች ዘንድ ነው የምትሄደው ከአላህ በስተቀር የሚገዙት አካል እንደሌለ፤ሙሀመድም (ሰ.ዐ.ወ) መልዕክተኛው እንደሆኑ አስተምራቸው...» በማለት አደራ አስይዘው ላኩት፡፡ ነገር ግን አሉት ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) «ምናልባት እስከሚቀጥለው ዓመት ላልቆይ እችላለሁ፡፡ ስትመለስ ቀብሬን ብቻ ሊሆን ይችላል የምታገኘው፡፡» አሉት፡፡ ሙዓዝ አምርሮ አለቀሰ፡፡ የወዳጁን መርዶ በህይወት እያሉ ራሳቸው ነገሩት፡፡ እርሙን አወጣ፡፡ የወዳጁን የፍኖት አመላካቹን ሕልፈተ-ሕይወት ቀድሞ እንዲረዳ የተፈለገበት ምክንያት ሊኖር ይችላል ምናልባም ጽኑ መንፈስ ያለው ብርቱ መሆኑ በነብዩ ታምኖ ይሆናል፡፡ ዋናው ነገር የርሳቸው ተልዕኮ መሳካቱ ነበር፡፡ እነሆ ከዚህ መራር ሀዘን ጋር ሙዓዝ ተልዕኮውን ለማድረስ ተንቀሳቀሰ፡፡ ወጣትነቱን በአግባቡና ለታላቅ ዓላማ ተጠቅሞ እስልምና እስከምድር ፍጻሜ ስሙን ሲዘክርለት ይኖራል፡፡

## ሙስዓብ ኢብኑ ዑመይር(ረ.ዐ)

ከተንደላቀቀ ቤተሰብ የተገኘ የቅምጥል ሕይወት ኗሪ ነበር፡፡ ኢስላም ሲመጣ የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ጎራ ተቀላቀለ፡፡ መልከ-መልካሙን ሙስዓቡል-ኸይር የማትመኝ አንዲትም መካዊት ኮረዳ አልነበረችም፡፡ ነገር ግን አላህ የዘመናትን የጉዞ ታሪክ ለመቀየር ለኢስላማዊው ጎዳና ተፋላሚነት አጨው፡፡ ሙስዓብ ኢስላምን ከተቀላቀለ በኋላ ኑሮ አልጋ ባልጋ፤ የሕይወት ጎዳና ገር በገር አልሆነለትም፡፡ ሲያቀማጥሉት የነበሩት ቁሳዊ ነገሮች በሙሉ በቤተሰቡ ቁጣ ምክንያት ተወገዱበት፡፡ የሚበላው እና የሚለብሰው አጥቶ የተቀደዱ ልብሶችን በእሾህ አያይዞ እስከ መልበስ ያደረሰ ችግር ቀመሰ፡፡ ነገር ግን ይህ ስጋዊ እና ቁሳዊ ኪሳራ የፈጠረው አሉታዊ ተፅዕኖ አልነበረም፡፡ ነፍሱ እና መንፈሱ ከጊዜ ወደ ጊዜ በነብያዊው ፍቅር በአምላካዊው ራዕይ ወደ ከፍታ ይመጥቃሉ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሙስዓብን ባዩት ቁጥር ያለቅሱ ነበር፡፡ ነብዩ (ሰዐወ) ያለቀሱለት ወጣት እንዴት ያስቀናል !

ያንን የነበረበትን የድሎት ኑሮ አሁን ከደረሰበት እንግልት ጋር ሲያነፃፅሩት ዓይናቸው በእምባ ይሞላል፡፡ አዎ! ሙስዓብ ከመራቡ እና መቸገሩ የተነሳ የሰውነቱ ቆዳ እንደ እባብ ቆዳ ይገለፈፍ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ስቃይ ለእምነቱ ከመስራት የነብዩን ትዕዛዝ ከመተግበር አላገደውም፡፡ በኢስላም ታሪክ ውስጥ ወደ መዲና የተሾመ የመጀመሪያው አምባሳደር ነበር፡፡ ለጋና አስተዋይ ወጣት...

ኢስላምን ከሂጅራ በፊት ለመዲናውያን አስተማረ፡፡ መዲናንም ለመልእክተኛውና ስደተኞች ምቹ አቀባበል ይኖራት ዘንድ የተቻለውን ያህል ጥረት አደረገ፡፡ በስተመጨረሻም በኡሁድ የጦር ውሎ የኢስላምን ባንዲራ ከፍ አድርጎ የአጋሪያንን ትኩረት ከነብዩ(ሰዐወ) ለመውሰድ ከፍ ባለ ድምፅ ተክቢራ እያለ ሁለት እጆቹ ተቆርጠውና በአንካሴ ተወግቶ ወደቀ፡፡ ይህ ለጋ ወጣት በአላህ መንገድ ላይ እንደቆመ ነው በአፍላ እድሜው የተቀጨው፡፡

## *ሰዕድ ኢብኑ አቢወቃስ (ረ.ዐ)*

ጠንቃቃና ብልህ ወጣት ነበር፡፡ ጀግንነት ባህሪው ሲሆን ቀስተኝነት ደግሞ ተሰጦዖው ነበር፡፡ ሰዕድ ከኢስላም በፊት ሁለንተናውን ለሆነ ተልዕኮ የሚያዘጋጅ የሚመስል አብሰልሳይ ነበር፡፡ ጃሂሊያው ክፉኛ ያስመረረው ወጣት፡፡ወዲያው ግን ኢስላማዊው ጮራ በነብያዊ ለዛ ታጅቦ በራ፡፡ ሰዕድ ለነብዩ አጋር ሆነ፡፡ ይህን ሲወስን ዕድሜው ገና 17 ዓመት ብቻ ነበር፡፡

በጣም የምትወደው እናቱ ክፉኛ ኮነነችው፡፡ ከምግብና መጠጥ በመታቀብ ራሷን እንደምታጠፋ አረዳችው፡፡ ኢስላምን የማይተው ከሆነ በአሰቃቂ ሞት ዱንያን ለቃ ዘላለም ሲፀፀት እንደሚኖር ነገረችው፡፡ እሱ ግን ቁርጥ አቋሙን አሳወቃት፡፡ ኢስላም ከደሙ ተደባልቋል፡፡ ሊተወው ፈፅሞ አይቻለውም፡፡ ሰዕድ (ረ.ዐ) ያን ጀግንነትና ቀስተኝነት ለህይወት መንገዱ ኢስላም ተጠቀመበት ፡፡ በፍልሚያ ዘመቻ ሜዳዎች ላይ ተገኝቷል፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) በኡሁድ ዘመቻ ዕለት የአጋርያን ጥቃት በርትቶና የድል ሚዛኑ ወደነርሱ አድልቶ በዙሪያቸው ሆነው ከተከላከሉ የቁርጥ ቀን ጀግኖች ውስጥ ሲሆን መልዕክተኛው*‹‹ሰዕድ ሆይ! ወርውር እናቴም አባቴም ፊዳ ይሁኑልህ››*

ሲሉ ፍቅርና ክብራቸውን ገልፀውለታል፡፡ ይህን በቀላሉ የማይገኝ ውድ ስጦታ የተቸረ የመጀመሪያውና ብቸኛው ሶሃባ ነበር፡፡ የቃዲሲያን ጦርነት እግሩን ታሞ እያለ እንኳ መርቷል፤ ለድልም በቅቷል፡፡

### *ዙበይር ኢብኑል-ዓዋም (ረዐ)*

-የነብዩ(ሰዐወ) ሓዋሪያ

-ከኢስላም ምርጥ ፈረሰኞች ውስጥ አንዱ

-የጦር ግንባሮች ጀግናና

- የኢስላማዊው ጥሪ ቀኝ እጅ የነበረ ድንቅ ወጣት ነበር፡፡

ይህ ድንቅ ስብዕና ኢስላምን ሲቀበል ዕድሜው ገና 15 ዓመት ብቻ ነበር፡፡ በዘመናችን ይህ ዕድሜ የስንተኛ ክፍል ተማሪ ማለት ይሆን...የ8ተኛ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ዙበይር ሲያስብና፤ ሲተገብር የነበረውን ጀብዱ መፈፀም ይችላል......

አዎ! መታሰብ አለበት፡፡ ዙበይር ከላይ የነበሩትን ስሞች የተጎናፀፈው በዚህ ዕድሜ ነው፡፡

### *ጦልሃ ኢብኑ ዑበይዲላህ(ረዐ)*

-መካ ውስጥ ለበቀለችው ኢላማዊ ጥሪ ደጀን

-ወደ አላህ መንገድ ከተጣሩ ሰዎች አንጋፋው

-ጀግና ፤ፈረሰኛና ድንቅ የጦር ስልት አዋቂ

-እንዲሁም በአላህ መንገድ ላይ ገንዘቡን በመስጠት የሚታወቅ ቸር እንቁ ሶሃባ ነበር፡፡ ኢስላምን ሲቀበል ገና 16 ዓመቱ ነበር፡፡

### *አርቀም ኢብን አል-አርቀም አል-መኽዙሚ (ረዐ)*

ይህ ስም ሲነሳ የሁሉም ሙስሊም ህሊና ውስጥ አንድ የታሪክ ክስተት ይታወሰዋል፡፡ የቁረይሾችን በተለይ የበኒ መኽዙሞችን (የነ አቡ-ጀህልን) ተፅዕኖ ተቋቁሞ በቤቱ ውስጥ ለ13 ዓመታት ኢስላማዊውን ሰማያዊ ጥሪ በእንግድነት ያስተናገደ ሁሌም የሚታወስ የኡመተ-ሙሐመድ ባለውለታ ነው፡፡ ይህ ድንቅ ሰው ኢስላምን ሲቀበል ዕድሜው ገና 16 ዓመት ብቻ ነበር፡፡

በዕድሜያቸው ትንሽ ግን በተግባራቸው ትልቅ ዘላለማዊ ስሞችን እያወሳን ነው፡፡ ምድር ከነበረችበት ፅልመታዊ ገፅታ ወደ ብርሃናዊ ፍካት ያወጡ ነበሩ፡፡ በርግጥ የቆሙለት እሴት፤የታገሉለት ዓላማ፤የኖሩለት ስነ-ምግባር፤የተሰዉለት ኢስላም ትልቅ ነው፡፡

## ዓሊይ ኢብኑ አቢ ጧሊብ(ረዐ)

ነብዩ(ሰዐወ) መልዕክቱን ማስተማር ሲጀምሩ ገና የ 10 ዓመት ታዳጊ ነበሩ፡፡ በዚህ ለጋ ዕድሜ ኢስላማዊው መልዕክት ቀረበላቸው፡፡ መቀበሉን አላህ አገራላቸው፡፡ እናም ይህ የልጅ አዕምሮ የአላህን አንድነት፤ የመልዕክተኝነትንና ነብይነትን ፅንሰ-ሃሳብ፤ሰለ ራዕይና ህይወትን በአላህ መንገድ ላይ ፈዳ ስለማድረግ ከአዛውንት ህሊና በተሻለ መልኩ ተገነዘበ፡፡ ይህ ሁሉ ግንዛቤ በአስር ዓመት ዕድሜ ላይ ተሁኖ ነው፡፡ ይህ ህፃን በዚያ ኢማን ወንጀል ተደርጎ በሚቆጠርበት  ወቅትና ጊዜ እንዴት ተደብቆ ወደ አርቀም ቤት መግባት እንዳለበት፤ተደብቆ መስገድንና፤ከሰዎች ዕይታ ራቅ ብሎ ቁርአንን ማንበብ እንዳለበት ያወቀ ህሊና ነበረው፡፡

## ዘይድ ኢብኑ ሳቢት(ረዐ)

«በአላህ ይሁንብኝ ቁርአንን ሰብስብ ብለው ከሚያዙኝ ተራራን ከቦታው አንስተህ ሌላ ቦታ አድርግ ቢሉኝ ይቀለኝ ነበር፡፡»

ለአቅመ አዳም ያልደረሰ፤ሰውነቱ ያልፈረጠመ ለጋ  የ13 ዓመት ታዳጊ ነበር፡፡ እንዲህ ከመሆኑ ጋር ግን ለኡመተል-ኢስላም ጉዳዮችን በመፈፀም ላይ ራሱን የወጠረ ልጅ ነበር፡፡ የሙስሊሞች ሰራዊት ሙሽሪኮችን ለመግጠም ወደ በድር

ዘመቻ ሊወጣ እንደሆነ ይህ ለጋ ታዳጊ ይሰማል፡፡ ልቡ ውስጥ ኢስላምንና መልዕክቱን የመርዳት ፅኑ ወኔው ተንቀሳቀሰች፡፡ እሱን በቁመት የሚበልጥ ሰይፉን በማንገብ እግሩን ነቅሎ እየሮጠ የሙስሊሙን ሰራዊት ለመቀላቀል ሄደ፡፡ ይህ ታዳጊ የጂሃድን ልቅና፤ጠላትን የመጋፈጥ ምንዳ፤የአላህን ዲን መታደግ ምን ያህል ከፍተኛ ማዕረግ እንደሆነ ተገንዝቧል፡፡ ነገር ግን ከሰራዊቱ መስከ ሲደርስ ድንገት ደነገጠ፡፡

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በዕድሜም በሰውነትም በጣም ትንሽ ስለሆነ ጉዳት እንዳይደርስበት በመስጋት ከጂሃድ መለሱት፡፡ ወደ እናቱ ነዋር ቢንት ማሊክ (ረ.ዓ) አምርሮ እያለቀሰ ተመለሰ፡፡ ለእናቱም «የአላህ መልዕክተኛ ከጂሃድ ከለከሉኝ፡፡» ሲል ብሶቱን ነገራት፡፡ ዲኗን በቅጡ የተገነዘበችው እናቱ ግን « አትዘን ኢስላምን በሌላ መልኩ ማገልገል ትችላለህ፡፡ ጂሃድ በሰይፍ ባይሆንልህ በምላስና ብዕርም ይሆናል» በማለት የልጇን አስተሳሰብ በበሰለ ቅኝቷ አሰፋችው፡፡ መፃፍና ማንበብ ትችላለህ፡፡ ሁሉም ለተፈጠረለት የተገራ ነው፡፡ ከቁርአን ብዙ ሽምድደሃል ስትል አፅናናቸው፡፡ ቀጥላም "በዚህ ልዩ ችሎታህ ኢስላምንና ሙስሊሞችን በምን መልኩ ማገልገል እንዳለብህ ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንማከርበት" በማለት ከተወሰኑ የጎሳዋ አባላት ጋር ይዛው ሄደች፡፡ ለነብዩም(ሰ.ዐ.ወ) «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ይህ ልጃችን ዘይድ ከቁርአን 17 ምዕራፎችን ወደ ልቦናዎት እንደወረደ አድርጎ ሃፍዟል፡፡ የማንበብና መፃፍ ልዩ ችሎታ ደግሞ አለው፡፡ በነዚህ ችሎታዎቹ እርሶን መቅረብ ይሻል፡፡ ከፈለጉም ያድምጡት፡፡» ብለው ተናገሩ፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በደንብ ሰሙት፡፡ ውስጣዊ ችሎታውን አወቁ፡፡ የእርካታውን መርጊያ ተረዱለት፡፡ ከማንም ያለፈለጉትንና ማንንም ያለዘዙትን ልዩ ተልዕኮ አሸከሙት፡፡ የመፅሐፍ ባለቤቶችን ቋንቋ  መማር፡፡ ጭራሽ ደግሞ የሰማያዊ አዋጅ(ወሕይ) ፀሃፊ ሆነ፡፡.......ቀናት አለፉ፤ዓመታት ነጎዱ፤ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ሞቱ፡፡ በወቅቱ አንጋፋ ሶሃቦች ለመጪው ዘመን ትውልድ አሰቡ፡፡ ከቁርኣን አንዷት አንቀፅ ብትጠፋ ሊያስከትል የሚችለውን ኪሳራ አሰሉ፡፡ ስለዚህም ቁርአን በአንድ መፅሃፍ መሰብሰብ እንዳለበት ታመነ፡፡ አቡበክር(ረ.ዐ) ከዘይድ የተሻለ ሰው ስላላገኙ ሙሉ ኃላፊነቱን ሰጡት፡፡ ምክንያቱም ዘይድ እያንዳንዷ አንቀፅ መች እንደወረደች፤እንዴት እንደወረደች፤በምን ምክንያት እንደወረደች

፤የአወራረዱን ቅደም ተከተል የሚያውቀው እርሱ መሆኑን ያውቁ ነበር፡፡ ይህን ትልቅ አደራና ኃላፊነት ሲሸከም የ21 አመት ወጣት ነበር፡፡ ነገር ግን በሚገባ ተወጣው፡፡ ይህ ዕድሜ በዘመናችን ምን ላይ ይውል ይሆን?.......

ቢላል፣ኸባብ ኢብን አል-አረት(ረ.ዐ) ሀቅን አጥብቀው በመያዛቸው የእምነትና በነፃ የማሰብ መብታቸውን ተነፍገው የስቃይ እና እንግልትን ገፈት ቀምሰዋል፡፡ በጠራራ ፀሀይ በዓረቢያ አቃጣይ አሸዋ ላይ ተጎትተዋል፡፡ በእሳት ተቃጥለዋል፤ በጋለ ብረት ተተኩሰዋል፡፡ ሁሉን በፅናት ተወጥተው ግን ድልን ተጎናፅፈዋል፡፡ አላህም (ሱ.ወ) መልካም ስራቸውን ወደደላቸው፡፡

አቡል ሐሰን አንነደዊ እንዲህ ይላሉ፡-«መልዕክተኛው (ሰዐወ) ያለ መታከት ወደ ኢስላም ጥሪ አደረጉ፡፡ ጣኦታውያኑ ሊያስተጓጉሏቸው ሞከሩ፡፡ ጥሪያቸውን የወጣትነት መረብ፣የምድር ብልጭልጭ ያላታለላቸው ወጣቶች ተቀበሉ፡፡ ከአጋርያኑ ያልተወረወረባቸው የቀስት ዓይነት አልነበረም፡፡ ነገርግን ፅናትንና እምነትን እንጂ አልጨመረላቸውም፡፡ ጭንቀታቸው ወዲያኛው ዓለም፣ትልቁ ፍላጎታቸው ጀነት ሆነ፡፡ ምክንያቱም መልዕክተኛው(ሰዐወ) ነፍሳቸውን በቁርአን፣መንፈሳቸውን በኢማን ኮተኮቷቸው፡፡ በንፁህ ሰውነት፣ በመጠቀ መንፈስና በተቅጣጨ ህሊና በቀን አምስት ጊዜ ለዓለማቱ ጌታ ይጎነበሳሉ፡፡ የልብ ንፅህና፣የባህሪ ማማር፣ከቁስ የበላይነት፣ ከስሜት ተነጂነት ወጡ፡፡ ከውስጣቸውም የሰይጣን ድርሻ ወጣ፡፡ ከነፍሳቸው የነፍሳቸው ድርሻም ተወገደ፡፡ ማጣት የማይበግራቸው፣ችግር የማያስበረግጋቸው፣ ንግድ የማያታልላቸውና በመሬትም ላይ ብክለትንና ኩራትን የማይሹ፣ምድር ላይ የሚንቀሳቀሱ የአኼራ ሰዎች ሆኑ፡፡»

رَّضِيَ اللَّهُ عَنْهُمْ وَرَضُوا عَنْهُ ۚ ذَٰلِكَ لِمَنْ خَشِيَ رَبَّهُ [٩٨:٨]

**«አላህ ከእነርሱ ወደደ፡፡ ከእርሱም ወደዱ፡፡ ይህ ጌታውን ለፈራ ሰው ነው፡፡»**[2]

---

[1]አል–በይናህ 98

ሶሀቦች ምድር ላይ ልዩ ትውልድ (Unique Generations) ነበሩ፡፡ ኡማው በተምሳሌትነት ይይዛቸው ዘንድ መልዕክተኛው ከአብሪ ከዋክብት ጋር አመሳስለዋቸዋል፡፡
«ሶሀቦቼ (ባልደረቦቼ) እንደ ከዋክብት ናቸው፡፡ በማናቸውም ብትከተሉ ቀጥተኛ ትሆናላችሁ፡፡ »ብለዋል፡፡

# ኢስላም እና ማፍራት የሚሻው ትውልድ

የሁለት ዓለማትን ስኬት ለፍጡራን ለማበርከት በዘመናት ራስ ላይ ተገንብቶ፤የኢስላማዊው ብርሀን ችቦ በብዙ ነብያት እጅ ተጨብጦ እዚህ ደርሷል። በህይወት መንገድነቱ በተጨባጭ ውጤትን አሳይቷል፡፡ የሰዎችን ስብዕና ቀረፃ ከምናባዊነት ወደተጨባጭ አሳድጓል፡፡ ፍጡራን ይጠቀሙበት ዘንድ የተስተካከለ እና ሚዛናዊ ህግጋትን ዘርግቷል፡፡ ጉዳት ይደርስባቸውና ይጨናነቁ ዘንድ አልተደነገገም፡፡ ለዚህ ነው አላህ (ሱ.ወ) የቁርአንን መውረድ ተልዕኮ ሲገልፅ እንደህ ያለው፡፡

طه*مَا أَنزَلْنَا عَلَيْكَ الْقُرْآنَ لِتَشْقَى

*«ጧ.ሀ ቁርአንን ባንተ ላይ እንድትቸገር አላወረድንም፡፡»*

እምነትን ከስልጣኔ እና መሻሻል ለይቶ የማያየው ተፈጥሯዊው ሀይማኖት ኢስላም ዕንቁ ትውልድን መቅረፅ ይሻል፡፡ በተለይ ወጣቱን እጅግ ይፈልገዋል፡፡ ምክንያቱም ተልዕኮን ለማሳካት ወጣቱ ዘንድ ያልደከመ ጉልበት፣ያልነጠፈ ብርታት እና ያልወየበ አስተሳሰብ ስላለ ነው፡፡ እንዳሳለፍነው ወጣቱን በመጠቀም ብክለትን ምድራዊ ተኩላዎቹ ፅዮናውያን

---

2 ጣሀ፤ 1–2

ይሻሉ፡፡ ኢስላም ደግሞ የወጣቱን አዕምሮ በዕውነትና ዕውቀት በማበልፀግ የዱንያ መሪ ሊያደርገው  ይፈልጋል፡፡ ኢስላም የባንዲራውን ካስማ በወጣቱ ልቦና ውስጥ ተክሎ ማውለብለብ እና መስቀል ይፈልጋል፡፡ ለንዋይ ያላጎበደደ የአስተሳሰብ ዘመቻ ጥቃት ሰለባ ያልሆነ ትውልድ ይሻል፡፡

በእምነቱ የሚኮራ፣ በተግባር የሚያሳይ እና ለሌሎች የሚተርፍ ዜጋን በስሩ ማስጠለል ይሻል፡፡ በምድር ላይ ወጣትነቱን በአግባቡ ተጠቅሞ የሁለት ሀገር ትርፈኛ እንዲሆን ጥረት የሚያደርግ ስብዕና ኢስላም እጅግ ይወዳል፡፡

ተጠያቂነትን የተገነዘበ፣ ሀላፊነትን የሚወጣ፣ታማኝነትን የተላበሰ እና ሰብዓዊነትን ያነገበ ነገ አላህ ፊት መቆምን የሚሰጋ ወጣት የኢስላማዊው መንገድ ምርት ነው፡፡

ብክለትን በሩቁ የሚኮንን፣ የፀያፍ ተግባራትን በር የሚዘጋ፣ለማህበረሰብ ችግሮች መፍትሄ የሚያመነጭ፣ለነፃነት እና እኩልነት የሚታገል በእምነቱ ድርድር የማያውቅ ጀግና ትውልድ የኢስላም ልጅ ነው፡፡

ዛሬ ላይ በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ፣ በትምህርት እና ንግድ፣ በዕድገትና ስልጣኔ ምጡቅ ሰዎች የኢስላም ፍሬዎች  ይሆኑ ዘንድ ጥረት ያደርጋል፡፡

የሰዎች ከስነ-ምግባር መሸሽ፣ከዕድገት ማፈግፈግ እንቅልፍ የሚነሳው አሳቢ ለኢሰላም ውድ ንብረት ነው፡፡

# በወጣትነት እና እርጅና መሀል

ወጣትነት ሙሉ ጤንነት ከጠንካራ የመስራት እና የማወቅ መንፈስ ጋር የተዋሀደበት እርከን ነው፡፡

እርጅና ጤንነት ይጎድልበታል፡፡ በአብዛኛው የሞትን መምጣት እንጂ የማይጠብቁበት እርከን ነው፡፡

ወጣትነት ላይ አዕምሮ በፍጥነት የሰጡትን ይቀበላል፡፡ ያስተነትናል፡፡ ልብ ደም ይረጫል፡፡ ኩላሊት ይሰራል፡፡ ደም ይዘዋወራል፡፡ ጉበት ስራውን ያከናውናል፡፡ ዓይኖች በሚገባ ያያሉ፡፡ ጆሮ ሁሉን ይሰማል፡፡ እግሮችና እጆች ሁሉን ይፈፅማሉ፡፡

እርጅና ላይ ግን አዕምሮን በቀላሉ መግራት ይከብዳል፡፡ አስቀድሞ የያዘውን ሙጥኝ ይላል፡፡ አዲስ ሐሳብን ተቀበል ቢሉት በጄ አይልም ያመነታል፡፡ ልብ የደም ርጭቱን እየቀነሰ ይመጣል፣ በደቂቃ ከ65 ጊዜ በላይ ደልቃ ደም ትረጭ የነበረችው ቱቦ (Valve) ትደክማለች፡፡ ኩላሊት ለዘመናት የማስወገድ (Excretion) ስራ ሲሰራ ስለነበረ ጡረታ ይጠይቃል፡፡ ደም በየጊዜው የሚቀያየረው በወጣትነት ዘመን ነው፡፡ አሁን ግን ደም አይቀየርም፡፡ ሰውነት እና ቱቦዎች ውስጥ ደም መርጋት ይጀምራል፡፡ ማቅጠኛ መድሀኒቶች ካልተወሰዱ ወደ ሞት ይገፋል፡፡ ጉበት ይደክማል፡፡ ዓይኖች ይፈዛሉ፡፡ ጆሮዎች ይሰንፋሉ፡፡ እግርና እጅ እንተፈለጉት አይላወሱም፡፡ ይተሳሰራሉ፡፡ በሌሎች ድጋፍ እንጂ መንቀሳቀስ ከባድ ይሆናል፡፡

ለዚህ ነው ነብዩ(ሰዐወ) የሚከተለውን ምክር የለገሱት

*‹‹ከአምስት ነገሮች በፊት አምስት ነገሮችን ተጠቀም፡፡**ወጣትነትህን ከእርጅናህ፣ጤናህን ከህመምህ፣ሰፊ ጊዜህን ከውጥረትህ፣ሐብትህን ከማጣትህና፣ህይወትህን ከሞትህ በፊት፡፡››***

## በህይወትህ ተጠቀምት

የዚህች ዓለም ምሳሌ የጠዋት ጤዛ ነው፡፡ ጤዛ ጠዋት ታይቶ ረፋድ ላይ በደካማና ለስላሳ የፀሀይ ሙቀት ይወገዳል፡፡ ህይወት ምድር በምትባል ለምለም አፈር ላይ የተተከለች ችግኝ ናት፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ዛፍ ትሆንና ተቆርጣ አሊያም በጣም ትልቅ ሆና ደርቃ ትጠፋለች፡፡ ለፍጡራንና የአላህ ባሪያዎች ጠቃሚ ህይወት አለች፡፡ በተቃራኒውም ጎጂ ሕይወትም አለች፡፡ ይህን አስመልክቶ እስቲ ቁርአንን እንስማው፡-

أَلَمْ تَرَ كَيْفَ ضَرَبَ اللّهُ مَثَلاً كَلِمَةً طَيِّبَةً كَشَجَرةٍ طَيِّبَةٍ
أَصْلُهَا ثَابِتٌ وَفَرْعُهَا فِي السَّمَاء* تُؤْتِي أُكُلَهَا كُلَّ حِينٍ
بِإِذْنِ رَبِّهَا وَيَضْرِبُ اللّهُ الأَمْثَالَ لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمْ يَتَذَكَّرُونَ
إبراهيم: ٢٥

***«አላህ መልካምን ቃል ሥርዋ (በምድር ውስጥ) የተደላደለች ቅርንጫፍዋም ወደ ሰማይ (የረዘመች) እንደሆነች መልካም ዛፍ አድርጎ ምሳሌን እንዴት እንደገለጸ አላየኽምን። ምግቧን (ፍሬዋን) በጌታዋ ፈቃድ በየጊዜው ትሰጣለች፡፡ አላህም ለሰዎች ይገሰጹ ዘንድ ምሳሌዎችን ይገልጻል፡፡>>***[3]

በጓሮ የሚተከል ዛፍ ካደገ በኋላ ፍራፍሬ የሚሰጥ መሆን ቢችል ጥሩ ነው፡፡ የኡማው ወጣት ምሳሌም ይህ ነው፡፡ በኢስላም ጉያ ስር ተጠልሎ ያደገ ወጣት በማንኛውም ወቅት ለህዝብ ግልጋሎት (service) ለመዋል ዝግጁ የሆነ ነው፡፡ በህይወት ምሳሌ ውስጥ ክፉዋና ጎጂዋ ደግሞ

وَمَثلُ كَلِمَةٍ خَبِيثَةٍ كَشَجَرَةٍ خَبِيثَةٍ اجْتُثَّتْ مِن فَوْقِ الأَرْضِ مَا لَهَا مِن
قَرَارٍ إبراهيم: ٢٦

***«የመጥፎም ቃል ምሳሌ ከምድር በላይ የተገለሰሰች ለእርሷ ምንም መደላደል የሌላት እንደኾነች መጥፎ ዛፍ ነው፡፡»***[4]

---

[3] *ኢብራሂም 24–25*

[4] *ኢብራሂም 26*

አላህ ነፍስን ለዚህ ዓይነት ተግባር አልፈጠራትም፡፡ ወጣቱ ሙስሊም ከላይ ያየናቸው የእርጅና ጣጣዎች ሳይመጣበት ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሁለት ምክሮችን ለግሰውታል፡፡

## *ሀ/ ወጣትነትን በሁሉም ዘርፍ በአግባቡና ጥንቃቄ መጠቀም፡፡*

የምፅዓት ቀን ማንኛውም ሰው ከአራት ነገሮች ሳይጠየቅ በፊት እግሩ ከሂሳብ ሜዳ ወደ ጀነትም ይሁን ጀሀነም አይንቀሳቀስም ሲሉ ነብዩ በሀዲሳቸው ተናግረዋል፡፡ *‹‹ወጣትነትን ተሰጥተህ ነበር በምን አዋልከው?››* የሚለው ዋናው ነው፡፡

ስለዚህ አሉ ወዳጃችን (ሰ.ዐ.ወ) አምስት ነገሮች መጥተው የአምስት ነገሮችን ለዛ ሳያጠፉ ተጠቀምባቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ***‹‹ወጣትነትህን ከእርጅናህ በፊት››*** ብለዋል፡፡

## *ለ/ ወደ መጃጃት የዕድሜ ክልል እንዳይደርሱ አላህን መለመን*

ወጣቶች በወጣትነት ዘመናቸው በታላቅ ሞራል ተነሳስተው የሰሯቸው ትላልቅ ስራዎቻቸው በጎልማሳነት እድሜ ላይ ትቢያ ሲሆን ይታያል፡፡ ከዚህ አላህ እንዲጠብቃቸው ዱዓ ማድረግ አለባቸው፡፡ ‹‹አላህ ሆይ ! ለዲንህ ግልጋሎት አውለኝ፣አትተካብኝ....››

ዱዓ የአማኞች መሳሪያ ነው፡፡ አላህ ሁሌም ለማኞችን ይሰማል፡፡ ጥሪያቸውን ይቀበላል፡፡ ለነርሱ ከነርሱ በላይ የሚያውቅላቸው ነውና መልካማቸውን ይመርጥላቸዋል፡፡

በምድራዊ ህይወት መልካም የተባሉ ነገራትን ሁሉ አሰርተኸኝ ከመጃጃቴ በፊት ሰማዕት አድርገኝ ብሎ መለመን ትልቅ ዱዓ ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) በዱዓቸው *‹‹አላህ ሆይ ! ከመጃጀት በአንተ እጠበቃለሁ፡፡ ››* ይሉ ነበር፡፡ ስለዚህ ወጣትነትህን በአግባቡ ተጠቀመው፡፡ በማይረባ የህይወት ጉዞ ባክኖ የእርጅና ቤት እንዳይገነባበት ጥረት አድርግ፡፡

ምክንያቱም ከወጣትነትና ልጅነት በኋላ እርጅና የሚባለው እርከን ይመጣል፡፡ የዕድሜ ርዝማኔ ከመልካም ስራ ጋር ከሆነ እጅግ ጥሩ ነገር ነው፡፡ ነብዩ

(ሰ.ዐ.ወ) በሀዲሳቸው *«ከሰዎች በላጩ ዕድሜው ረዝሞ ስራው ያማረው ነው፡፡»* ብለዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ እንደፈጠረን ከዚያም እንደሚገድለን ይገልጽና ከኛው ውስጥ ደግሞ ወደ መጃጃት የዕድሜ ክልል የሚደርስ እንዳለም ይገልፃል፡፡

وَاللَّهُ خَلَقَكُمْ ثُمَّ يَتَوَفَّاكُمْ ۚ وَمِنكُم مَّن يُرَدُّ إِلَىٰ أَرْذَلِ الْعُمُرِ لِكَيْ لَا يَعْلَمَ بَعْدَ عِلْمٍ شَيْئًا ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ قَدِيرٌ [١٦:٧٠]

***«አላህም ፈጠራችሁ፤ ከዚያም ይገድላችኋል፡፡ ከእናንተም ከዕወቅት በኋላ ምንንም ነገር እንዳያውቅ ወደ ወራዳ ዕድሜ የሚመለስ ሰው አልለ፡፡ አላህ ዐዋቂ ቻይ ነው፡፡»*** [5]

መጃጃት በጣም ረዥምና የተንዘላዘለ የዕድሜ ክልል ነው፡፡ ከዕውቀትና የሕሊና ብስለት በኋላ ወደ ህፃን ባህሪ ይመልሳል፡፡ እንደ ልጅ ይሄ ጥሩ አይደለም ይህ ደግሞ ይጎዳል የሚሉ መመሪያዎችን ከሌሎች ያስከትላል፡፡ በሰው እጅ ውስጥ ይጥላል፡፡ አደግንና ሰለጠንን ባሉ ሀገራት ደግሞ የዕርጅና ቤት (old age home) ውስጥ ያስወረውራል፡፡ በእርግጥ በተወለዱ ልጆች ላይ የወላጆች መብት የፀና ነው፡፡ እስከ ህልፈታቸው ቀን ድረስ አስፈልጎታቸውን በሙሉ ያለ መሰላቸት ማሟላት ግዴታ ነው፡፡ አላህ ሆይ !አንተው መልካሙን ግጠመን፡፡

# 2

# ለምጡቅ ማህበረሰብ ግንባታ

---

[5] *ነ ህል፤ 70*

## *በመንፈሳዊው ዘርፍ*

ከተጨባጭ ዕውቀትና ብስለት በኋላ ማህበረሰብን መገንባት የአንድ ህዝብ አብሰልሳይ ወጣቶች ሀላፊነት ነው፡፡ የመንፈስ እርቃናዊነትን በልብሰ-ኢማን መጠቅለል ለላቀ የስነ-ምግባር ምጥቀት ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡ የሀይማኖቱን መቅኒ መሰረቶች በሚገባ በተግባር ካዋሉ፤ ራስን ከገነቡና ማንነትን ለአላህ ካስገዙ በኋላ ሌሎችን ማስተማር ዋጋው ጀነት ነው፡፡
ወጣቱ አምስት ወቅት የግዴታ ሶላቶቹን ጊዜያቸውን ጠብቆ በህብረት ከሰገደ ሰናይ ባህሪን ይላበሳል፡፡ ምክንያቱም ሶላት በባህሪዋ ከፀያፍና አልባሌ ተግባራት ታቅባለች፡፡

اتْلُ مَا أُوحِيَ إِلَيْكَ مِنَ الْكِتَابِ وَأَقِمِ الصَّلَاةَ ۖ إِنَّ الصَّلَاةَ تَنْهَىٰ عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنكَرِ ۗ وَلَذِكْرُ اللَّهِ أَكْبَرُ ۗ وَاللَّهُ يَعْلَمُ مَا تَصْنَعُونَ [٢٩:٤٥]

***«ከመጽሐፍ ወደ አንተ የተወረደውን አንብብ፡፡ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፡፡ ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡ አላህንም ማውሳት ከሁሉ ነገር በላጭ ነው፤ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃል፡፡»*** [6]

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሰላትን በአግባቡ ጠብቀው የሚሰግዱ፣ የአላህን እቀባዎች የሚጠብቁና ከመጥፎ ከልክለው በበጎ የሚያዙ ወጣቶች ቁጥር ሲበረክት የመንፈስ ህንፃ በፅኑ መሰረት ላይ ይገነባል፡፡ ግዙፍና አንፀባራቂም ይሆናል፡፡ ወጣቱ ዲኑን በሚገባ አውቆ በተግባር ካዋለ በመንፈሳዊው ዘርፍ ምጡቅ ስብዕናን ለመገንባት ወሳኝ ግብዓት ይሆናል፡፡ ራሳቸውን ለአላህ አስገዝተው፣መስጂዶችን ተቆራኝተው መጪያቸውን ለማሳመር የሚጥሩ ወጣቶች ያሏት ሀገር ከውስጥም ከውጭም ጥቃት የተጠበቀች ትሆናለች፡፡ የሌሎችን አስተሳሰብና የህይወት ፍልስፍና ተላብሰው መንፈሳቸውን የተሰለቡ

---

[6] *አል-ዓንከቡት 45*

ወጣቶች የህይወትም የድንበርም አስደፋሪዎች ይሆናሉ፡፡ አሳልፈው ለስሜታቸው የሰጡት ህሊናቸው እርቃኑን ነው፡፡

## ወጣቱና አላህን መፍራት(ተቅዋ)

*«ተቅዋን ተሰነቁ፡፡ ከመልካም ስንቆች ሁሉ በላጩ አላህን መፍራት ነው፡፡»*

ሰባት ዓይነት ሰዎች የምፅዓት ቀን የአላህ እንጂ የማንም ጥላ በሌለበት ቀን ከጥላው ስር ይውላሉ፡፡ ወጣቱ ሰባቱንም የመሆን ሰፊ እድል በእጁ ነው «ፍትሃዊ መሪ፣አላህን ፈርቶ ዓይኑ ያነባች፣ አላህን በማምለክ ያደገ ወጣት፣ የውበትና ክብር ባለቤት እንስት ለሃራም ጋብዛው አላህን እፈራለሁ ያለ፣ቀኝ እጁ ሲሰጥ ግራው እስከማያይበት የሚደብቅ፣በአላህ መንገድ ተዋደው በርሱ የተለያዩ፣ልቦናው ከመስጂድ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው ሰው፡፡» ሲሉ መልዕክተኛው ተናግረዋል፡፡ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰትን አለመግባባት ያለ አድሎ መዳኘት ከቻለ፣የመጪውን ዓለም የጉዞ መስመሮች አስታውሶ ከልቡ ወደ አላህ ተመልሶ ካለቀሰ፣አምልኮን የህይወቱ አንድ ክፍል ያደረገ፣ጊዜያዊ ፍላጎቶቹን ችላ ካለ ከላይ የተጠቀሱትን ላለመሆን የሚይዘው አይኖርም፡፡ ንፉግነትን ጥሎ በእጁ ካለው የበታቾቹን ከፈቀደ፣የእምነት ወንድሞቹን ከወደደ፣መስጂድ የዓይኑ መርጊያ ከሆነለት እድለኛ ነው፡፡ ወጣቱ እነዚህን ማድረግ ይችላል፡፡

አላህን መፍራት የእምነት አስኳል ነው፡፡ አላህ ቀደምት ህዝቦችንም ይሁን የአሁኑን ትውልድ አዞበታል፡፡ በአደራነትም አስተላልፎታል፡፡ ቁርአን ውስጥ እጅግ ብዙ ቦታ ላይ ገልፆታል፡፡ ነስር (የአላህ እርዳታ) የሚገኘው በርሱ እንደሆነም አትቷል፡፡

ወጣትነት ለስሜታዊ ጉዞ ቅርብ ነው፡፡ ለወንጀል ተግባርም የተመቸ ጊዜ ነው፡ ፡ ነገር ግን በዚህ አፍላ የእድሜ ክልል ራሱን በዒባዳና ተቅዋ አጥር ስር ጠብቆ ያኖረ ወጣት ከሁሉም በላጭ ነው፡፡ የቂያማ ቀን ፍርሀት የለበትም፡፡ ሰላምንና መረጋጋትን አላህ ያጎናፅፈዋል፡፡ በታላቁ አላህ ዓርሽ ስርም ከሚጠለሉት ይሆናል፡፡

ተቅዋ የህይወት ስንቅ ናት፡፡ አላህ አማኞችን አዞባታል፡-

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ اتَّقُواْ اللّهَ حَقَّ تُقَاتِهِ وَلاَ تَمُوتُنَّ إِلاَّ وَأَنتُم مُّسْلِمُونَ

***«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁት እናንተንም ሙስሊም ሆናችሁ እንጂ አትሙቱ፡፡»*** [7]

ነብያት በሙሉ ህዝቦቻቸውን በተቅዋ አዘዋል፡፡ ኑህ ፤ሁድ፤ሷሊህ፤ሉጥና ሹዓይብ......

ለዚህም ነው አላህ ተቅዋን ለመጀመሪያዎቹም ለመጨረሻዎቹም ህዝቦች አደራ ያለው፡፡

ተቅዋ ማለት ሙሉ በሙሉ ከወንጀል መቆጠብ ነው፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ ባህሪ ሆኖ መሳሳትና መርሳት አለ፡፡ አላህን የሚፈሩ ወጣቶች መላዕክት ወይም ነብያት አይደሉም፡፡ ስህተትና መርሳት ይኖራል፡፡ ያኔ ታዲያ በተውበት ከገቡበት ውድቀት መንቃትና አላህን ማስታወሱ ነው ተቅዋ የሚሰኘው፡፡

እግራቸው አዳልጣ ወደ ስህተት ስታስገባቸው ፤ቶሎ ብለው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ለመመለስ ይፈጥናሉ፡፡ አላህ ልክ ስለ መልካም ባሪያዎቹ ሲናገር እንዳለው

وَالَّذِينَ إِذَا فَعَلُواْ فَاحِشَةً أَوْ ظَلَمُواْ أَنْفُسَهُمْ ذَكَرُواْ اللّهَ فَاسْتَغْفَرُواْ لِذُنُوبِهِمْ وَمَن يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلاَّ اللّهُ وَلَمْ يُصِرُّواْ عَلَى مَا فَعَلُواْ وَهُمْ يَعْلَمُونَ

[7] *አል ዒምራን 102*

*«ለነዚያም መጥፎ ስራን በሰሩ ወይም ነፍሶቻቸውን በበደሉ ጊዜ አላህን የሚያስታውሱና በኃጢያቶቻቸው ምህረትን የሚለምኑ ለኾኑት ከአላህም ሌላ ኃጢያቶችን የሚምር ኣንድም የለ (በስህተት) በሰሩትም ላይ እነርሱ የሚያውቁ ሲሆኑ የማይዘወትሩት ለኾኑት(ተደግሳለች)፡፡»* [8]

## ተቅዋና መልካም ውጤቶቿ

- ከጭንቅ መውጫና የሲሳይ ምንጭ ነው
- ከባድ ችግሮችን ማግራሪያ ነው
- ከጠላት ተንኮል መጠበቂያ ጋሻ ነው
- የአላህ እርዳታ አብሮ መሆን ነው፡፡
- የአላህን ውዴታ ያስገኛል
- ስራን በሙሉ ተቀባይ ያደርጋል
- በአኼራ የጀነት ባለቤት ያደርጋል
- ከጀሀነም እሳት ነፃ ያወጣል፡፡

ስለዚህ ተቅዋ (አላህን መፍራት) የስኬት ሁሉ ቁልፍ ነውና ወጣቱ ሊላበሰው ይገባል፡፡ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ ተፅዕኖውን ያየዋል፡፡ የጎመራ ፍሬውን ይቋደሰዋል፡፡ተጨባጭ ወደ ሆነ እውነተኛ ውጤት ይመራዋል፡፡

## ወጣቱና የቀን ተግባራቱ ቅኝት

1) ግዴታ ትዕዛዛትን መፈፀም
   - አምስት ወቅት ሶላትን በጀምዓ መስገድ
   - ሱና (ነዋፊል) ተጨማሪ ሶላቶችን በቀን 12 ረከዓዎችን በትንሹ ማስገኘት፡፡

---

[8] *አልዒምራን 135*

- ሶላተል ዊትርን መስገድ፡፡

2) ዊርዶች
   - በቀን ውስጥ ከቁርአን የተወሰነውን ማንበብ መሸምደድ፤ ማስተንተን
   - የጠዋትና ማታ፤ ከመኝታ በፊትና ከእንቅልፍ ሲነቁ የሚባሉ አዝካሮችን በራስ ላይ ግዴታ ማድረግ፡፡
   - በሁሉም ተግባርና ጉዳይ ላይ አላህን ማውሳት፡፡

3) ራስን በዒባዳ መጥመድ
   - ዕውቀትን መፈለግ
   - ሀላል ሲሳይን ማሰስ
   - ለኡማ ጉዳዮች መትጋት
   - ስፖርታዊና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ፡፡

እነዚህ ሁሉ ተደማምረው ሰውየውን ብቁ ያደርጉታል፡፡ ለጀነት ዕጩነት ያቀርቡታል፡፡ ምድራዊ ስኬትና ምኞቱ ይፋጠኑለታል፡፡ ሙስሊም ወጣት በሁሉም አቅጣጫ ምሉዕ ለመሆን ይፈጥናል፡፡

4) በተቻለ መጠን ከወንጀል መራቅ
   - ዓይንን መስበር
   - በሱስ አለመጠመድ
   - ሀሜት፤ውሸትና መሰል ነገሮችን መራቅ፡፡
   - ጊዜን አለማቃጠል

እነዚህ ዒባዳዎች ላይ ለተጠመደ ወጣት ነብዩ(ሰዐወ) «አላህ ግድፈት በሌለበት ወጣት ይገረማል፡፡» ሲሉ የምስራች ይናገራሉ፡፡

## *ወጣቱና ብሩህ ተስፋው*

ቅዠትን ብቻ መረጃና ሀይል አድርጎ የያዘው የአምባገነኖች እምነት አክትሞለታል፡፡ ህዝብን አታሎና ደልሎ ረግጦ መግዛት ከዘመኑ የህሊና ብስለት ጋር አብሮ ችሎ አይራመድም፡፡ መጪውን ጊዜ ኢስላም ያለማንም

ተቀናቃኝ ይረከበዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ተጨባጭ ማስረጃዎች ከታሪክ፤ከቁርአን እና ነብያዊ ትንቢቶች እንዲሁም ከነባራዊ ሁኔታ የምናየው ነው፡፡

## ከታሪክ

ኢስላም በታሪክ ገፁ እንደሚያስነብበን ከርሱ በተቃራኒ የተነሱ አስተሳሰቦችን፤ሀይሎችንና ጠላቶችን በሙሉ አንበርክኳል፡፡ ከጥንት ነብያት ጀምሮ እስከ ሙሐመድ (ሰዐወ) ዘመን ድረስ የታየ ነው፡፡ የመካ ቁረይሾች መልዕክተኛውን መቆሚያ መቀመጫ አሳጡ፡፡ ከሀገር እንዲሰደዱ ሰበብ ሆኑ፡፡ ተሰደው ባሉበት ቦታም ሳይቦዝኑ 13 ያህል የግድያ ሙከራዎችን ፈፀሙ፡፡ ባልደረቦቻቸውን ገደሉ፤አረዱ፤ረገጡ፤በደሉ፤ወዘተ.... ነገር ግን የአላህ እርዳታ ሲመጣ መካ ከአጋሪዎችና እኩይ ተግባራቸው ነፃ ወጣች፡፡

## ሰላሁዲን አል አዩቢ

ይህን ስምና ስብዕና የምእራቡ ዓለም መስቀለኞች በሚገባ ያውቁታል፡፡ በታሪካቸው ውስጥ ላይረሱት በጉልህ የሚታይ ጀግና ነው፡፡ መስቀለኞቹ በተደጋጋሚ ኢስላማዊውን የሻም ምድር ድንበር ይጥሳሉ፡፡ በይተል መቅዲስን በእጃቸው አድርገው ይጫወቱበታል፡፡ በ583 ዓ.ሂ ወይም እ.ኤ.አ 1187 ይህ ፈርጣማና የዓላማ ሰው ሰላሁዲን ታዲያ ከግብፅ ምድር ተነስቶ ወደ ቁድስ ሲያመራ የመስቀላውያኑ ጦር ሒጢን የተባለ ቦታ ላይ ጠበቀው፡፡ በፍልሚያው የሰላሁዲን ጦር ድል ቀናው፡፡ ሉዚናንና ሮናልድ የተሰኙ የቁድስን ባለስልጣናት ማረከ፡፡ ከዚህ ፍልሚያ በኋላ ቁድስ ነፃ ወጣች፡፡ በሙስሊሞች እጅ ዳግም ከዑመር ጊዜ በኋላ ተመለሰች፡፡

ሰው ሰውን ሳይሆን ሃያሉን አምላክ መገዛት ጀመረ፡፡ ዛሬ የስርዓት አልባ ፅዮናውያን አይሁዶች መጫወቻና መፈንጫ ብትሆንም በወቅቱ ግን በሙስሊሞች ቁጥጥር ስር ነበረች፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ዑመርም (ረዐ) በዘመነ-ኺላፋቸው ነፃ አውጥተዋት ነበር፡፡ ሙስሊሞች ባለፈ ታሪካቸው

ሽንፈትና ውርደትን ለብሰው አያውቁም፡፡ ዛሬ ግን ኡማው ዲኑን ትቶ የሌሎች አጨብጫቢና አጃቢ ሲሆን መሰረታዊ ማንነቱ ኪሳራ ላይ ወደቀ፡፡ ቢሆንም ሙስሊሙ እንቅልፍና መታለሉ ለጥቂት ጊዜ ነው፡፡ ንቃቱና ብርታቱ ግን ከአንዴ በኋላ መሸወድ አያውቀውም፡፡ ለዚህ ነው መልዕክተኛው (ሰዐወ) «ሙእሚን በአንድ ጉድጓድ ሁለቴ አይወድቅም» ያሉት፡፡ የዚህች ኡማ ዳግም ውልደት ሩቅ አይደለም፡፡ ለመወለድ ደግሞ የእርግዝናውንና ምጡን ህመም ማስተናገድ ይጠበቃል፡፡

ሙስሊሙ ወጣት ታሪካዊ ማንነቱ የጀግንነት የወኔ የአሸናፊነት ነው፡፡ ኢስላም የወጣቱን ክንድ መጠቀም ይሻል፡፡ በትግል ሜዳ አምባገነኖችንና ጥጋበኞችን በኢማን ስንቅነት ይረታል፡፡ ይህ ነባር ታሪካችን ነበር፡፡ ዛሬ ያንን ጀብዱ ለመፈፀምና ለመድገም ግንዛቤያችንን ማስተካከልና የጉዞ አቅጣጫችንን አንድ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

አዎ! ችግሩ ከዲናችን መራቃችን በኡማችን ጉዳይ አለመጨነቃችን እና ኢስላማዊውን ስልጣኔ አለመናፈቃችን ብቻ ነው ፡፡ ታሪክ ትልቅ ሀብት ነው፡፡ ለጉራና ፉከራ ሳይሆን ለስራ፤ስህተትን ለማረምና ዓላማን ለማረቅ ከሆነ ማለት ነው፡፡

አዎ! የሶሀቦቹ፤የሰለፎቹና የጀግኖቹ ጉዳይ ሲወራ ያልነበረ ህልም ሳይሆን የሆነ፤የተተገበረ ጀብዱ ነው፡፡ ማንም ቀጥፎ አላወራም፡፡ ዛሬም ታዲያ አዲስ ኢስላማዊ ታሪኮች እየተመዘገቡ ነው፡፡ በቱኒዚያ፤ሊቢያ፤ሱሪያ ኢስላምን ያረጀ ዕቃ አድርገው ትተው በስልጣን ዙፋናቸው ተደላድለው የፈለጉትን ሲገድሉ፤ ሲያርዱና ሲያስሩ የነበሩ አምባገነን መሪዎችን መንጭቆ ጥሏል፡፡ በቃችሁን፤ ሰለቻችሁን ሲሉም አደባባዮችን በሰልፍ አናውጠዋል፡፡ ከፊሎች ሲቆስሉ፤ ብዙዎች ለሞት ተዳርገዋል፡፡ ሀገር ንብረት ወድሟል፡፡ህፃናትና አዛውንት የህንፃ ፍርስራሽ ስር ቀብራቸው ሆኗል፡፡ ይህ ሁሉ እየሆነ ያለው በምድሪቱ ነቀዝ ቫይረሶች በጽዮናውያን ቅንብር ኡማውን በቁስ ብቻ በልፅጎ መንፈሱ ይራቆት ዘንድ በተተከሉ ነፍስ ያላቸው ጣዖታት አማካኝነት ነው፡፡ በግልፅ የሚታየው ፖለቲካዊ ልዩነት ይመስል እንጂ ቅሉ ኃይማኖት ነው፡፡

ሙስሊሙ ወጣት ሆይ ! ታሪክህን ዕወቅ፡፡ ሀገራችን ላይ ሙስሊም በመሆናቸው ብቻ ለስቃይና እንግልት ለሞትና ስደት ተዳርገው የነበሩ የአባቶቻችንና እናት ወንድሞቻችንን ታሪክ እናውቃለን፡፡ ዛሬም የዛ በደል ቅሪት ራሱ መልኩን ሳይቀይር መምጣቱን ሁሉም እያየ ነው፡፡ መጠነ-ሰፊ የበቀል እርምጃዎች በኡማው ሰውነት ላይ እያረፉ ነው፡፡ ሙስሊም በመሆኑ ብቻ በዘዴ እየተገለለ ነው፡፡ የኒቨርሲቲ ወስጥ ሂጃብ መልበስ በየዓመቱ ሞት ሽረት ትግል ሆኗል፡፡ ሙስሊም በመሆኑ ብቻ ሶላትና መብቶቹን ተነፍጓል፡፡ መስጂዶች መጫወት ካለባቸው ሚና መስገጃ ብቻ ተደርገዋል ፡፡

ይህ ታሪክ ሆኖ ብቻ ሳይሆን ማለፍ ያለበት፤ከፍተኛ የአስተሳሰብ ለውጥ፣ ትግልና መስዋዕትነትን ይጠይቃል፡፡ ነብዩ(ሰዐወ) « ***ድል ያለው ከትዕግስት ጋር ነው፡፡ የአላህ እርዳታም ከመጨናነቅ ጋር ነው»*** ብለዋል፡፡

## ከቅዱስ ቁርአንና ነብያዊ ትንቢቶች

ቁርአን ዘመን እያለፈ በሄደ ቁጥር ተዓምርነቱም ይጨምራል፡፡ ተገዳዳሪ የሌለው ብቸኛ መለኮታዊ መፅሀፍ ነው፡፡ ሙስሊሞች በእርሱ ምርጥ ህዝቦች ናቸው፡፡ በርሱ ጠላትን ያንበረክካሉ፡፡ መረጃን በመጥቀስ በክፋት የተወጠሩ ህሊናዎችን ይረታሉ፡፡ በወንጀል የቆሸሹ ልቦናዎችን ያፀዳሉ፡፡ ቁርአንን አጥብቆ የያዘ አይጠምም፡፡ ቁርአንን የያዘ አይሸነፍም፡፡ ይህ ኡማ ባለድል እንደሚሆን ይህ ተዓምራዊ ቃል ይነግረናል፡፡

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِن تَنصُرُوا اللَّهَ يَنصُرْكُمْ وَيُثَبِّتْ أَقْدَامَكُمْ

***«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን (ሀይማኖቱን) ብትረዱ ይረዳችኋል፡፡ ጫማዎቻችሁንም ያደላድላል፡፡»*** [9]

ኢስላም የሁሉንም ዘመናት እንቅፋቶች በድል ተወጥቷል፡፡ዛሬም ይወጣዋል፡፡ ነገም እንዲሁ ፡፡ ፈተናዎች ሁሉ አይበግሩትም፡፡ የተከታዮቹ ሞት

---

[9] ሙሀመድ 17

አያጎድለውም፡፡ የጠላቶቹ ብርታት አያሰጋውም፡፡ መሰረታዊ ምንጩ ቁርአን አይደርቅም፡፡ እንደ ጅረት ዘላለም ይፈሳል፡፡ ሁሉንም ያጠጣል፡፡ ዋስትና ከአላህ ተሰጥቶታል፡፡

إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ

***«እኛ ቁርዓንን እኛው አወረድነው እኛው ለርሱ ጠባቂዎች ነን» አል ሂጅር 9***

አምባገነኖች የህሊናዎችን ብስለትና ዕውቀት እጅግ ይፈሩታል፡፡ አይፈልጉትም፡፡ ቁርአን ግን በዚህ ተቃራኒ ሆኖ ነው የወረደው፡፡ ህሊናዎችን በአስተሳሰብ ለማምጠቅ፡፡ ልቦናዎችን በዒባዳ ለማበልፀግ፡፡ ቁርአን መጪውን ጊዜ ሊረከብ አቅሙ ያለው የተስፋ ትውልድን መልምሎ ያዘጋጃል፡፡ ለፍጡራን የተገነባ አዕምሮን ያፈራል፡፡ ከዘረኝነትና ጎሰኝነት የፀዳ አስተሳሰብን ወደ ጎን በመተው አንድነትና መተሳሰብን ግዴታ ያደርጋል፡፡ ጠርዘኝነትና ልዩነትን በማስወገድ መሀከለኝነትንና መግባባትን ይፈጥራል፡፡ አንድነትን ሰብኮ፤ሰዎችን አስተሳስሮ አንድ ህዝብን መቅረፅ ይሻል፡፡

إِنَّ هَذِهِ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَأَنَا رَبُّكُمْ فَاعْبُدُونِ

***«ይህች (ህግጋት) አንዲት መንገድ ስትሆን በእርግጥ ሀይማኖታችሁ ናት እኔም ጌታችሁ ነኝና ተገዙኝ» አል አንቢያዕ-92***

ምስክርነት በአላህ በቃ፡፡ ከህደትና ማጋራት ከአምባገነንነት ጋር ተዳብለው ቢመጡ የኢስላምን ብርሃን ማጥፋት ቀርቶ ሊያደበዝዙት አይሞክሩም፡፡ ይባስ ብሎ ተከታዩን ህዝብ ወደ ዲኑ እንዲመለስ ፤እንዲዋሀድ፤ዲኑን ተባብሮ እንዲጠብቅ መቀስቀሻ ደወል ነው፡፡ ለዚህ ነው ረስቱም የተባለው ገዢ የሙስሊሞች ሰራዊት ድንበራችንን ዘልቆ ገብቷል ምን ሊበቃን ነው ሲባል፤

***«ተዋቸው ወደ ሀገሬ ይግቡ ፤እናንተ ከምትበሉት ይብሉ፤ከምትጠጡት ይጠጡ ከቆነጃጅት ጋር ይቃበጡ፡፡ የዛኔ ነው እነርሱን ማሸነፍ***

***የምትችሉት»***ሲል ለጦር አበጋዞቹና ሹማምንቱ የተናገረው፡፡ ምዕራቡ ዓለም የአባቱን ስትራቴጂ ተከትሎ ኡማውን ቢያስተኛም ግን አሁን ነቅቷል፡፡

ነብዩም(ሰዐወ) ***«ይህ ጉዳይ(ኢስላም) ፀሀይ የደረሰችበት ቦታ ሁሉ ይደርሳል፡፡ »*** ሲሉ የተናገሩት፡፡ ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው ኢስላማዊው ንቃት በደልና ስቃይ ያበረታዋል እንጂ አያደክመውም፡፡

## ሙሐመድ አል-ፋቲህ (1451-1481 ዓ.ል)

መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) በዘመናቸው እንዲህ ማለታቸው ይታወሳል፡- «ኮንስታንቲኖፐል (ቱርክ በኢስላም) ትከፈታለች፣ መሪውና ወታደሮቹ ምንኛ አማሩ፡፡» (ሙስነድ ኢማም አህመድ)

ዕድሜው 22 ዓመት ሲሆን የህዝብ ኃላፊነትን ተሸከመ፡፡ከአባቱ ሞት በኋላ መሪ መሆን ቻለ፡፡ ኃይልንና ፍትህን አመጣጥኖ በመምራት ከሌሎች ልዩ ያደረገው ነበር፡፡ ኮንስታንቲኖፐል ከወቅቱ ከተሞች ልዩ ነበረች፡፡ ቆንስጣንጢን በ330 የተቆረቆረች ሲሆን «ምድር አንድ ግዛት ብትሆን ኮንስታንቲኖፐል ዋና ከተማዋ ትሆን ነበር» እስከመባል ደርሳ ነበር፡፡ ከተመሰረተች ጀምሮ ቤዛንታናውያን መናገሻቸው አድርገዋት ነበር፡፡

ከላይ ያየነው የመልእክተኛውን (ሰዐወ) ትንቢት ለመሙላት ከሙዓዊያ ኢብኑ አቢ ሱፍያን ስልጣን ዘመን ጀምሮ ከ30 በላይ ሙስሊም መሪዎችና ኸሊፋዎች ጥረት አድርገው ነበር፡፡ ነገር ግን ሁሉም አልተሳካላቸውም፡፡

ይህ ወጣት ወደ ስልጣን ከመውጣቱ በፊት ግን አባቱ በአሊሞች እጅ ነበር ያሳደገው፡፡ ኢስላምን ይወዳል፣ቁርአንና የነብዩ(ሰዐወ) ፈለግ ያፈቅራል፡፡ ዕውቀትን ከመውደዱም በላይ ለመስፋፋቱ ጥረት ያደርጋል፡፡ ዑለማዎች ቅርብ ሰዎቹና አማካሪዎቹ ናቸው፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ በምድራዊ ህይወትና ኑሮዋ አለመሸወዳቸው ተፅዕኖን አሳድሮበታል፡፡በተለይ በፋቲህ ህይወትና የትግል ጉዞ ላይ የሸይኽ አቅ ሸምሰዲን ሚና ጉልህ ነበር፡፡ የዑስማናውያንን የትግል ገድል ይተርኩለታል፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ ያ የነብዩ(ሰዐወ) ትንቢት እሱን የሚመለከት እንደሆነ ይነግሩታል፡፡ በዚህ የተነሳ ይህን ሐዲስ ተግባራዊ

ለማድረግ ለሊትና ቀን ይጥር ጀመር፡፡ ይህችን ሀገር በኢስላም ለመክፈት ዝግጅቱን ጀመረ፡፤ ከሩብ ሚሊዮን በላይ ወታደር አሰለጠነ፡፡ ይህ ቁጥር በወቅቱ ብዙ ነበር፡፡ ኦርባን የተባለ ከባድ መሳሪያ (መድፍ) የሚሰራ መሀንዲስ በማስመጣትና የሚያስፈልገውን በማሟላት ማሰራት ቻለ፡፡

የባህር ጦር ኃይሉንም በሚገባ አነጸ፡፡ ከአራት መቶ በላይ የጦር ጀልባዎች ግልጋሎት ላይ እንደዋሉ ተዘግቧል፡፡ ወደ ፍልሚያው ገባ፡፡ አርባ ቀናት ከፈጀ ፍልሚያ በኋላ በ1453 ዓ.ል ኮንስታንቲኖፕል ተከፈተች፡፡ ለነዋሪዎቿና ቤተክርስትያኖቿ ሙሉ ነፃነትና መብትን ሰጠ፡፡ የዚህ ታሪክ አርማና አሻራው በቱርክ ምድር ላይ ቆሞ ይገኛል፡፡[10]

## ከነባራዊ ሁኔታ

ዛሬ ሚዲያው ሁሉ ስለ ኢስላም ሳያወሳ አይውልም፡፡ ምዕራቡና ጣዖታውያኑ ያሴራሉ፡፡ ሴራው ይከሽፋል፡፡ ምክንያቱም ዲኑ የዓለማቱ ጌታ ነውና፡፡

وَمَكَرُواْ وَمَكَرَ اللّهُ وَاللّهُ خَيْرُ الْمَاكِرِينَ

***«(አይሁዶችም) አደሙ አላህም አድማቸውን መለሰባቸው፡፡አላህም ከአድመኞች ሁሉ በላጭ ነው፡፡» ዓለ ዒምራን 54***

የኡማውን ጥንካሬ ለማልፈስፈስ ምዕራቡ ዓለም አንዴ በሽብርተኝነት ሲለው በህይወት መንገድነት በተሰኙ የውሸት ቀለማት የደመቁ ፍልስፍናዎቹን

---

[10] *መሀመድ* አልፋቲህ ፋቲሁል ቆንስጣንጠን ዓሊ ሶላቢ

ለዓለም በመልቀቅ ፤ሙስሊሙን ማሸማቀቅ ፤በራስ መተማመኑን ለመሸርሸርና ሰላሙን ማደፍረስ ይዟል፡፡

በዓለም ላይ አሉ የተባሉ መጥፎ ወህኒ ቤቶች በሙስሊሞች ነው የተሞሉት፡፡ ከባድ የተባሉ የስቃይ መሳሪያዎች (torching materials) የሚሞከሩት በሙስሊም እስረኞች ነው፡፡ ሀገራት ተወረው የሚያልቁት ሙስሊሞች የሚበዙበት ቦታ ነው፡፡ አፍጋን፤ኢራቅ፤ቺቺኒያ፤በርማ፤ፍልስጤም ወዘተ...

ይህ ሁሉ ለምንድን ነው ሲባል ኢስላማዊ ንቃት ተፈጠረ፡፡ ወይም በፈሪዎቹ ምዕራባውያን አገላለፅ አክራሪነት ተወለደ ተብሎ ነው፡፡ ዲኑን የተገበረ ሶላት የሰገደ፤ቁርአን የቀራ፤ዚክር ያደረገ፤ የሴትና ወንድ ህገ-ወጥ መደባለቅን የተቃረነ፤አስካሪ መጠጥን የከለከለ፤ዚናን የኮነነ ሁሉ አክራሪ አሸባሪ ነው፡፡

ይህን ሁሉ ስጋት አልፎ ግን ኢስላም መጪውን ዘመን ይረከባል፡፡ ምክንያቱም ዓለም ዛሬ ላለችበት የድረሱልኝ ጥሪ መፍትሄ ስላለው ነው፡፡ ህግና እሴቶቹ አሳማኝ ከመሆናቸው ጋር ምክንያታዊ (logical) ሳይንሳዊ እና ለአተገባበር ቀላል መሆኑን የሚያውቁት የምዕራቡ ዓለም አሬንታሊስቶች ፤ አምባገነን መሪዎችን እንደ በግ በማስበርገግ ንፁህንን ለእስር፤ግድያና ስቃይ የሚዳርጉት፡፡

ያም ሆነ ይህ ሰዎች ህሊናቸውን እያሰሩ ነው፡፡ ባለጌ የሀይማኖት መሪ ተብዬዎችንና አጥፊዎችን በመተው ወደ ራሱ በመመለስ ማስተንተን ጀምሯል፡ ፡ የህይወት መንገዱን በመመርመርና ማወቅ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ መንገዶች ሁሉ ወደ ኢስላም እያመሩ መሆናቸውን ነው የሚያሳየው፡፡ ሙስሊም ሆኖ አለመሞት እድለ-ቢስነት ነው፡፡

وَوَصَّى بِهَا إِبْرَاهِيمُ بَنِيهِ وَيَعْقُوبُ يَا بَنِيَّ إِنَّ اللّهَ اصْطَفَى لَكُمُ الدِّينَ

فَلاَ تَمُوتُنَّ إَلاَّ وَأَنتُم مُّسْلِمُونَ

*«በርሷም(በሕግጋቱ) ኢብራሂም ልጆቹን አዘዘ ያዕቁብም(እንደዚሁ ልጆቹን አዘዘ) ልጆቼ ሆይ አላህ ለናንት ሀይማኖትን መረጠ ስለዚህ ሙስሊም ሆናችሁ እንጂ አትሙቱ(አላቸው)»*

## ድንቅ የድል ትውልድ

በአላህ መንገድ ላይ ለመታገል የኳተነች እግር ባዶዋን ያለ ውጤት በፍፁም አትመለስም፡፡ እውነተኛ አማኞች እነዚያ ነፍሳቸውን በጀነት የቀየሩ ናቸው፡፡

በጦር ስልትና ይዘት ምጥቀት ያላቸው እጅግ ብዙ ወታደሮችን ጥቂት የእምነት ሰዎች እንዳሸነፏቸው ከዚህ በፊት ለማየት ሞክረናል፡፡

كَم مِّن فِئَةٍ قَلِيلَةٍ غَلَبَتْ فِئَةً كَثِيرَةً بِإِذْنِ اللّهِ وَاللّهُ مَعَ الصَّابِرِينَ

*«...ከጥቂት ጭፍራ በአላህ ፈቃድ ብዙውን ጭፍራ ያሸነፈች ብዙ ናት አላህም ከታጋሾች ጋር ነው ኣሉ፡፡» አል በቀራ 249*

ዛሬ ደግሞ ምዕራቡና የኡማው ቀንደኛ ጠላቶች በጦር መሳሪያ መጥቀዋል፡፡ አቶሚክ ቦምብና የኬሚካል መሳሪያዎች ታንክና ሚሳኤላቸው መጥቋል፡፡

ይህ ሁሉ መቼም ቢሆን መንፈስን ሊረብሽና ሊያሸብር አይችልም፡፡ ምክንያቱም የክህደት አቀንቃኞች በፍርሀት የራዱ ናቸው፡፡ እንደዚህ እንኳ ሆነው በራስ የመተማመን ስሜታቸው የላሸቀ ነው፡፡

እነርሱ ዘመናዊ የሀይድሮጂን ቦንቦችን ተሸክመው በፍልስጤማውያን እጅ የሚወረወር ድንጋይ ያስጋቸዋል፡፡ እነርሱ በታንክና ሚሳኤል ታጅበው ተራ ጋዜጣዊ መግለጫ ያርበደብዳቸዋል፡፡

አዎ ! በማጋራታቸው ምክንያት ፍርሀት ተለቀቀባቸው፡፡ ይህ ነው እንግዲህ የዚህ ትውልድ ዋነኛ መለዮ፡፡ የድል ትውልድ ነው፡፡ ሲዋከ ይዞ ልዕለ-ሀያላንን ያስጋል፡፡ በሀሳብና ጭንቀት ለኪሳራ ይዳርጋቸዋል፡፡ እንጂ በተጨባጭ በገሀዱ ዓለም ሙስሊሞች መቼም አደጋን አድርሰው አያውቁም፡፡

አሜሪካና አጋሮቿ ግን ሙስሊም ሀገራትን በሽብርተኝነት ቀለም አውድመዋል፡ ፡ ልቅ ወታደሮቻቸው ሙስሊም ሴት ልጃገረዶችን አስገድደው ደፍረዋል፡፡ ህፃናትን ያለ ርህራሄ ጥይት ተኩሰው ገድለዋል፡፡ አዛውንትን ያለምንም መሸማቀቅ በሳንጃቸው አጋድመው አርደዋል፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን የዓለማችን ሃያላን ሀገራት መንግስታት ያውቁታል፡፡ የሰው ልጆች እንባ ጠባቂ ተቋም ያውቀዋል፡፡ Human rights watch በደንብ ያያል፡፡

እነዚህ ተልካሻ ድርጅቶች በሙሉ የሚተዳደሩት በአምባገነኖቹ መልካም ፍቃድ ስለሆነ የውሸት ናቸው፡፡ ሙስሊሞች በየወህኒ ቤቱ ተገደው ግብረ-ሶዶም ሲፈፀምባቸው፤ተናካሽ ውሾች ሲለቀቁባቸው፤በኤሌክትሪክ ሲቃጠሉ (electric torch) ሁሉም እያወቀ ዝምታን መርጧል፡፡ ፈተናና ስቃይ ሲበረታ ፤ጭቆናና ግፍ እንዲሁም ግድያ ሲበዛ የአላህ ዕርዳታ መቅረቡን ነው የሚያሳየው፡፡

أَمْ حَسِبْتُمْ أَن تَدْخُلُواْ الْجَنَّةَ وَلَمَّا يَأْتِكُم مَّثَلُ الَّذِينَ خَلَوْاْ مِن قَبْلِكُم مَّسَّتْهُمُ الْبَأْسَاء وَالضَّرَّاء وَزُلْزِلُواْ حَتَّى يَقُولَ الرَّسُولُ وَالَّذِينَ آمَنُواْ مَعَهُ مَتَى نَصْرُ اللّهِ أَلا إِنَّ نَصْرَ اللّهِ قَرِيبٌ

***«በእውነቱ የነዚያ ከበፊታችሁ ያለፉት (ምእመናን መከራ) ብጤ ሳይመጣባችሁ ገነትን ልትገቡ ታስባላችሁን? መልዕክተኛውና እነዚያ ከርሱ ጋር ያመኑት የአላህ እርዳታ መቼ ነው? እስከሚሉ ድረስ መከራና ጉዳት ነካቸቸው ተርበደበዱም ንቁ የአላህ እርዳታ ቅርብ ነው፡፡» አል በቀራ 214***

## ማን ማንን ምን ይቀበል?

የኡማው አርአያ ታላቁ የፍጡራን ዓይነታ ሙሀመዱል-አሚን (ሰዐወ) ናቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በአላህ መንገድ ላይ እልህ አስጨራሽ ትግል አድርገዋል፡፡ በርሱ መንገድ ተርበው፣ተደብድበው፣ደምተውና

ተንቋሸው ድልን ተጎናፅፈው ኢስላምን አቁመው አልፈዋል፡፡ ባልደረቦቻቸው ተተኩ አቡበክር ነብዩ ያስረከቧቸውን ኃላፊነት እኔ በህይወት እያለሁ ኢስላም አይጎድልም ብለው ታግለው ለዑመር አስረከቡት፡፡ ዑመር በጀግንነትና በአላህ ፍራቻ በአዛኝነት መሀል በመሆን ዒራቅ ላይ አንዲት ፈረስ መንገድ ሳይመቻት ቀርቶ እግሯ ቢሰበር አላህ ዘንድ እጠየቃለሁ፤ብለው ኢስላማዊውን ኃላፊነት ጥግ ድረስ በመስራት ለዑስማን ዑስማን ለዓሊ እያለ… ዑመር ኢብን ዐ/አዚዝ ዘንድ ደረሰ፡፡ ሁሉም ለኢስላም ሲሉ እንቅልፍን ከዓይናቸው ላይ እርም አደረጉ፡፡ ዝንጋቴን ከልቦናቸው አወጡ፡፡

ሌት ቀን ሳይሉ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንደደከሙት ታከቱ፡፡የሶሀባ ተከታይ ትውልድ (ታቢዒን) ባንዲራውን ተቀብለው አውለበለቡት፡፡ ሰለፎች ተቀብለው ለእኛ አቀበሉት፡፡ ዛሬ አሊሞች የተቻላቸውን ሁሉ ጥረት እያደረጉ ለወጣቱ ለማቀበል እየተሯሯጡ ነው፡፡

## ወጣቱ ባለ አደራ

አማና በኢስላም ግዙፍ ቦታ አለው፡፡ ለባለቤቱ የመመለስ ግዴታ በተቀባይ ላይ አለ፡፡

إِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُكُمْ أَن تُؤَدُّوا الْأَمَانَاتِ إِلَىٰ أَهْلِهَا

***«አላህ አደራዎችን ወደ ባለቤቶቻቸው እንድታደርሱ ያዛችኋል፡፡»***

መለኮታዊው አደራ ደግሞ በዚህ መልኩ ተገልጧል፡፡

إِنَّا عَرَضْنَا الْأَمَانَةَ عَلَى السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَالْجِبَالِ فَأَبَيْنَ أَن يَحْمِلْنَهَا وَأَشْفَقْنَ مِنْهَا وَحَمَلَهَا الْإِنسَانُ ۖ إِنَّهُ كَانَ ظَلُومًا جَهُولًا

***«እኛ አደራን በሰማያትና በምድር፣ በተራራዎችም ላይ አቀረብናት፡፡ መሸከሟንም እንቢ አሉ፡፡ ከእርሷም ፈሩ፡፡ ሰውም ተሸከማት፡፡ እርሱ በጣም በደለኛ ተሳሳች ነውና፡፡»*** **አል-አህዛብ 72**

በዚህች ሀገራችን ለኢስላምና ተከታዮቹ መከፈል ያለበትን መስዋእትነት መከፈልና ከሌሎች ህዝቦች በታች ሳይሆን የራሳቸው ማንነት ያላቸው፣ ተከባብረው የሚኖሩ፣ የሙብት ጠያቂ ሳይሆኑ እንደሌሎች ሀገራዊ አበርክቶ ያላቸው እንዲሆኑ ማድረግ የሙስሊሙ ወጣት ኃላፊነት ነው፡፡ መልዕክተኛው(ሰዐወ) ***«የምፅዓት ቀን የአንድም ባሪያ እግር አራት ነገሮችን ሳይጠየቅ አይንቀሳቀስም፡፡ ወጣትነቱን በምን እንዳሳለፈው፣ዕድሜውን በምን እንደጨረሰው፣ገንዘቡን ከየት እንዳመጣውና ምን ላይ እንዳዋለው እንዲሁም በእውቀቱ ምን እንደሰራበት፡፡»*** ብለዋል፡፡

ኢስላም በተዋረድ መጥቶ ዛሬ እኛ ጋር ደርሷል፡፡ ከርሱ ሊለያዩንና ሊያፋቱን የሚፈልጉ አካላት ብዙና መሰሪዎች ስለሆኑ ጥንቃቄ በማድረግ አደራችንን ልናደርስ ይገባል፡፡ከርሳቸው ራዕያዊ መድረሳ ስር የፈለቁ ባልደረቦቻቸው ሁሉም ቅኖች ናቸው፡፡ እነርሱን መከተል መቀናት ነው፡፡« ***ባልደረቦቼ እንደ ከዋክብት ናቸው፡፡ የትኛውንም ከተከተላችሁ ተመራችሁ፡፡»*** ማለታቸው ተወስቷል፡፡ በየክፍለ-ዘመኑ ተነስተው ኡማውን በተሰጣቸው ልዩ ተሰጦኦ ሲያገለግሉ ቆይተው ወደ ዘውታሪውና ቆንጆው ዓለም የተሻገሩ ቅኖች ሁሉ ሲተካኩ ነበር፡፡ ዛሬም ያ መተካካት ሊቀጥል ግድ ይላል፡፡

በሀገራችን የነበረው ሁኔታ እንደሚታወቀው በየጊዜው የተነሱ አፄዎች ኢስላምን ለማጥፋት ሲያሴሩ ቆይተዋል፡፡ ይህ ገና ይቀጥላል፡፡ ነገር ግን ያ ሁኔታ የሚፈጠረው ብለው የሚያስቡት ዛሬ ዓለማዊነት፣ አምባገነንነትና ድብቅ ሴራ በኡማው ላይ ተሸርቧል፡፡ ያም

### 1) በአስተሳሰብ ዘመቻ

ኢስላም ኋላ ቀር፣ ከዘመናዊነት ጋር የማይጣጣምና የሰውን ፍላጎት ለማሟላት ፍቃደኛ ያልሆነ ፍኖተ- ህይወት ነው በማለት ተነዝቷል፡፡ በዚህ መንገድ የኢስላም እሴቶች ተዘርፈዋል፤ አሊያም ተዘልፈዋል፡፡

### 2) በመሰረት አልባ ፕሮፓጋንዳዎች

ሴቶች ተበድለዋል፤ ነፃነታቸው ተገፏል፤ ጂሀድና መሰል ኢስላማዊ እሴቶችን ትርጉም አልባ ለማድረግ በማብጠልጠል ብዙ ተብሏል፡፡ ነብዩ ሙሃመድን(ሰዐወ) ለማንቋሸሽ ሞክረዋል፡፡

እና ደግሞ የዲኑን መምህራን፡-

1) በዓለማዊ መጣቀሚያዎች በማታለል
   - ገንዘብና ንዋይን በመለገስ ከሀቀኝነት ወደ ሀሰተኝነት እንዲዘነበሉ ማድረግ፡፡
2) መድረሳዎችንና መርከዞችን መዝጋት
   - የዕውቀት ጅረትን በመገደብና ት/ቤቶችን ወደ ሌላ ተቋምነት በመቀየር፡፡
3) በማሰርና ማሰቃየት
   - የዲን መምህራንን በማሰቃየት፤በማሳደድና ማሰር ወና ማህበረሰብን በመፍጠር፡፡
4) ኢስላማዊ እንቅስቃሴዎችን በእኩይ በመፈረጅ
   - ሁሉንም ተግባራት በአንድ ቀለም በማቅለም ሞራላዊና አካላዊ ጉዳትን ማድረስ፡፡
5) ኡማውን ከሁሉም ዘርፍ በማገት
   - ወደ ተለያዩ መስኮች ሊተም የተዘጋጀውን ኡማ ከሀሳቡ እንዳይደርስ እንቅፋት በመሆን

ምሳሌ፡- ተማሪውን በሂጃብና ሶላት፤ነጋዴውን ከአቅም በላይ ግብርና መሰል ነገሮችን በመጠቀም የሙስሊሙን ማህበረሰብ የማንሰራራት ሞራል፣ የኢስላምን ፈጣን እርምጃ እንገታለን ብለው ያስባሉ፡፡ ተተኪ ያስፈልጋል፡፡ ዓሊሞች ከስራቸው ብዙ እነርሱን ሊተኩ የሚችሉ ወጣቶችን ማስተማር አለባቸው፡፡ ዳዒዎች በችሎታቸው መጠን እና ዓይነት ከስራቸው መሰሎቻቸውን ማፍራት ይኖርባቸዋል፡፡ የታሪክ ምሁራንም እንዲሁ የሚያውቋቸውን ታሪካዊ እውነታዎች (Historical facts) ሊያሳውቁና ሊፅፏቸው ይገባል፡፡ ይህ ነው ቅብብሎሹ፡፡ ዘመንን ይሻገራል፡፡ ትውልድን

ከሩቅ መታደግ ይቻላል፡፡ ለስኬት ያበቃል፡፡ ህልም ሁሉ ቅዠት አይደለም፡፡ ለዚህ ነው ኢማም ሀሰነል-በና « ***የዛሬ እውነታዎች የትናንት ህልሞች ነበሩ፤ የዛሬ ህልሞችም የነገ እውነታዎች ናቸው፡፡»*** ያሉት፡፡ አላህ ቀጥተኛውን መንገድ ይምራን፡፡ የኡማችንን ተጨባጭ ድል በቅርቡ ያሳየን፡፡ የንግግርና አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን የተግባርና ለውጥ ትውልዶች ያድርገን፡፡ አሚን

## የአቋም ፅናት እስከ ዕለተ -ሞት

ስራዎች ሁሉ መጨረሻቸው ነው የሚለካው፡፡ መጨረሻው ያማረ ስራ ፍሬያማ ነው፡፡ በመጀመሪያ በጥሩ መጥቶ መጨረሻን ማበላሸት ከባድ ኪሳራ ነው፡፡ አላህ ይጠብቀን፡፡ ኢስላማዊ ተግባራትን በቋሚነት መስራት የመድህን ድልድይ ነው፡፡

ምክንያቱም በሞት አፋፍ ላይ ያለን ስቃይ ሊያገራ ፤ፍርሀትን አስወጋጅ ፤ ሀዘንን ገርሳሽ ሁኔታዎች የሚገኙት በቋሚነት(በኢስቲቃማ) ነው፡፡

إِنَّ الَّذِينَ قَالُوا رَبُّنَا اللَّهُ ثُمَّ اسْتَقَامُوا تَتَنَزَّلُ عَلَيْهِمُ الْمَلَائِكَةُ أَلَّا تَخَافُوا وَلَا تَحْزَنُوا وَأَبْشِرُوا بِالْجَنَّةِ الَّتِي كُنتُمْ تُوعَدُونَ

***«እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉ ከዚያም ቀጥ ያሉ ኣትፍሩ ኣትዘኑም በዚያችም ተስፋ ቃል ትደረግላችሁ በነበራችሁት ገነት ተበሰሩ በማለት በነሱ ላይ መላዕክት ይወርዳሉ፡፡» ፉሲለት 30***

በትግል መስክ የተሰማራ የኡማው ወጣት ድል እስኪገኝ በችግሮቹ መሀል ሆኖ ሊታገስና በአቋሙ ሊፀና ግድ ይለዋል፡፡ በተስፋ አስቆራጭና እልህ አስጨራሽ ሂደቶች ያልተጓዘበት ትግል ለፍሬ ሲበቃ አልታየም፡፡

أَحَسِبَ النَّاسُ أَن يُتْرَكُوا أَن يَقُولُوا آمَنَّا وَهُمْ لَا يُفْتَنُونَ

*«ሰዎች ኣምነናል በማለታቸው ብቻ እነሱ የሚትተዉ መኾናቸውን ጠረጠሩን?»*

የመንገዱ እርዝመትና አድከምነት መልእክተኞችን እንኳ ተስፋእስከማስቆረጥ አድርሷል፡፡ እህልና ገለባው አንድ አይደለም፡፡ ወርቅ በእሳት ተፈትኖ እንጂ ጌጥ አይሆንም፡፡ውጤት የአላህ እርዳታ (ነስር) ከአቋም ፅናት ነው ሚገኘው፡፡

ለኡማው ደግሞ የፅናት ተምሳሌቶቹ ብዙ ናቸው፡፡ ስጋቸውን በእሳት ፤ ዲንጋይና ዱላ ቢያሰቃዩትም መንፈሳቸው ግን ጠንካራ የነበሩ የኢስላም ፍሬዎችን አሳልፏል፡፡

- ቢላል ኢብኑ ረባህ(ረዐ)
- ኸባብ ኢብኑ አል-አረት(ረዐ)
- ዚኒራ(ረዐ)
- ዘይነበል-ገዛሊ (ረህምቱሏሂ ዓለይሃ) .......ወዘተ

እነኚህ ሁሉ እንግዲህ ግፍን በተለያየ ቀለም አይተውታል፡፡መራር ጣዕሙንም ቀምሰውታል፡፡ መንፈሰ-ብርቱ፤ሞራለ-ጠንካራ ስለነበሩ በአሸናፊነት ተወጡት፡፡

*ፈተና ግድ ነው፡፡ ሁሉም ይፈተናል፡፡በዲኑ በቁርኣኑ፤በዱንያው ሁሉም በየፊናው ይፈተናል፡፡ ፈተናውን የተወጣ ግን ምንኛ አማረለት፡፡*

## ወጣቱና ስነ-ምግባር

ስነ-ምግባር ለምድራዊ ህይወት ጌጥ፤ለአኼራዊው ዓለም ደግሞ ከመልዕክተኛው ቅርብ የመሆንን መልካም ዕድል ይቸራል፡፡ ወጣቱ በስነ-ምግባር እሴቶች የተዋበና በነርሱም ከሰዎች ጋር ብሎም ከግዑዛን አካላት ጋር ያለውን ውሎ ካሳመረ ነገን ለዚህ ኡማ ያስረክባል፡፡ ምድር እስከ ዛሬ ድረስ በላይዋ ላይ ጋጠ-ወጥና አምባገነን መሪዎች ነዋሪዎቿን ገዝተውባታል፡፡ አፈ-ሙዛቸውን ተገን በማድረግ ሰዎችን አዘቅት ከተዋል፡፡ እናም በስነ-ምግባር ዱንያን ያሸበረቀ አገዛዝ ቢኖር ኢስላም ብቻ ነው፡፡

## የስነ-ምግባር ማዕዘናት

በዚህ ስር ደግሞ የስነ-ምግባር ማዕዘናትን ለማየት እንሞክራለን፡፡

## 1) ቸርነት

ሙስሊሙ ወጣት የሰዎችን ልቦና በቀላሉ አሸንፎ ወደ ቀጥተኛው መንገድ የሚመጡበትን ዘዴ መቀየስ ይኖርበታል፡፡ ቸርነት አንዱ የልቦና መከፈቻ ቁልፍ ነው፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በህይወት በኖሩበት ጊዜ ሰዎች እርሳቸው ጋር የነበረን መጣቀሚያ እንደራሳቸው ይቆጥሩት ነበር፡፡ በአንድ ወቅት አንድ የገጠር ሰው ወደ መልዕክተኛው በመምጣት ***« አላህ ከሠጠህ ስጠኝ» አላቸው፡፡*** በአንድ ሸለቆ ውስጥ የነበሩ ፍየሎችን በሙሉ ሰጡት፡፡ ይህ ሰው ወደ ህዝቦቹ በመመለስ ***« እስልምናን ተቀበሉ፤ ሙሀመድ ድህነትን የማይፈራ ዓይነት ሰው አሰጣጥ ነው የሚሰጠው፡፡»*** ሲል ተጣራ፡፡ስለዚህ እኛም ካለን ማንኛውም ምድራዊ መጣቀሚያ ለየቲሞችና ደካሞች ብናካፍል ዳዕዋ ላይ ነን፡፡ ሚሽነሪዎች በገጠሪቱ የሀገራችን ክፍል እያደረሱት ያለውን የአክፍሮት ዘመቻ የረዳቸው የእምነታቸው ይዘት ሳይሆን የገንዘባቸው ብርታትና ቸርነታቸው ብቻ ነው፡፡ የቸርነት ተቃራኒው ስስት ሲሆን መልዕክተኛው (ሰዐወ) ***« ስስትን ተጠንቀቁ ፤ስስት ከናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦችን አጥፍቷል፡፡ »*** ሲሉ አስጠንቅቀዋል፡፡ ቸርነት በገንዘብ ብቻ ተቀስኖ የሚቆም ፅንሰ ሃሳብ አይደለም፡፡ ወጣቱ ለእምነቱ ጊዜውን ጉልበቱንና ገንዘቡንም መሳሳት እንደሌለበት ይጠቁማል፡፡

## 2) ይቅር ባይነት

በደልን ተቋቁሞ ለድል ለመብቃትና ተፅዕኖ አሳዳሪ ለመሆን የፈለገ ሙስሊም ወጣት የበደሉትን ፤ያቆሰሉትን ያስቀየሙትን አካላት ይቅር ይበል፡፡ የዛኔ ልባቸውን ያገኘዋል፡፡ በቀላሉም ያሻውን ምሪት ሊያኖርበት ይመቻል፡፡ አላህ ይቅር ባይ ነው፡፡ ይቅር ባይ ባሪያዎቹን በጣም ይወዳቸዋል፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከመካ አሳደው መዲና ላይ ከ13 ጊዜ በላይ የግድያ ሙከራ ያደረጉባቸውን የመካ ሙሽሪኮች ***« ሂዱ እናንተ ነፃ ሰዎች ናችሁ፡፡»*** ሲሉ

በእንባ አጅበውታል፡፡ በወቅቱ መካን ሲከፍቱ ከ10 ሺ በላይ ጦር አስከትለው ነበር የገቡት፡፡ ነገር ግን መበቀል እየቻሉ መተውን መረጡ፡፡

## 3) ቅንነት

ሀሳብን ቅን ማድረግ፤ተግባርን በቅንነት ማጀብ፤ማንንም ለመጉዳት ሳይሆን ለጋራ መሻሻልና ዕድገት መትጋት፡፡ ምቀኝነትና ቅናትን በማስወገድ የመተባበርና መፈቃቀድ ባህሎችን ማዳበር ቅንነት ይባላል፡፡

ሙስሊም ማለት ሙስሊሞች ከምላሱና ከእጁ ተንኮል የተጠበቁለት ነው ሲሉ ነብያችን(ሰ.ዐ.ወ) አስተምረዋል፡፡ ከስነ-ምግባር ማዕዘናት ውስጥ ቅንነት የልቡን ድርሻ ይይዛል፡፡ ለህዝብ ቅን መሆን ማለት ምኞታቸውን ለራስ ተቸግሮ ማስቀደም ነው፡፡ ለራስ ተርቦ ሰዎችን ማጥገብ፣ሌሎች ያርፉ ዘንድ ለራስ እንቅልፍና እረፍትን ማጣትም ነው፡፡

## 4) ሌሎችን ማክበር

ሰዎች ስንባል መልካችን፤አቋማችንና አስተሳሰባችን የተለያየ ነው፡፡ የዕድሜ ልዩነት ፤የዕውቀት መበላለጥ የኑሮ ደረጃ ከፍ ዝቅ ማለት ወዘተ.... በሙሉ በኛ መሀል ያሉ ሚዛኖች ናቸው፡፡ ኢስላም ለሁሉም የሚገባውን መብት ችሯል፡፡ የዕድሜን ልዩነት በተመለከተ ነብያችን(ሰዐወ) ***« ታላላቆችን የማያከብርና ለታናናሾች የማያዝን ከኛ አይደለም፡፡»*** ብለዋል፡፡

የእውቀትን መበላለጥ አስመልክቶ ቁርአን

يَرْفَعِ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا مِنكُمْ وَالَّذِينَ أُوتُوا الْعِلْمَ دَرَجَاتٍ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ

***«...አላህ ከናንተ እነዚያን ያመኑትንና እነዚያንም እውቀትን የተሰጡትን በ ደረጃዎች ከፍ ያደርጋል፡፡አላህም በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው፡፡» አል ሙጃደላህ 11***

የኑሮ ደረጃን ደግሞ ነብያችን (ሰዐወ) « ***እናንተ ሲሳይ የምትለገሱት በመካከላችሁ ባሉ ደካሞችና ድሆች ነው፡፡*** » ሲሉ አስተምረዋል፡፡ ማጣት ወንጀል አይደለም፡፡ ማግኘት ግን በሁለቱም በኩል ስለት ያለው ቢላዋ ነው፡፡

ሙስሊም ወጣት ሰውን በሰውነቱ ብቻ ሊያልቅ ፤ሙስሊም ወንድሞቹን ከልብ ሊያፈቅር ደካሞችና አዛውንትን መንከባከብ የህይወቱ ውስጥ ቤት ስራዎች ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 5) ሌሎችን ማገልገል

ሙስሊም ወጣት የማህበረሰብ ሁሉን አቀፍ አገልግሎት ሰጪ አካል ነው፡፡ ቁንጮው መልዕክተ-ኢስላምን ማድረስ ነው፡፡ በየመንደሩና ደሳሳ ጎጆ ውስጥ ያለ ጧሪ የቀሩ አዛውንት፤ያለ አሳዳጊ ያሉ ወላጅ አጦችን፤የኢስላም ሰራተኞችን ማገልገል ምንኛ የመንፈስ ደስታን ይቸራል፡፡

## 6) ፍትህ

የሰዎች ድንበር ማለፍና አጥር ጥሰው እኛን መበደል ከፍትሃዊነት በረት ውስጥ እንዳያስወጣን ጥንቃቄ ያሻናል፡፡ እናት፤አባት ጓደኛ ልጅ ሊሆኑ ይችላል፡፡ የፍትህን ሚዛን ማጓደል የለብንም፡፡

ዱንያ ፍትህ ርቧታል፡፡ እንደ ውሀ ጠምቷታል፡፡ ረሃቧን ለማስታገስ ታዲያ ዛሬ ላይ ሙስሊሙ ወጣት ከቤት ጀምሮ እስከ ት/ቤት ባሉ የዕለት ተዕለት ተግባራት ውስጥ ፍትሃዊነትን መላበስ አለበት፡፡ ፍትሀዊ ሁኑ አላህ ፍትሀውያንን ይወዳል፡፡የቁጣንናየሻህዋንጉልበትተቋቁሞነፍስንበጥበብጎዳና የሚያስኬድ ባህሪ ፍትህ ይባላል፡፡ ፍትህ ከልክ ሊያልፍ ወይም ሊያንስ የሚችል ባህሪ አይደለም፡፡ በራሱ ሚዛናዊ ነው፡፡ የርሱ ተቃራኒ ባህሪ በደል ይባላል፡፡ ፍትህ ባህሪን ሚዛናዊ፣ ስነ ምግባርን ልከኛ ያደርጋል፡፡

## 7) እውነተኝነት

ሀሰት ቤት አይገነባም፡፡ ሀገር አያሳድግም፡፡ ስብዕናን ያረክሳል፡፡ ክብርን ያወርዳል፡፡ ባህሪን ያቆሽሻል፡፡ እውነት የልቦና ፀዳል ነች፡፡ አላህ እውነተኛ

ነው፡፡የሀሰት መጨረሻው እሳት ነው፡፡ እወነተኝነት ደግሞ ከጀነት አፀድ ያደርሳል፡፡

## 8) የእውቀት ሐይል

በርሱአማካይነትትክክለኛውንከተሳሳተውይለያል፡፡ጥበብየሚባለውምይህነው፡፡ለከፋ አላማ በመዋል ሲባክን «ኹብስ» ይባላል፡፡ ሲያንስ ደግሞ ቂልነት ነው፡፡ መካከለኛው ጥበብ ይሰኛል፡፡ እውቀት ከፉውን ከደጉ፣ መልካሙን ከመጥፎ ለመለየት ያስችላል፡፡

## 9) ጀግንነት

በአእምሮልጓምየተያዘየቁጣሐይልጀግንነትይባላል፡፡የቁጣጉልበትከልክሲያልፍ ወደ አደጋ መማገድ (ተሐውር)፣ ከልክ ሲያንስ ደግሞ ፍርሃት ይሆናል፡፡ ጀግንነት የክብር ሸማ ያላብሳል፡፡ ከተግባር መልካሙን ለመምረጥ፣ ቁጣን ለመቆጣጠርና ለታጋሽነት ይረዳል፡፡

## 10) ቁጥብነት

የስጋዊስሜትን (ሻህዋን) ጉልበት በአእምሮና በሸሪዓ ልጓም መቆጣጠር ቁጥብነት (ዒፍፋህ) ይባላል፡፡ የሻህዋ ጉልበት ከልክ ሲያልፍ ስግብግብነት፣ ከልክ ሲያንስ ደግሞ ስንፈት ይሆናል፡፡ ቁጥብነት እኩይ ቃልና ተግባር ከመፈጸም ያቅባል፡፡ የበጎ ነገሮች ሁሉ ዓይነታ የሆነውን የይሉኝታ (ሐያእ) ባህሪ ያላብሳል፡፡ ሐያእ ከብልግና፣ ከውሸት፣ ከሐሜትና ነገር ከማሳበቅ የሚታደግ ስነ ምግባር ነው፡፡

## *በማህበራዊ ዘርፍ*

ተግባቢና ሌሎችን የማይከብድ፤ በቀላሉ ከሰዎች የሚናኗር ወጣት መሰሎቹን ለማብዛት የምጡቅ ማህበረሰብ አባላትን ለማበራከት ጥረት ያደርጋል፡፡ ሙስሊም ወጣት  የእምነት ወንድሞቹን ከሚገባው በላይ ለአላህ

ሲል ይወዳል፡፡ እጅግ ያዝንላቸዋል፡፡ ክብራቸውን ይጠብቃል፡፡ ችግራቸውን ለማቃለል ደፋ ቀና ይላል፡፡ ጉድለታቸውን ለመድፈን ጥረት ያደርጋል፡፡ ለዚህ ነው አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን የአማኞችን ሁኔታ ሲገልፅ፡-

مُّحَمَّدٌ رَّسُولُ اللَّهِ ۚ وَالَّذِينَ مَعَهُ أَشِدَّاءُ عَلَى الْكُفَّارِ رُحَمَاءُ بَيْنَهُمْ ۖ تَرَاهُمْ رُكَّعًا سُجَّدًا يَبْتَغُونَ فَضْلًا مِّنَ اللَّهِ وَرِضْوَانًا ۖ سِيمَاهُمْ فِي وُجُوهِهِم مِّنْ أَثَرِ السُّجُودِ ۚ ذَٰلِكَ مَثَلُهُمْ فِي التَّوْرَاةِ ۚ وَمَثَلُهُمْ فِي الْإِنجِيلِ كَزَرْعٍ أَخْرَجَ شَطْأَهُ فَآزَرَهُ فَاسْتَغْلَظَ فَاسْتَوَىٰ عَلَىٰ سُوقِهِ يُعْجِبُ الزُّرَّاعَ لِيَغِيظَ بِهِمُ الْكُفَّارَ ۗ وَعَدَ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ مِنْهُم مَّغْفِرَةً وَأَجْرًا عَظِيمًا [٤٨:٢٩]

*«የአላህ መልክተኛ ሙሐመድ እነዚያም ከእርሱ ጋር ያሉት (ወዳጆቹ) በከሓዲዎቹ ላይ ብርቱዎች በመካከላቸው አዛኞች ናቸው፡፡ አጎንባሾች፣ ሰጋጆች ኾነው ታያቸዋለህ፡፡ ከአላህ ችሮታንና ውዴታን ይፈልጋሉ፡፡ ምልክታቸው ከስግደታቸው ፈለግ ስትኾን በፊቶቻቸው ላይ ናት፡፡ ይህ በተውራት (የተነገረው) ጠባያቸው ነው፡፡ በኢንጂልም ውስጥ ምሳሌያቸው ቀንዘሉን እንደአወጣ አዝመራና፣ (ቀንዘሉ) እንዳበረታው፣ እንደወፈረምና፣ ገበሬዎቹን የሚያስደንቅ ኾኖ በአገዳዎቹ ላይ ተስተካከሎ እንደ ቆመ (አዝመራ) ነው፡፡ (ያበረታቸውና ያበዛቸው) ከሓዲዎችን በእነርሱ ሊያስቆጭ ነው፡፡ አላህም እነዚያን ያመኑትንና ከእነርሱ በጎዎችን የሠሩትን ምሕረትንና ታላቅ ምንዳን ተስፋ አድርጎላቸዋል፡፡»*[11]

---

[11] *አል-ፈትህ 28*

ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችን ያከብራል፡፡ ሀይማኖታቸውን አያንቋሽሽም፡፡ መንገዳቸውን በግድ ይቀይሩ ዘንድ ሀይል አይጠቀምም፡፡ ኢስላምን ግን በጥበብ ለማስተማር ጥረት ያደርጋል፡፡ ሀሰትን ከእውነታ የሚለዩ ድንበሮችን ይፋ ያወጣል፡፡ ምሪትና ቅናቻን ለቀልብ ባለቤቱ ይተዋል፡፡
በመከባበር መንፈስ አብሮ ይኗኗራል፡፡

لَّا يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ لَمْ يُقَاتِلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُم مِّن دِيَارِكُمْ أَن تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوا إِلَيْهِمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ [٦٠:٨]

***«ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደእነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፡፡ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና፡፡»አል-ሙምተሂናህ፤8***

ማህበረሰቡ ውስጥ የሰናይ ተምሳሌት ነው፡፡ ሙስሊም ወጣት ሴቶችን ያከብራል፤ አዛውንትና የዕድሜ ባለፀጋዎችን ያልቃል፤ ለታናናሾቹ ያዝናል፡፡ ለዚህ ነው ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ***«ታላላቆቻችንን ያላከበረና ለታናናሾቻችን ያላዘነ ከኛ አይደለም፡፡»*** ያሉት፡፡
ሙስሊም ወጣት የአላህ ዲን ሲደፈርና ሲዋረድ ማየት እንደሚያንገሸግሸው ሁሉ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ወላጅ አጦችን፣ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶችን በምን መልኩ ደስታ ያገኛሉ ብሎ ጥናትም ይሰራል፡፡ ሙስሊም ወጣት ማህበረሰቡን ከአስተሳሰብ ወረራ ለመከላከል ሁሌም ማስተማር ተግባሩ ነው፡፡ በዕውቀትና ተግባር የዳበሩ ስብዕናዎችን በመቅረፅ ስለሚጠመድ እንቅልፉ ውስን ነው፡፡
የዛን ዕንቁ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ሁኔታ በማስታወስ ሁሌም ለኡማው ይጨነቃል፡፡ ***«የሙስሊሞች ጉዳይ ያላሳሰበው ከኛ አይደለም»*** የምትለው ሀዲስ ለርሱ ከጥልቅ ዝንጋቴ መውጫ ዳሉ ናት፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህዝባቸውን ከመሀይምነትና እንስሳዊነት ጥቁር ጭቃ ውስጥ መንጥቆ ለማውጣት ብዙ

ደክሚል፡፡ ይህን ያስተውላል፡፡ ህዝቤ ብለው ጠዋት ማታ ያለቅሱ ነበር፡፡ ድካምና ጉዳት እያለባቸው ከምንም ሳያዩት ማህበረሰቡን ገንብተው አልፈዋል፡፡ አማኝ ወጣት

*ለቅርብ ዘመዶቹ*

- መልካም ይውላል፤ያዝንላቸዋል፡፡
- የሚያስከፋቸውንና የሚያስቀይማቸውን ተግባርና ንግግር ይርቃል፡፡

*ለየቲሞች*

- ለንብረታቸው ጋሻ ነው፡፡
- ለመብቶቻቸው ተሟጋች ነው፡፡
- ተርቢያና አደብን ያስተምራቸዋል፡፡
- ተንኮላቸውንና ጥፋታቸውን ይታገሳል፡፡
- ፊታቸውን ይዳብሳል፤ራሳቸውን ያሻሻል፡፡

*ለሚስኪኖች*

- በምግብ ረሀባቸውን ያስታግሳል፡፡
- በልብስ ሀፍረተ-ገላቸውን ይሸፍናል፡፡
- ሌሎች መብቶቻቸውን ይጠብቁ ዘንድ ያነሳሳል፡፡

*ለመንገደኛ*

- ጉዳዩን ይሞላለታል፡፡
- ጉዳቱን ይጠግንለታል፡፡
- ንብረቱን ይጠብቅለታል፡፡
- ክብሩን በአግባቡ ይይዝለታል፡፡
- መንገድ ከሳተ ያመላክተዋል፡፡
- ስህተት ላይ ሲወድቅ ይመክረዋል፡፡

*ለሰራተኛ*

- ላቡ ሳይደርቅ በፊት ዋጋውን ይከፍላል፡፡
- ከአቅሙ በላይ እንዲሰራ አያስገድደውም፡፡
- ክብሩን ይጠብቅለታል፡፡

- ከሚበላው ያበላዋል፤ከሚለብሰው ያለብሰዋል፡፡

*ለአጠቃላይ ሰዎች*

- በንግግሩ አያስከፋም፡፡
- በመልካም ያዛል፤ከመጥፎ ይከለክላል፡፡
- መንገድ ለሳቱ ምሪትን ያመላክታል፡፡
- ለማያውቁ ያስተምራል፡፡
- ተንኮሉን ይይዛል፡፡
- ከእኩይ ምግባራት ራሱን ያቅባል፡፡

*ለእንስሳት*

- ሲራቡ ያበላቸዋል፤ሲታመሙ ያሳክማቸዋል፡፡
- የማይችሉትን አያሸክምም፡፡
- ሲሰራባቸው ያዝንላቸዋል፡፡
- ሲደክሙ ያሳርፋቸዋል፡፡

## *በትምህርት ዘርፍ*

*ዕውቀትን መፈለግ ግዴታ ነው፡፡ ሙስሊም በየትኛውም ሁኔታው ከዕውቀት ገበታ መራቅ የለበትም፡፡ በወጣትነት የተያዘ ዕውቀት የተቋጠረ ዘላለማዊ ስንቅ ነው፡፡ ነገር ግን ወጣትነት በአግባቡ በኢስላማዊው መንገድ ላለመጠቀም ከሚያቅቡ ነጥቦች አንዱ መሀይምነት ነው፡፡ የመሀይምነት በሽታ በቀላሉ በመማር ሊድን ይችላል፡፡ መማርና ዕውቀትን ቻይና ድረስ እንኳ ቢሆን ሄደን መፈለግ እንዳለብን የኢስላሙ ዓለማቀፍ ነብይ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) አስረድተውናል፡፡ አለማወቅ ማለት አለማወቅን አለማወቅ ብቻ ነው፡፡ አለማወቅን አውቆ ለማወቅ መነሳሳት የዕውቀት አንዱ ክፍል ነው፡፡ መፅሀፍትን በሚገባ ማንበብ ገለፃዎችን መስማት ተሞክሮዎችን ማየት ከዕውቀት ባህር ውስጥ ያስዋኛል፡፡*

*ወጣቱ ከአዋቂዎች እግር ስር በመቀመጥ እውቀታቸውን መቅሰም ይኖርበታል፡፡ የሚያስፈራውን ወደጎን ትቶ ፣ጥቅሙን ተረድቶና ለመጪ ጊዜ በቂ ዝግጅት ኖሮት ይወጣል፡፡*

የዛኔ የኢስላምን ባንዲራ ማውለብለብ ይችላል፡፡ብቁና ለኢስላም ስርጭት የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ በነገራችን ላይ ግን ትልቅ ጥንቃቄ የሚሰጠው ጥራት ያላቸውን አስተማሪና አዋቂዎች መምረጡ ላይ ነው፡፡እነዚህ መምህሮች ጠንካራ ስነ-ምግባርን በመገንባቱ ረገድ የዳበሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በእምነት የፈረጠሙ፣ በተግባር የታጀቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ምክንያቱም ትምህርትን በመስጠት ላይ የሚገኙ ስብዕናዎች አዲስ ትውልድን በመቅረፅ ላይ ስለሆኑ ነው፡፡

ሙስሊም ወጣት ቀለም ነው፡፡ በትምህርት ዓለም ጥግ ድረስ ይሄዳል፡፡ ዕውቀትን ከመሰብሰብና ከመጨመር አይቦዝንም፡፡ አንባቢና ሰቃይ ነው፡፡ የታሪክ ምንጣፎቹ እንደሚያሳዩት እነ ሒሳብ፣ ፊዚክስ፣ኬሚስትሪ ባዩሎጂና ሌሎች ስነ-ፈለክና ጅግራፊ የመሳሰሉትን የትምህርት ዘርፎች ሙስሊሞች ናቸው የጀመሯቸው፡፡ ለዘመናዊ ትምህርት ጉጉት ያለው ማህበረሰብ መፍጠር የሙስሊም ወጣቶች ኃላፊነት ነው፡፡ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ሙስሊም ዶክተሮችና መሀንዲሶች ተመራማሪዎችና ተንታኞች ያስፈልጉታል፡፡ ለዚህም ታዲያ...ዕውቀትን መፈለግ በያንዳንዱ ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው፡፡ ሲሉ መልዕክተኛው አስታውሰውናል፡፡ ሙስሊም ሐገራት ከተማረ ኃይል መራቆታቸው የሌሎች ምርት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስገድዷቸዋል፡፡ ከቁስ በዘለለ አስተሳሰባቸውን ተቀብለዋል፡፡ ኢስላማዊውን ባህል አስወርረዋል፡፡ የወጣቱንና የታዳጊውን ትውልድ አዕምሮ በርካሽ ሸጠውላቸዋል፡፡

ሙስሊሙ ወጣት ቤተ- መፅሀፍትንና ቤተ-ሙከራዎችን በእጅጉ ተቆራኝቶ አዲስ የምርምር ውጤቶችን ይፋ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ሀቅን አንግባ በእውነት የምትመራ ምድርን ሊገነቡ የሚችሉት ምድራዊ የአላህ ልዑካንና ምትኮች ብቻ ናቸው፡፡የነፃ አስተሳሰብ ፣ ነፃነትና ምክክር፤ መቻቻል የሚባሉት እሴቶች ሊዳብሩ የሚችሉት በማህበረሰብ ሳይንስ ብቁና ታታሪ ሙስሊም ወጣቶች ሲበዙ ብቻ ነው፡፡ ልማትና ዲሞክራሲ፣ የዜጎች ሰላም በዚህ መልኩ ይመጣል፡፡

## *በኢኮኖሚው ዘርፍ*

ጠንካራ ፋይናንስ ለውጥና መሻሻል፤ ወደፊት መራመድ ዕድገትና ጣራ መንካትን ኢስላም አይጣረስም፡፡ሙስሊም ወጣት በህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ በሌሎች ላይ ጥገኝነትን ይጠላል፡፡ (Self handed Personality) ራሱን የቻለ ስብዕና ይወጣው ዘንድ ስራውን በትጋት ይፈፅማል፡፡ አስፈልጎቶቹን ለማሟላት ቤተሰቡን ለመርዳት ይለፋል፡፡

ወጣቱ ሙስሊም እንደነ ዓብዱራህማን ኢብኑ ዐውፍ ፣ ዑስማን ኢብኑ ዓፋን እና መሰል የመልዕክተኛው ባልደረቦች የስራና ገንዘብ ሰው (Business Man) መሆን አለበት፡፡ የሌሎች ተረጣቢና እጅ ጠባቂ ከመሆን ራሱን በስራ መወጠር ብሎም አምራች መሆን አለበት፡፡ ይህ ሲሆን በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ወጣቶች ሲተገብሩት ራሱን የቻለ ለሌሎች የሚጠቅም የተመጣጣኝ ኢኮኖሚ ባለቤት ሙስሊም ኡማ ይኖራል ማለት ነው፡፡ ይህ ካልሆነና የስራ ዕድሎች ተመቻችተው ሁሉም ወጣት ስራ ላይ ካልተሰማራ አደጋው የከፋ ይሆናል፡፡

ድህነት በኢስላም የተወገዘ ነው፡፡ ነገር ግን ወንጀል አይደለም፡፡ ሀብት ግን ሁለት ጎኑ ስለት ያለው ሰይፍ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የመልካም ሰውን ገንዘብ ምንኛ ያማረ ሲሉ አድናቆትን ችረዋታል፡፡ በተቃራኒው እኩይ ሰዎች ጋር ያለ ሀብት ደግሞ ጎጂ ነው፡፡ ኢስላም ከካፒታሊዝም ኮሚኒዝም እና ሶሻሊዝም በተለየ መልኩ ሚዛናዊ የሆነ የግል ባለይዞታነትን ያፀድቃል ማለት ነው፡፡ ያለፈው የመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ሀዲስ የሚያሳየንይህን ነው ፡፡

ወጣቱ ሙስሊም ከወለድ እና ርዝራዦቹ በመራቅ በሀላል ከስብ ብቻ ፋብሪካዎችና ግዙፍ እንዱስትሪዎችን የመገንባት ሰማይ ጠቀስ ህልም ብቻ ሳይሆን መሬት የያዘ ተግባር ሊኖረው ይገባል፡፡ ድሆችና ወላጅ አጦች ደካሞችና አዛውንቶችን ይረዳበታል፡፡ መስጂዶችና መድረሳዎችን ይገነባበታል፡፡ ውሀ ያስቆፍርበታል፣ መንገድ ያሰራበታል፡፡ የኢስላማዊ ዳዕዋ ደጀን ይሆንበታል፡፡ ይህ ሁሉ ሊሆን የሚችለው ግን ተንቀሳቅሶ በመስራትና ፍሬያማ በመሆን ብቻ ነው፡፡

ከማጭበርበር፣ መዝረፍና ቅሚያ ያልመጣ ገንዘብ ምንኛ ይጣፍጣል፡፡ ሀራም ነገሮችን መነገድ ለምሳሌ ኸምር ምን ያህል ህዝባዊ ፍላጎቱ ያየለ ቢሆንም ክልክል ነው፡፡

ወጣቱ አባካኝነትን መራቅ አለበት፡፡ ንፉግነትን ከልቦናው ማውጣትም እንዲሁ፡፡ በዚህ መሀል ግን ሚዛናዊነት ትልቁ ቁም ነገር ነው፡፡ የዲናችንና ህዝባችን መለያ መቅኒ ባህሪ ሚዛናዊነት (ወሰጥያ) ብቻ ነው፡፡ሌላው ደግሞ ሙያተኝነት ነው፡፡ ኢስላም እጅግ ያበረታታዋል፡፡ የነብያትን ተምሳሌትነት በማቅረብም ጉዳዩን ያጠናከረዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል

- ኑህ (ዐ.ሰ) ጀልባን የገነቡ ሜካኒካል መሃንዲስ ነበሩ፡፡
- ኢብራሂምና ኢስማኤል (ዐ.ሰ) ካዕባን የገነቡ ግንበኞችም ሲቪል ኢንጂነሮችም ነበሩ፡፡
- ዳውድ (ዐ.ሰ) በብረት ስራ (metallurgy) ላይ ባለሙያ ነበሩ፡፡ ኢስላም ልመናን ከጥቂት አሳማኝ ምክንያቶች ውጪ አጥብቆ ኮንኖታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከልመና ይልቅ አንድ ሰው ገመድ ይዞ ተራራ ላይ በመሄድ እንጨት ሰብሮ በጀርባው ተሸክሞ ሸጦ የላቡን መመገቡ ከሰዎች የፊት ግርፊያ ይሻለዋል ብለዋል፡፡ ኢስላም ስራ ፈትነትና ስንፍና ላይ ጦርነት አውጇል፡፡ ወጣቱ ሙስሊም ኢስላም የሰጠውን የመስራት የማደግና ማበረታታት ዕድል በመጠቀም ራሱን መለወጥ ይጠበቅበታል፡፡ ስራን መስራት በድህውና ባለፀጋው መሀል ያሉ ክፍተቶችን ለማጥበብ ይረዳል፡፡

# 3

# በትግል ሜዳ ውስጥ

***“ባሪያዎችን ባሪያ ከማምለክ ወደ አንዱና ብቸኛው አላህ አምልኮ እናወጣ፤ ከዱንያ ጥበት ወደ ሰፊቷ፣ ከሀይማኖቶች በደል ወደ ኢስላም ፍትህ እናወጣ ዘንድ አላህ ልኮናል፡፡”***

ረቢዕ ኢብኑ ዓሚር በቃድሲያ ዘመቻ እለት ረስቱም ለተባለው ገዢ የተናገረውን ነበር ከላይ ያየነው፡፡ ኢስላም ራሱን ለማስፋት ይቅርታን ጠያቂ አይደለም፡፡ ልምጥምጥና ሰነፍ፤ ደካማና ራስ በል ሳይሆን በየክ/ዘመናቱ በተደጋጋሚያጋጠሙትን እንቅፋቶች በሙሉ በድል አድራጊነት ተወጥቷል፡፡ ኢስላም ሰዎች በነፃነት ይኖሩ ዘንድ በአላህ መንገድ መታገልን አንዱ ዘዴ አድርጎታል፡፡ ለዚህ ነው በቃዲሲያ ዘመቻ ጊዜ ረቢዕ ኢብኑ ዓሚር ለረስቱም ለምን ከሀገራችሁ ወጣችሁ፣ ወደኛስ ዘመታችሁ ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ ከላይ ያየነውን የመለሰው፡፡ አዎ! ኢስላማዊው ድል በቅርቡ ነው፡፡ ወጣቱ ሳይቸኩልና ተስፋ ሳይቆርጥ፤ ወደ ኋላ ሳያፈገፍግ መታገል አለበት፡፡ ድል ማጎናፀፍ፣ እርዳታን መለገሱ የጀሊሉ ፋንታ ነው።

አላህን የፈሩት፣ የእርሱን ልቅና የተረዱት ምድራዊ የርሱ ምትክ(ኸሊፋ) መሆናቸውን የተገነዘቡ ታጋይ የአላህ ወታደሮች ተስፋቸው የነገ ኢስላማዊ ሰንደቅ መውለብለብ ነው፡፡

በተለይ ሙስሊሙ ወጣት ነስር(የአላህ ግዙፍና ሁለንተናዊ ዕርዳታ) ከትግል በኋላ መሆኑን ከቅዱስ ቁርአንና ነብያዊ ሀዲስ ይረዳዋል፡፡

በዓለም ዙሪያ የኢስላማዊ መነቃቃት ለምዕራቡና ለዲኑ ጠላቶች ምንም ያህል የእግር እሳት ሆኖባቸው እንቅፋቱ ለመሆን ቢጥሩም እንኳ እያሸነፋቸው ነው፡፡ፍልስጤማውያን፤አፍጋናውያን በየቀኑ የቦምብ እራት የሚሆኑት ምንም አይነት ወንጀል ፈፅመው አይደለም፡፡ የሰው ሀገር ወረው፤የሰዎችን መብት ጥሰው አይደለም፡፡ ወንጀላቸው ሙስሊሞች ስለሆኑ ፤ራሳቸውን ለአላህ

ያሳደሩ ስለሆኑ ብቻ ነው፡፡ ይህን እውነታ ሁሉም ያውቀዋል፡፡ ሙስሊሙ ዓለም ምዕራቡን ዓለም አይነኬ ሀይል አድርጎ በመሳል፤ ለወገኖቹ ደም ጥብቅና መቆም አይደለም  በልሳኑ እንኳ እንዳይናገር አድርጎታል፡፡ ሙስሊሞች በዲናቸው የተነሳ ብቻ በየእስር ቤቱ ታጉረዋል፡፡ በየሀገሩ ተሰደዋል፡፡ በረሀብና ጥም ህይወታቸውን እንዲያጡ ተደርገዋል፡፡ በየማሰቃያ ቦታዎች አረመኔያዊ ተግባራት ተፈፅሞባቸዋል፡፡ ስንት ሙስሊሞች በውስጡ በኤሌክትሪክ ቶርች እንደተደረጉ፤የኢስላም ልጆች ስጋቸው በቢላ እንደተተለተለ፤ስንት የኢስላም ልጆች በስልጡን ውሾች እንደተነከሱና እንደተበሉ፤ስንት የኢስላም ልጆች በተሰባበረ መስታወት ላይ ባዶ እግራቸውን እንዲሄዱ እንደተገደዱ፤ የአላህ ባሪያዎች ጨለማ ቤት ውስጥ ወራትን እንዳሳለፉና አይናቸው ከአገልግሎት ውጭ እንደሆነ፤.......ጓንታናሞ ይመስክር፡፡ ታዲያ ይህን ሁሉ በደል የዓለማቱ ጌታ ዝም ይላልን ? ድሉ ቅርብ ነው አዋጅ ! የአላህ ወታደሮች ሆይ ! ፅኑ

## ዳዕዋን በጥበብ

ሙስሊም ወጣት ከተሻለ ግንዛቤና ዕውቀት በኋላ ጥበብን በመጠቀም በዳዕዋው ኡማውን ይደርሳል፡፡ ወደ ኢስላም ጥሪ ማድረግ የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ህዝብ መለያ ካባ ነው፡፡ እጅግ ያስመነዳል፡፡ ሙስሊም ላልሆኑም  ይሁን ሙስሊም ወገኖች ጥበብን  ያማከለ ጥሪ ስኬትን ያጎናፅፋል፡፡

ኢስላም ያልደረሰባቸው ቦታዎች አሉ፡፡ እነዚህ ስፍራዎች የሙስሊሙን ወጣት ልፋት ይሻሉ፡፡ በአላህ መንገድ ላይ የመታገል አንዱ ዘርፍ ነው፡፡ ኃላፊነቴና ግዴታዬ ብሎ ወጣቱ ሊዘምት ይገባል፡፡

*“አላህ በአንተ ሰበብ አንድን ሰው ወደ ቅኑ መንገድ ቢመራልህ ከቀያይ ግመሎች ይበልጥልሀል፡፡” (ሙስሊም)*

ኡማው የወጣቱን የብዕር ቀለም የአዕምሮ ውጤት ይጠብቃል፡፡ ኢስላም ከተፈጥሮ ጋር ሳይጣረስ ቀስ ብሎና ምቹ ሆኖ ሰዎችን እየማረከ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ለዓለማት የመጣ መልእክት ላልደረሳቸው ማድረስ እያንዳንዱ

አማኝ ላይ ግዴታ ቢሆንም ወጣቱ ላይ ግን ሀላፊነቱ ይጠነክራል፡፡ ዳዕዋን በተመለከተ ከወጣቱ ግዴታዎች መሀል፡-

## ማድረስ

ዘር፤ቀለም፤ እና የኑሮ ደረጃን ሳይለይ ለሁሉም የሰው ዘር የኢስላምን ድንበሮች፤ህግጋትና ውበት ያለምንም ማጓደልና መጨማመር ያለምንም ማለባበስና ማጣመም ማመላከት ነው፡፡ ይህን ሀላፊነት ወጣቱ ከተወጣ ሁሉም አካል ኢስላም የሚፈልግበትን ሁሉ ይወጣል፡፡ በስራ ይጠመዳል፡፡ ለተሻለ ደረጃም ይደርሳል፡፡

## መመሪያን አጥብቆ መያዝ

ከበስተፊቱም ይሁን ከኋላው ጥሜት የማይመጣበትን ቁርአንን የመጀመሪያ መረጃ ማድረግ፡፡ ንፁሁን የረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) ሱናም ማስከተል፡፡ የሰለፎችን ተሞክሮና ታሪክ ማወቅ፡፡ ከዚህ ባሻገር ሌላውን መተው ያሻል፡፡ ጠማማና እርባና-ቢስ ፍልስፍናዎችን መራቅ ምጡቅነት ነው፡፡ የሰው ልጅ ቀጥተኛውን መንገድ ይመራ ዘንድ ነው የኢስላም ፍላጎት፡፡

## ግብንና መዳረሻን ማስመር

ኢስላማዊ የሆነውን አስተሳሰብ ለማስፋትና የሁሉም ሀብት ለማድረግ መታገል ከእንቅልፍ ተነስቶ ድንገት የሚፈጸም ጊዜያዊ ሩጫ ሳይሆን ግብ የታለመለት ፤ መዳረሻ የተሰመረለት ረዘም ያለ ሂደት ነው፡፡

ኢስላም ለተከታዮቹና ሠራተኞቹ ያስቀመጠው ግብ በክብርና ነፃነት መኖር አሊያም ደግሞ የክብር ሞትን መጎናፀፍ ነው፡አላህ ግባችን፤ መልዕክተኛው(ሰ.ዐ.ወ) አርአያና ተናፋቂያችን፤ ቁርአን ደግሞ መመሪያችን፤ ትግል መንገዳችን በአላህ መንገድ ላይ መሞት ፍላጎታችን ነው፡፡

በአጠቃላይ ወጣቱ እምነቱን በማደስ ፤ ግብና መንገዱን በማስመር ለዲኑ ዘብ ይቆማል፡፡ የእምነት ብርታት አንድነትን የአንድነትን ፍሬ ደግሞ የአላህ እርዳታ (ነስር) ነው፡፡

- የእምነት ብርታት
- አንድነትና ወንድማማችነት ተግባር
- የአላህ እርዳታ

ዓለም በከባድ ነውጥ ውስጥ ናት፡፡ ካለችበት ውጥንቅጥ ያሉት ዓለማዊ ስርዓቶች ሊያወጧት አልቻሉም፤ለወደፊቱም አይችሉም፡፡ ለዚህ ጉዳትና ውድቀቷ ደግሞ ከኢስላም ውጭ አማራጭ የላትም፡፡ ወጣቱ በአላህ ስም ወደ ስራው በማግባት ሊያድናት ይገባል፡፡

በባህሪው ኢስላማዊው ጥሪ ሁሉን አቀፍና የምድርን አድማስ ያዳረሰ ነው፡፡ ምድር ያላስቸገሯት አምባገነኖች መድሃኒት ነው፡፡ ይህ ደግሞ

ከንጹህ ልቦና 🕮 ኢማን

ከብሩህ ዕይታ 🕮 ኢኽላስ ሲገኙ ነው፡፡

ወጣቱ በረኸሙ በማስብና ነገን በማዳመጥ ብዙ በመስራት ለኡማው ሙሉ መብቱን ሲሰጥ ያኔ ህልማችን ይሳካል፡፡

የጥሪያችን እርስ በርስ መጠላለፍ ፣የጩኸትና ማበራገግ መብዛት፣የአስተሳሰብ መስመሮች መጣረስና የሁኔታዎች መጨናነቅና መሰል እንቅፋቶች መብዛት በምንም መልኩ ወደ ግባችን ሳንደርስ ሊጠልፉን አይገባም፡፡

# ወጣቶች ነበሩ

## ኢብራሂም (ዐ.ሰ)

ህዝባቸው ጣዖት አምላኪ ስለሆነ በልባቸው ቢኮንኑትም በተግባርና ንግግራቸው ግን በጥበብ ከባድ ትግል አደረጉ፡፡ይህ ሰው ተውሂድን

ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃ ለማውጣት የታገሉ ወጣት ለርሱም ሲሉ ወደ እሳት የተወረወሩ ወጣት ነበሩ፡፡ ልዩ የአላህ ወዳጅ የቁርጥ ቀን ወጣት፤ የእውነት ደጀን፤የሀሰት ጠላትና ተዋጊ ነበሩ፡፡ ህዝባቸውንና አባታቸውን እንዲህ ብለው ነበር ስለ አምልኮአቸው የጠየቁት፡፡

مَا هَذِهِ التَّمَاثِيلُ الَّتِي أَنتُمْ لَهَا عَاكِفُونَ

*"እነዚህን በዙሪያቸው ተቀምጣችሁ የምታመልኳቸው ምስሎች ምንድን ናቸው፡፡"* አል አንቢያ 52

እነርሱም <<አባቶቻችን ሲያመልኳቸው አገኘን፡፡ እኛም አመለክናቸው፡፡» ሲሉ መለሱ፡፡

قَالَ لَقَدْ كُنتُمْ أَنتُمْ وَآبَاؤُكُمْ فِي ضَلَالٍ مُّبِينٍ

*«እናንተም አባቶቻችሁም በእርግጥ ግልፅ በሆነ ጥመት ውስጥ ናችሁ፡፡»* አንቢያ 53

የተውሂድን መልዕክት አንቀበልም አሏቸው፡፡ ይባስ አስፈራሯቸው፤ ኢብራሂም ቆራጥ አቋማቸውን ተናገሩ፡፡

وَتَاللَّهِ لَأَكِيدَنَّ أَصْنَامَكُم بَعْدَ أَن تُوَلُّوا مُدْبِرِينَ

*«በአላህ ይሁንብኝ እናንተ ስትሄዱ ጣዖቶቻችሁ ላይ ደባ ፈፅምባቸዋለሁ፡፡»* አንቢያ 57

ኢብራሂም በወሬ ብቻ አልቀሩም፡፡ የተናገሩትን ቃል በገቢር አስገኙት፡፡ እንዳሉትም

فَجَعَلَهُمْ جُذَاذًا إِلَّا كَبِيرًا لَّهُمْ لَعَلَّهُمْ إِلَيْهِ يَرْجِعُونَ

*«ሁሉን ጣዖታት ሰባበራቸው፡፡ ትልቁ ሲቀር እሱንስ አምላኪዎቹ ወደርሱ ይመለሱ ዘንድ ተወው፡፡»* አንቢያ 58

ህዝቡ ከክብረ በዓሉ ሲመለስ ጣዖታቱ እንዳልነበሩ ሆነው አገኙ፡፡ እርስ በርስ ማን እንደሰበረ ተጠያየቁ፡፡

قَالُوا مَن فَعَلَ هَذَا بِآلِهَتِنَا إِنَّهُ لَمِنَ الظَّالِمِينَ

*«ማን ነው በአምላኮቻችን ላይ ይህን የፈፀመው ተባባሉ፡፡»* አንቢያ 59

ከነርሱ ውስጥ ከፊሉ ሰው ኢብራሂም የሚባለው ወጣት በክፉ ሲያወሳቸው ነበር ሲሉ መሰከሩ፡፡

قَالُوا سَمِعْنَا فَتًى يَذْكُرُهُمْ يُقَالُ لَهُ إِبْرَاهِيمُ

*«ኢብራሂም የሚባል ወጣት በክፉ ሲያወሳቸው ሰምተናል አሉ፡፡»* አንቢያ 60

ወጣቱ ኢብራሂም(ዐሰ) ሸንጎ ቀረቡ፡፡ ተጠየቁም

قَالُوا أَأَنتَ فَعَلْتَ هَذَا بِآلِهَتِنَا يَا إِبْرَاهِيمُ

*«በአምላኮቻችን ላይ ይህን የፈፀምከው አንተ ነህን አሉት፡፡»* አንቢያ 62

ኢብራሂም ይህቺን አጋጣሚ በመጠቀም የተውሂድን አስኳል ተነፈሱ፡፡ ከእውነተኛው አምላክ ውጭ ያሉ አማልክትን አንቋሸሹ፡፡

قَالَ بَلْ فَعَلَهُ كَبِيرُهُمْ هَذَا فَاسْأَلُوهُمْ إِن كَانُوا يَنطِقُونَ

*«ጥቃቱን የፈፀመው ይህ ከሁሉም የሚልቀው ጣዖት ነው፡፡ መናገር የሚችሉ ከሆነ ጠይቋቸው አለ፡፡»* አንቢያ 63

ወጣቱ ኢብራሂም የሸንነውን ታዳሚ በበሰለ አዕምሮ መረጃ ነረተው፡፡ ሞኞች ሲሉ አሸማቀቀው፡፡ አንገታቸውን በሀፍረት ደፋ አድርገው እንዲህ አሉት፡፡

ثُمَّ نُكِسُوا عَلَى رُؤُوسِهِمْ لَقَدْ عَلِمْتَ مَا هَؤُلَاءِ يَنطِقُونَ

***«እነዚህ ጣዖታት መናገር እንደማይችሉ (አሳምረህ) ታውቃለህ፡፡»*** አንቢያ 65

ከዚህ በመነሳት ብቸኛ ጠቃሚና ጎጂ አላህ እንደሆነ ተናግረው አምልኮታቸውን ተቹት፡፡ የሚገነዘቡ ህዝቦች እንዳልሆኑ፣ አዕምሯቸው የሚያስተነትን አለመሆኑን በግልፅ ነገሯቸው፡፡

أُفٍّ لَّكُمْ وَلِمَا تَعْبُدُونَ مِن دُونِ اللَّهِ أَفَلَا تَعْقِلُونَ

«***ሑፍ ለናንተም ከአላህ ሌላ ለምታመልኳቸውም ጣኦታት አታስቡምን***» (ሲል በፅኑ ኮነኗቸው) አንቢያ 67

ኢብራሂም ላይ አይቀጡ አቀጣጥ እንደሚፈፀምባቸው ለአምላኮቻቸው እንሚበቀሉ አስታወቁ፡፡

قَالُوا حَرِّقُوهُ وَانصُرُوا آلِهَتَكُمْ إِن كُنتُمْ فَاعِلِينَ

***«ኢቃጥሉትና አማልክቶቻችሁን እርዱ (አንዳች ነገር የምታደርጉ) ከሆናችሁ (አሁን አድርጉ) አሉ፡፡» አንቢያ 68***

ተንኮልን አስበው ተሰባሰበዋል፡፡ ኢብራሂም ብቸኛ ናቸው፡፡ ከሰው የሆነ ረዳትም ይሁን ተከታይ የላቸውም፡፡ ለብዙ ወራት በተቀጣጠለ እሳት ውስጥ በወስፈንጥር ወርውረው አስገቧቸው፡፡

ለባሪያዎቹ ቅርብ ረዳት የሆነው አላህ መላዕክትን ላከ፡፡ ጅብሪል፣ሚካኢል፣ ኢስራፊል በየተራ መጡ፡፡ ሊረዷቸው ዝግጁና ታዛዥ እንደሆኑ ገለፁላቸው፡፡ ባለሙሉ ልቡ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) ግን

*«አላህ ቢቃኝ በሱ መመካት ምንኛ ያማረ ነው፡፡»* አሉ

አላህ (ሱ.ወ) በባሪያውና ወዳጁ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) የእምነት ፅናት ስለተደሰተ እሳትን ከአቃጣይነቷ ጋር ለኢብራሂም ቀዝቃዛና ሰላም ምቹ እንድትሆን የማይሻረውን ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡

قُلْنَا يَا نَارُ كُونِي بَرْدًا وَسَلَامًا عَلَى إِبْرَاهِيمَ

*«እሳት ሆይ! ለኢብራሂም ቀዝቃዛና ምቹ ሁኚለት አልን፡፡»* አንቢያ 69

ወጣቱ ከኢብራሂም (ዐ.ሰ) የህይወትና፣ የዳዕዋ እንዲሁም የትግልና ዳዕዋን ህይወት አስተምህሮ ይቀስማል፡፡ ኢስላማዊ ዳዕዋን ለማድረስ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ያሻል፡፡ ጥበብ የአማኝ የጠፋች ንብረት ናት፤ ካገኘባት ቦታ ላይ ይይዛታል፡፡

## የዋሻው ባለቤቶች (አስሀቡል -ከህፍ)

በተመሳሳይ ዕድሜ ላይ የነበሩ ለጋ ወጣቶች ነበሩ፡፡ በሮም ድንበር አካባቢ አንድ ፍትሀዊ ንጉስ ህዝቡን ያስተዳድር ነበር፡፡ ይህ ንጉስ ረዘም ላሉ ዓመታት በፍትሀና እኩልነት ስለገዛ ህዝቡ ሰላምና ምቾትን ሊያገኝ ቻለ፡፡

ይህ ንጉስ ሲሞት ግን የህዝቡን የወደፊት እርምጃ ሊገታ የሚችል ልዩነት ተፈጠረ፡፡ ያ ልዩነታቸው ወደ ዕድለ ቢስነት መራቸው፡፡

የጎረቤት ሀገር ንጉስ የነበረው ዳቁዊስ ይህችን የድንበር ላይ ሀገር በመውረር በራሱ አገዛዝ ስር እንድትወድቅ አደረገ፡፡ ዳቁዊስ ለራሱ ያሸበረቀ መኖሪያ (ቤተ-መንግስት) በመገንባት የተቻለውን ያህል በጌጥ እንዲያምር ጣረ፡፡ ከተወረሩት ህዝቦች ውስጥ በጥበብና ችሎታ የተካኑ ስድስት ሰዎች በመምረጥ ሚኒስትሮቹ አደረጋቸው፡፡ በመቀጠልም የሚያስተዳድረውን ህዝብ ያመልከው ዘንድ አዘዘ፡፡ መሀይምና ቂሉ ህዝብ ይህን ንጉስ እንደ አምላክ በመቁጠር ከርሱ ፊት መስገድና ማምለክ ጀመረ፡፡ በእንዲህ መልኩ የተወሰነ ጊዜ አለፈ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ለዚያች ሀገር ልዩና ግዙፍ ፌስቲቫል ተዘጋጀ፡፡

በዚህ ፌስቲቫል እየተዝናኑ ሳለ ለንጉሱ አንድ መልዕክት ደረሰው፡፡ አስደንጋጭ፣ ንግስናውን የሚዋጋና ተመላኪነቱን  የሚነጥቅ ነበር፡፡ ፊቱ ተለዋወጠ መልዕክቱም የፐርሺያ ገዥ የሮምን ድንበር ጥሶ በመግባት ወደ ዋና ከተማው (መናገሻው) እየገሰገሰ እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡

እነዚያ ስድስት ሚኒስትሮቹ ከንጉሱ ንዴትና ብስጭት የተረዱት ነገር ስላለ በተገናኙ ጊዜ የሆነ ታሪካዊ ክስተት እንደሚኖር እርስ በእርስ ተነጋገሩ፡፡ ታዲያ የዚህ ጌታ ነኝ ብሎ የሚያስብና ህዝቡን  እንደ ጋሪ የሚመራ ተራ ሰው አምላክ ሊሆን እንዴት ይቻለዋል ሲሉ እርስ በእርስ መነጋገር ጀመሩ፡፡ ይህ ደግሞ የአስተሳሰባቸውን ምህዳር አዳበረው፡፡ ፀሀይና ጨረቃን የፈጠረው ፣አንፀባራቂ ከዋክብትን የበተነው እኛን በእናቶቻችን ማህፀን ውስጥ መገኘት (existence) ያመጣ፣ የአካል ጥንካሬ የሰጠ፣ ለመኖር የሚረዱ ግብዓቶችን ያሟላ ማን ሊሆን ይችላል? በማለት ከስድስት አንዳቸው ጥያቄ አቀረበ፡፡ "ጓደኞቼ ሆይ! ይህን የማድረግ ብቸኛ ችሎታ ያለው ሀያሉ አላህ ብቻ ነው" በማለት ጉዳዩን አጠበቀው፡፡ "ስለዚህ ይህ ዳቁዊስ ትልቁ ጌታ ሊሆን አይችልም" ብሎ አስተሳሰቡን አከሰመው፡፡ "ጓደኞቼ ሆይ! ይህ ርካሽ ንጉስ ህይወታችንን አዋርዶታል፡፡ አምልኮ የሚገባው ለርሱ ሳይሆን ለሀያሉ አላህ ሲሆን ጊዜያችንን በዝብዞታል፡፡ ለምን ለርሱ ተገዢዎችና ተጨቋኝነት ቀንበር መንጭቀን በማውጣት አላህን አናመልክም፡፡ ለበፊቱ ሀጢአቶቻችንም ምህረትን እንለምናለን" ተባባሉ፡፡ ዓለማዊ ቅንጦትና ደስታ ከአላህ ቁጣና ቅጣት አያወጣንም ሲል ይህን ተልዕኮ የጀመረው ብልህ ወጣት መልዕክቱን አሰማ፡፡

ባልደረቦቹ እጅግ ተመስጠው አዳመጡት፡፡ "ከዚህ ጣዖት አምላኪ ቦታ ሸሽተን በረሀማና  ነፃነት ያለበት ቦታ በመሄድ አላህን እናመልካለን" በማለት ወሰኑ፡፡

በሚቀጥለው  ቀን ስድስት ጓደኞሞች በሚስጥር ከቤታቸው በመውጣት ራቅ ወዳለ በረሀማ ስፍራ ነጎዱ ከመኖሪያ መንደራቸው የተወሰኑ ማይሎችን ከተጓዙ በኋላ አንድ እረኛ በጎች እያገደ አገኙት፡፡ የሚጠጣ ውሀ ጠየቁት፡፡ እረኛውም "ፊታችሁ ላይ የንግስናና ጨዋነት ምልክት

ይነበብባችኋል እነማን ናችሁ? ወዴትስ ነው የምትሄዱት?” ሲል ጠየቃቸው እነርሱም “እኛ የንጉሱ ሚኒስትሮች ነበርን፡፡ ነገር ግን ሠራተኝነታችንንና ባርነታችንን ለሌላ አካል ለመስጠት እየሄድን ነው፡፡ የዓለማቱን ጌታ አላህን በነፃነት ለማምለክ እየሸሸን ነው” አሉት፡፡ “ለምን?” በማለት ጥያቄውን አስከተለ “ንጉስ ዳቁዊስን ማምለክ መንፈሳዊ ማንነታችንን አሟጠጠው፡፡ በዚህም የተነሳ ነፍሳችን ላይ ከፉ ተፅዕኖ አደረብን” አሉት፡፡

እረኛውም “እኔም የናንተው ዓይነት አስተሳሰብ አለኝ፡፡ ባልደረባችሁ ሆኜ የጉዟችሁም ተባባሪ በመሆን አላህን ላምልክ” አላቸው፡፡ ተስማሙ፡፡ ይጠብቃቸው የነበሩ በጎችን ለየባለቤታቸው በመመለስ አብሯቸው ተጓዘ፡፡

የእረኛው ውሻ ስለነበር ተከተላቸው፡፡ ነገር ግን የውሻው ጩኸት የት እንዳለን ያሳውቅብናል በሚል ፍራቻ ወደ ኋላ ለማስቀረት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም ሌላ ምርጫ አጥተው ባልደረባነቱን የግድ ተቀበሉ፡፡

እረኛውም እየመራቸው ዋሻ ውስጥ አስገባቸው፡፡ ፍራፍሬዎች ይመገቡ ነበር፡፡ የፀሀይ ብርሀንና ሙቀት በዋሻው ቀዳዳ ትገባላቸው ነበር፡፡ ራሳቸውን ካረጋጉና ካፍታቱ በኋላ አላህን ወደ ማምለክ (ተመስጦ) ገቡ፡፡

## *ረዥሙ እንቅልፍ*

ከጥቂት ጊዜ በኋላ እነዚህ ውድ ሰዎች በአንድ ላይ እረፍት ለማድረግ ጋደም አሉ፡፡ ውሻቸውም በዋሻው በር ላይ ራሱን በፊት እግሮቹ ላይ በማሳረፍ ተኛ፡፡ መልካም መዓዛ፣ የፀሀይ ሙቀትና ብርሀን በነርሱ ላይ ይመጣላቸው ነበር፡፡ በዚህ መልኩ እነዚህ ወጣቶች ጓደኛሞች ለ309 ዓመታት ተኙ፡፡

## **እርስ በእርስ ተጠያየቁ**

ከእንቅልፋቸው የአላህ ገደበ-ቀን ሲደርስ ነቁ፡፡ እርስ በእርስም ተጠያየቁ ወደ ስምጥ እንቅልፍ ሲገቡ የነበሩት ዕፅዋትና ፍራፍሬዎች በሙሉ

ጠፍተዋል፡፡ እነርሱም ከባድ የረሀብ ስሜት አገኛቸው፡፡ እጅግ የገረማቸው ግን የምንጭ ውሀውና የሚበሏቸው ዕፅዋት በአንድ ቀን እንዴት ጠፉ ሲሉ ተጠያየቁ፡፡ ለዚህ ነው ዋሻው ውስጥ ስንት ጊዜ ቆየን ብለው የተጠያየቁት፡፡

አላህ ጠበቃቸው፡፡ እርሱን ወደው ከአምባገነን አገዛዝ ሸሽተው ዋሻ ገቡ፡፡ ተንከባከባቸው፡፡

ቁርአን ይህን ታሪክ አንድ ምዕራፍ በመሰየም ትኩረት ሰጥቶታል፡፡ የዋሻው ምዕራፍ በየሳምንቱ ጁምዓ ይነበባል፡፡ እነዚህ እንቁ ወጣት ታጋዮች ሁሌም ይታወሳሉ፡፡

የወጣትን የትግል ጉዞ መስመር የሚያስይዝ ልብን ሰቅዞ የሚይዝ ታሪክ ነው፡፡ ወጣት ሙስሊም ከአስሀቡል ከህፍ ግፈኞችንና ማን አለብኝ ባይ አምባገነኖችን መታገል፤ የተውሂድን ስር መጠበቅና ለአላህ ሲሉ ድሎትን ጥሎ መሰደድን ይማራል፡፡

نَّحْنُ نَقُصُّ عَلَيْكَ نَبَأَهُم بِالْحَقِّ إِنَّهُمْ فِتْيَةٌ آمَنُوا بِرَبِّهِمْ وَزِدْنَاهُمْ هُدًى

***«እኛ ወሬያቸውን በእርግጥ በአንተ ላይ በእውነት እንተርካለን፡፡ እነሱ በጌታቸው ያመኑ፤ጎበዞች ናቸው፡፡መመሪትንም ጨመርንላቸው፡፡»*** አል-ከህፍ 13

## የስነ- ምግባር አባት ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ)

በክብሩ ዝናብ ያመጣ ፃእድ

የባል አልባ እንስቶች ጠበቃ

የየቲሞች ተገን ማዕድ፡፡ (አቡ ጧሊብ)

ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከማር የጣፈጠ ስም፡፡ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) የላቀ ስብዕና፡፡ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) የሁለት ዓለማት ታላቁ ሰው፡፡ ፍትሀዊ ዳኛ፡፡ ዕንቁ ማንነት፡፡ ተናፋቂ አባት፤ የኡማ አለኝታ፡፡

የወጣትነት ጊዜያቸውን በሚገባ ራሳቸውን በመገንባት ለወደፊት ለሚቀበሉት የነብይነት ኃላፊነት አዘጋጅተው ነበር፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ የሰናይነትን ምስክርነት ተጎናፅፈዋል፡፡ ሁሌም ቢሆን ትሁትና ታታሪ፣ አዛኝና ርህሩህነት የርሳቸው መለያ ነው፡፡

ከሁዲያንና አጋሪዎች የእምነት ነፃነትን ለማፈን ያደረጉትን ከፍተኛ ጥረት በብዙ እርከኖች በአሸናፊነት ተወጥተዋል፡፡

## እንጀራ ፍለጋ

የአላህ መልእክተኛ ለወጣትነት እድሜ ሲደርሱ እንጀራ ፍለጋ መሮጥ ጀመሩ፡ ፡ ፍየል ጥበቃ የጥረታቸው መጀመሪያ ነበር፡፡ በኋላ ላይ፡- ‹‹ለመካ ሰዎች በቀራሪጥ (ክፍያ)ፍየል እጠብቅ ነበር፡፡›› ሲሉ ተናግረዋል፡

ከወጣትነት አጓጉል ድርጊቶችና ጨዋታዎች ሁሉ አላህ ጠብቋቸዋል፡፡ ስለ ራሳቸው እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

‹‹በመሐይምነት ዘመን ወጣቶች ይፈጽሟቸው የነበሩ ድርጊቶችን ለመፈጸም ያሰብኩት ሁለት ጊዜ ብቻ ነበር፡፡ በነዚህም ጊዜያት አላህ ያሰብኩትን እንዳላደርግ አቀበኝ፡፡ ከዚያ በኋላ በመልእክተኛነት እስኪልከኝ ድረስ ተመሳሳይ ድርጊት አስቤ አላውቅም፡፡ ይኸውም አንድ ቀን በሌሊት በመካ ከፍታማ ቦታዎች ላይ ፍየል አብሮኝ ይጠብቅ ለነበረ ልጅ፡- ፍየሌን ጠብቅልኝ፡፡ ልክ እንደወጣቶች መካ ውስጥ ስጫወት ልደር» አልኩት፡፡ ‹‹ይሁን›› አለኝ፡፡ወደ መካ ወረድኩ፡፡ እዚያ እንደደረስኩ ከአንድ ቤት ውስጥ ዘፈን ሰማሁ፡፡ ምንድን ነው? በማለት ስጠይቅ፣ የሰርግ ዘፈን እንደሆነ ተነገረኝ፡፡ ቁጭ ብዬ ማድመጥ ስጀምር አላህ ጆሮዬን ደፈነው፡፡ ጥልቅ እንቅልፍም ወሰደኝ፡፡ ከእንቅልፍ ያነቃኝ የረፋዱ ጸሐይ ግለት ነበር፡፡ ወደ ባልንጀራየም ተመለስኩ፡፡ ስለ አዳሩ ጠየቀኝ፡፡ የሆነውን ነገርኩት፡፡ በሌላ ሌሊትም ተመሳሳይ ሙከራ አደረግኩ፡፡ ልክ የመጀመሪያው ሌሊት ዓይነት ሁኔታ አጋጠመኝ፡፡ ከዚያ በኋላ ያን ዓይነት ሐሳብ አስቤ አላውቅም፡›› 

## ከመልዕክተኛው

ገና በለጋ እድሜያቸው እንጀራ ፍለጋ ያሳዩት ትጋት ጠቃሚ ትምህርቶችን አካቷል፡፡

1) አላህ ለነቢዩ ሙሐመድ ያላበሳቸውን ውብ ባህሪና ረቂቅ ስሜት ያሳያል፡፡ አጎታቸው የተሟላ እንክብኮቤ ያደርጉላቸው ነበር፡፡ ልክ እንደ አባት ያዝኑላቸው ነበር፡፡ ይህም ሆኖ ግን መልእክተኛው ሰርተው ማደር እንደሚችሉ ሲሰማቸው ወደ ስራ ተሰማሩ፡፡ የአጎታቸውን የገንዘብ ቀዳዳዎች ያቅማቸውን ያህል ለመሸፈን ጥረት አደረጉ፡፡ ከስራቸው የሚያገኙት ገቢ ምንም ያህል አነስተኛ ቢሆንም እንኳ ኩሩ ስብእናቸው፣ ያቅሙን ያህል ከመጣር የማይሰስተው ባህሪያቸው ወደ ስራ መራቸው፡፡ የአጎታቸው ውለታ ለመመለስና የተግባር ምስጋና ለማድረስ ይህን አደረጉ፡፡

ስለዚህም አንተም ልክ እንደርሳቸው ጥንቁቅና ኩሩ ሁን፡፡ «ራስህን ባንገትህ ተሸከም፡፡»

2) አላህ ለባሪያው በምድር ላይ የሚወድለትን የሕይወት ዓይነት የሚያብራራ ጌታ ነው፡፡ ይኸውም አላህ ቢፈልግ ኖሮ ለነቢዩ ገና ከሕይወታቸው መጀመሪያ አንስቶ ኑሯቸውን ድሎታማ በማድረግ እንጀራ ፍለጋ ከመኳተን መታደግ ይችል ነበር፡፡ ግና ለሰው ልጅ መልካሙ ገንዘብ ለሕብረተሰቡ በሚሰጠው አገልግሎት ወይም በጥረቱ የሚያገኘው መሆኑን፣ ሳይሰራ እና ሳይለፋ፣ ለሚኖርበት ማሕበረሰብ ቅንጣት በጎ ነገር ሳያደርግ፣ ስራ ፈትቶና እጁን አጣጥፎ ተቀምጦ የሚያገኘው ገንዘብ ደግሞ መጥፎ መሆኑን በጥበቡ ሊያስተምረን ስለከጀለ ነው፡፡

በመሆኑም ልክ እንደ ተወዳጁ ነብይ ሐላል ስራዎችን ብቻ ሰርተህ ገንዘብ ለማግኘት ጉጉና ትጉ ሁን፡፡

## አክቶበር 26 ቀን 1954

## የተጠነሰሱ ድብቅ ሴራዎች

ወጣት የምድርን ሁለንተናዊ ይዘትና ቅርፅ ሊቀይር የሚችል ሀይል መሆኑን በጥልቅ የተገነዘቡት መሰሪዎቹ ጽዮናውያኑ አይሁዶች አክቶበር 26 ቀን 1954 ከግብፅ የወቅቱ ፕሬዝዳንት ጀማል ዓብዱልናስር ጋር ሚስጥራዊ ሲምፖዚየም አድርገው እንደነበር ኡስታዝ ዓባስ ሀሰን ሰይሲ በአንድ መፅሀፋቸው ላይ ዘርዝረውታል፡፡ እነዚህን ሴራዎች ከላይ በማስቀመጥ ዛሬ በዕቅዳቸው የደረሱ ነገሮችን ለማየት እንሞክራለን፡፡

1) ***ሙስሊም ወጣቶች ከማንኛውም ዓይነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዲገለሉ ማድረግ በዒባዳ መጠመድንና ብህትውናን እንደ ብቸኛ ኢስላማዊ አስተምህሮ አድርገው እንዲያዩ ማድረግ፡፡***

<u>ፖለቲካን እንደ እሾህ</u> ፡- ይህ ሴራ ያሳደረው ተፅዕኖ ከባድ ነው፡፡ ወጣቱ ክፍል በሀገር ጉዳይ መጨነቅ፤ ሙብት ማስከበር በመሰረተ-ልማት አውታሮች ጎዳና መራመድን አስቦት አያውቅም፡፡ ምክንያቱም የነዚህ የምዕራቡ ዓለም ሴራዎች ተከታታይ ዱላዎች ከነዚህ አስተሳሰቦች አላቆታል፡፡ በዚህ ረገድ ታዲያ ሙስሊሙ ወጣት በተዘዋዋሪም ይሁን በቀጥታ ከፖለቲካው ዓለም ተገሏል፡፡ ይባስ ብሎም ፖለቲካ ሀራም (እርም) ነው የሚሉ አንጃዎች ሁሉ ተፈልፍለዋል፡፡ የኢስላም ግቡ ተከታዮቹ የምድርን የቆሸሸ ገፅታ ያፀዱ ዘንድ በመልካም የሚያዙ ከመጥፎ የሚከለክሉ ዕፁብ ስብዕናችን ማፍራት እንጂ ጋጠ-ወጥና ልቅ ዋልጌ ፖለቲከኞች በሰዎች ክብር ላይ እንዲጫወቱ አይደለም፡፡

***«ለሰው ልጆች ከተገለፁት ህዝብ ሁሉ በላጭ ኾናችሁ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ በአላህም ኣንድነተ ታማናላችሁ» » አል-ዒምራን 110***

ይህን አስኳል ግብ ያነገቡ ሙስሊም ወጣቶች እንዳይበዙ መሰሪዎቹ ወጣቱን በዒባዳና ብህትውና ላይ ብቻ እንዲያተኩርና ይተጋ ዘንድ ተዘዋዋሪ (indirect) ወጥመዶችን አዘጋጅተው ምድር ላይ አሰራጩት፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ግን ወጣትነት ካለፈና የስራ ሞራል ከሞተ በኋላ ይባነናል፡፡ ኢስላምን ከፖለቲካ የመለየት አባዜ የተጠናወታቸው አንዳንድ አንጃዎች የዚህ

ሲምፖዚየም ግፊት ከበስተጀርባቸው አለ፡፡ ኢስላም ሀይማኖት ብቻ ሳይሆን የህይወት መንገድም ጭምር ነው፡፡ ሁሉም መስኮችና እሴቶች የኢስላም ፋና አለባቸው፡፡

## *2) ሙስሊም ወጣቶች በመዝሀብ ልዩነቶቻቸው ዙሪያ የበለጠ እንዲያተኩሩ ማድረግ የኺላፍ አጀንዳዎችም በጣም ገዝፈው እንዲታይዋቸው ማድረግ*

**<u>የኺላፍ አጀንዳዎች፡-</u>** መሰረታዊ የኢስላም ማዕዘናት ላይ የተለያዩ የዘመናችን ዑለሞችና ሙስሊም ዱዓቶች ባይኖሩም በቅርንጫፍ ጉዳዮች ግን ቀደምት ሊቃውንት ሳይቀሩ ተለያይተዋል፡፡ መለያየት ደግሞ የሰው ባህሪ ሲሆን ከባህሪ ውሎና ከዕውቀት መሰረት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በኢስላማዊው ርዕዮተ-ዓለም ውስጥ ገብቶ መኖር ትልቅ ትዕግስትን ይጠይቃል፡፡

إِنَّ هَذِهِ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً

*‹‹ይህ ህዝባችሁ አንድ ህዝብ ነው"*

ኺላፍ ያለና የሚኖር ከመሆኑ ጋር እጅግ የሚያሳዝነው ኡማው ብናኟን ቋጥኝ፣ ኮረብታዋን ትልቅ ተራራ አሳክሎ ማቅረብ የተጠናወተው አካል አለው፡፡ የራስን ገመናና ዛፍ የሚያህል ነውር ተሸክሞ ሰው ላይ ያለችን ትንሽ ቁጥቋጦ ሲያራግቡ የሚስተዋሉ አንጃዎች የዚህ መርህ ስር ተጠላዮች ናቸው፡፡ ስራን አይሰሩም ግን የሚሰራን ይወርፋሉ፡፡ የጥላቻን ክር ይስባሉ፡፡ ልዩነቶቻችን መሰረታዊ የልዩነት አንድነት ማዳበር ይጠበቅብናል፡፡ ያ ሲሆን ነው የተጠነሰሱልንን ሴራዎች የምናከሽፈው የተተበተቡ ገመዶችን የምንበጣጥሰው፡፡ መዋዋጥና መተራረም ሀሳቦቻችንን የመጋራት ባህልን መላበስ አለብን፡፡

## *3) ወጣቶች የነብዩ ሱና ከሰልጣኔ የተቃረነ ሆኖ እንዲታያቸው እና በሱናው እና ሌሎችም የኢስላም ምንጮች ላይ እንዲጠራጠሩ ማድረግ፡፡*

**<u>ሱና ከስልጣኔ የተቃረነ፡-</u>** ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.0.ወ) የሁለት ዓለማት ጌጥ ናቸው፡፡ ለኡማቸው በምድራዊ ህይወት ደፋ ቀና ብለው አኼራ ሄደዋል፡፡ በዚያኛው ዓለምም የትድግናን ኃላፊነት ይወጣሉ፡፡ የዚህ ኡማ ዓይን ናቸው፡፡ ከጨለማ ወደ ብርሀን አውጥተውታል፡፡ የአላህ ድንቅና ውድ የሰው ልጆች ስጦታ ናቸው፡፡

وَمَا أَرْسَلْنَاكَ إِلَّا رَحْمَةً لِّلْعَالَمِينَ

**« ለአለማት እዝነት አድርገን እንጂ አላክንህም፡፡» አል አንቢያዕ 107**

ምዕራቡን ዓለም ጨምሮ በርሳቸው የተፅዕኖ ጥላ ስር ያላረፈ የለም፡፡ ሱናቸው ጣፋጭና መሰህብነት ያለው ነው፡፡ በሩቁ የደስታ አፀድ በገዛ ፈቃድ መግባት መሆኑን የተገነዘቡት ይሁዲዎች ረሱልን (ሰ.0.ወ) ለማንቋቋሸሽ ሩጫ ጀመሩ፡፡ ወጣቱ በሱና አፍሮ የምዕራቡን ቅዠት ተከተለ፡፡ ሴት እህቶች ለሂጃብ ጀርባቸውን ሰጡ፡፡ ኢስላም ለሴቶች መብት ግዴለሽ ነው አሉ፡፡ ቁርአንን ጥርጣሬ ውስጥ ለማስገባት ድንጋይ ፈነቀሉ፤ጉድጓድ ማሱ ነገር ግን ፍላጎታቸው አፈር ለበሰ፡፡

### *4) ኢስላማዊ ተቋማትና ማህበራት እርስ በእርስም ሆነ የአንድ ቡድን አባላት እንዲጋጩ ጠንክሮ መስራትና ክፍፍሎችን መፍጠር፡፡*

**<u>ኢስላማዊ ተቋማት፡-</u>** በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ኢስላማዊ ድርጅቶች አንድ ወይም ሁለት የጥቃት ሙከራ ተደርጎባቸዋል፡፡ ውጫዊው የኢስላማዊ ተቋማት መዘጋታቸው፣ በሽብርና ፅንፈኝነት መወረፋቸው ሲሆን ከውስጥ ደግሞ እርኩስ ተልዕኮ ያላቸው አባላትን ማቀፋቸው ነው፡፡ ኡማው ሊጠቃባቸው የሚችሉ ቀዳዳዎችን ለጠላቶች ያመላክታሉ፡፡ ለጥቂት ጥቅማ ጥቅም ብለው ኡማው ላይ የዘመናት ቤት ስራን ይወዝፋሉ፡፡

በዚህ ሲምፖዚየም የታቀዱ ዓላማዎች ታዲያ ለስኬት በቅተዋል፡፡ የምናውቀው ስለሆነ መጥቀሱ አስፈላጊ መስሎ አልታየኝም፡፡ ኢስላማዊ

ተቋማት መቼም ሲቋቋሙ በአብዛኛው ትርፍ -አልባ (Non-Profitable) ናቸው፡፡

ነገር ግን ዓለም ላይ ያሉ ተቋማት ሲጋጩና ሲለያዩ ይታያሉ፡፡

5) ***ለወጣት ሴቶችና ወንዶች የተለዩ ስልጠናዎችን በእስልምና ስም በመስጠት ሌሎች የዕውቀት ዘርፎችና ትምህርቶችን በመጥፎ ዓይን እንዲያዩዋቸው ማድረግ ፡፡ ይህንንም ለእስልምና ዕውቀት በሚኖር ጉጉት ሽፋን መፈፀም፡፡***

<u>**ትምህርት ሀራም ነው፡-**</u> ከመስሪዎቹ ይሁዲዎች ከተጠነሰሱት ኡማውን መግደያ መንገዶች አንዱ ይህ ነው፡፡ ዓለም ላይ ካሉ የስለላ ድርጅቶች ልዩ ጥቅም የሚያገኙ፣ የኡማውን ቆዳ የለበሱ፣ቋንቋውን የሚናገሩ፣ ሁለት ፊት ያላቸው ጭራቆች ዘመናዊ ትምህርት (Academy) ሀራም (እርም) ነው ሲሉ መስተዋላቸው(ከየዩኒቨርሲቲው ብዙዎችን አፈናቅለዋል፡፡) ሙስሊሙ ኡማ ከተሰጠው ወርቃማ ዲን በተጨማሪ ምድራዊ ት/ቶችን መቅሰሙ እጅግ እንደሚጠቅመው የተረዱት የምድሪቱ ቫይረሶች ይህን እኩይ ዓላማቸውን በተግባር አዋሉት፡፡

ያላወቁ አለቁ ነውና የኢስላምን ዱንያ ከአኼራ አለመለየት የማያውቁ ጥቂት ክፍሎች ይህን ከጀርባው እሾህ ያለበት ምክር ሰሙ፡፡ በእርግጥ ለኢስላም ጠላቶች አሉት፡፡

6) ***በስራ ላይ ያሉ ኢስላማዊ ተቋማትን ዝና ለማደብዘዝ ሌሎች ድርጅቶችን በማቋቋም በርካታ ስራዎች ላይ መሰማራት፣ ወጣቶች ጥሩ ዓላማ ያላቸውን ቀደምት ድርጅቶች ትተው ወደ ሌሎች እንዲዘነበሉ ማድረግ፡፡***

<u>**ሌሎች ድርጅቶች ማቋቋም**</u> ፡- ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የአህባሽ፣የሺዓና መሰል ድርጅቶች ናቸው፡፡ ሌሎች የአስተሳሰብ ት/ቤቶችን (School of tought's) አስፋሪ ቀለም በመቀባት የሰዎችን ዐቅል ነጥቀዋል፡፡

በአጠቃላይ ወጣቱን አምክኖ ለማስቀረትና ጥቅም አልባ ዜጋ ለመፍጠር ታች ላይ የሚሉት የእርኩሳን ስብስብ ዓለምን ለአንድ እነርሱ (New world order) ብለው ለሚጠሩት (System) ለማዘጋጀት ነው፡፡ ያንን ጊዜ በናፍቆትና ጉጉት እየተጠባበቁት እንደሆነ ይገልፃሉ (ይሁዲዎቹ)፡፡

ይህንንም እውን ለማድረግ ለራሳቸው የተለያየ ውስጠ ሚስጥር ያላቸውን ማህበራት በማቋቋም ከጥንት የነበሩ ርካሽ አምልኮዎችን እያስፋፉ ነው፡፡ በእርግጥ ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) በሀዲሳቸው ላይ ይህ ህዝብ ጣዖትን ሳያመልክ ምፅዓት አይቆምም ብለው ነበር፡፡ እነ (Secret Socities) የሚስጥር ማህበራት (illumunities) ጥበብ እና መዝናኛ የሚሉ ካባዎችን በለበሱ የጥመት ጥሪዎች ከተሰማሩ ቆይተዋል፡ ፡ ዓለም ላይ በተለይ ምዕራቡ ዝነኛ የፊልም ተዋናዮች ፣መሪዎች፣ ዘፋኞች፣አምላክ አድርገው የያዙት ሰይጣንን ነው፡፡ ለዚህ ነው ቁርአን ስሜትን ከመከተልና የሰይጣንን ጅራት ከማነፍነፍ አጥብቆ የከለከለው፡፡

## ይኸው ጀንበሩ

መንገዱ ልፋት፣ ትዕግስትንና ፅናትን ይጠይቃል፡፡ ግን ፍሬው ጣፋጭ፣ስር የሰደደ፣ ሁሉን ደራሽ እና ዘልዓለማዊ ነው፡፡ ምድርን የአላህ ትጉሀን ባሪያዎች ይወርሷታል፡፡

وَلَقَدْ كَتَبْنَا فِي الزَّبُورِ مِن بَعْدِ الذِّكْرِ أَنَّ الْأَرْضَ يَرِثُهَا عِبَادِيَ الصَّالِحُونَ

**«ምድርንም መልካሞቹ ባሮቼ ይወርሷታል ማለትን ከመጽሓፉ (ከተጠበቅ ሰሌዳ) በኋላ በመጽሓፎቹ በእርግጥ ጽፈናል፡፡» አል አንቢያ 105**

የመንገዱ ባህሪ ይኸው ነው፡፡ በየጊዜው የነበሩ የኩፍር አቀንቃኞች ነብያትና ንፁሀንን ተገዳድረዋል፡፡ ነገር ግን አማኞች ምድር ላይ አንዳንድ

ጠላቶቻቸውን ረተው በደስታና ነፃነት አሊያም ሰማዕታትና ምርጥ ሆነዋል፡፡ የፈርዖን ባለቤት፣ አስሀበል-ኡኽዱድ ወዘተ...

ባህሪው ሆኖ የአላህ ዕርዳታ ከተፍ የሚለው ተስፋ ካስቆረጠ፣ጉልበት ካብረከረከ፣ መሬት ጥብብ ካለች በኋላ፣ነፍስ ጉሮሮ ስትደርስ ነው፡፡

أَمْ حَسِبْتُمْ أَن تَدْخُلُوا الْجَنَّةَ وَلَمَّا يَأْتِكُم مَّثَلُ الَّذِينَ خَلَوْا مِن قَبْلِكُم مَّسَّتْهُمُ الْبَأْسَاءُ وَالضَّرَّاءُ وَزُلْزِلُوا حَتَّىٰ يَقُولَ الرَّسُولُ وَالَّذِينَ آمَنُوا مَعَهُ مَتَىٰ نَصْرُ اللَّهِ أَلَا إِنَّ نَصْرَ اللَّهِ قَرِيبٌ

***«በውነቱ የነዚያ ከበፊታችሁ ያለፉት (ምዕመናን መከራ ) ብጤ ሳይመጣባችሁ ገነትን ልትገቡ ታስባላችሁን? መልዕክተኛውና እነዚያ ከርሱ ጋር ያመኑት የአላህ እርዳታ መቼ ነው? እስከሚሉ ድረስ መከራና ጉዳት ነካቻቸው፣ተርበደበዱ ንቁ የአላህ እርዳታ በእርግጥ ቅርብ ነው (ተባሉም)፡፡» አል በቀራህ 214***

ፈተና ሲበዛ ዕርዳታ መምጣቱን ነው የሚያሳየው ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) አላህ ሰዎችን ሲወዳቸው ይፈትናቸዋል ብለዋል::

## ኢስላም ውስጥ ኪሳራ የለም፡፡

ለኢስላም በሚደረግ ትግል ውስጥ ገንዘብ፣ህይወትና ሌላም ውድ ነገር ቢጠፋ ኪሳራ ተብሎ ሂሳብ ስሌት ውስጥ አይገባም፡፡ ህይወት ቢጠፋ ሸሂድነት ነው፡ ፡ ሸሂዶች ደግሞ ሙታን አይደሉም፡፡

ስለዚህ ጉዳዩ ምድር ላይ እያሉ ነስር ማግኘት ወይም ደግሞ በወዲያኛው ዓለም ከምርጦቹ ጋር መቀላቀል ነው፡፡ ገንዘብ ቢወጣና ቢፈስ ሰደቃ ነው፡፡ ጊዜ ቢባክን ጂሀድ ነው፡፡ ታዲያ ኪሳራው ምኑ ላይ ነው?

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا هَلْ أَدُلُّكُمْ عَلَىٰ تِجَارَةٍ تُنجِيكُم مِّنْ عَذَابٍ أَلِيم

تُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ وَتُجَاهِدُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ بِأَمْوَالِكُمْ وَأَنفُسِكُمْ ۚ

ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ

***‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ ከአሳማሚ ቅጣት የምታድናችሁ የሆነችን ንግድ ላመላከታችሁን? (እርሷም) በአላህና በመልዕክተኛው ታምናላችሁ፤በአላህ መንገድም በገንዘቦቻችሁ በነፍሶቻችሁም ትታገላላችሁ፣ ይህን የምታውቁ ብትሆኑ ለእናንተ የተሻለ ነው፡፡›› አል ሶፍ 61***

## መንፈሳዊ ተከሎች

### 1) ትዕግስት

መንገዱ እጅግ አሰልቺና ረዥም እንዲሁም አድካሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ብዙ እሾሆች ይኖሩታል፡፡ ፍርሀትን ሊያመጡ የሚችሉ ሁነቶች ይከሰታሉ፡፡ ሰዎች ሊያሴሩ፣ እንቅፋት ሊሆኑና አጥፊ ሊሆኑ ያመቻል፡፡ ነገር ግን ትዕግስት የሁሉም ነገር ቁልፍ ነው፡፡ በትግል ወቅት ያበረታታል፡፡በፈተና ጊዜ ያፅናናል፡፡ የአማኝ ወጣቶች የእርስ በርስ ትውውስና የአደራ ቃል መሆኑ ፍቱን ነው፡፡

إِلَّا الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ وَتَوَاصَوْا بِالْحَقِّ وَتَوَاصَوْا بِالصَّبْرِ

*«በእውነትና ትዕግስት ላይ አደራ ይባባላሉ፡፡»* **አል-ዐስር**

## 2) ፅናት

ከትዕግስት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ ችግሮችን ታግሶ የማለፍ ሁኔታ ቢኖርም የፅናቱ ጉዳይ ግን ይፈታተናል፡፡ነገር ግን ወሳኝ ነው፡፡ ምን ያህል ጊዜው ቢረዝምም፣ዓመታት ተለውጠው መጨረሻቸው ቢናፈቅም አማኝ ግን በፅናቱ ከሁለት አንዱን ያገኛል፡፡ ዓላማውን ያሳካል አሊያም መስዋዕት ይሆናል፡፡

مِنَ الْمُؤْمِنِينَ رِجَالٌ صَدَقُوا مَا عَاهَدُوا اللَّهَ عَلَيْهِ فَمِنْهُم مَّن قَضَى نَحْبَهُ وَمِنْهُم مَّن يَنتَظِرُ وَمَا بَدَّلُوا تَبْدِيلًا

***«ከአማኞች በርሱ ላይ ለአላህ ቃል ኪዳን የገቡበትን በእውነት የፈጸሙ ወንዶች ኣልሉ ከነሱም ስለቱን የፈጸመ(ለሃይማኖቱ የተገደለ) ኣልለ፡፡ከነሱም ገና የሚጠብቅ ኣለ፡፡(የገቡበትን ቃል) መለወጥንም ኣልለወጡም፡፡»***

የፅናት ምንዳው ግዙፍ ነው፡፡ ፅናት ላይ ግን የተደነቀሩ እንቅፋች አሉ፡፡ የመንፈስ ጥንካሬን ማጣት፣ስንፍናን የሚያናፍሱ ወገኖች ጫና፣ ወዘተ... ለመሰሎቻቸው ቁርአን እነዲህ ይላል፡፡

وَمِنَ النَّاسِ مَن يَقُولُ آمَنَّا بِاللَّهِ فَإِذَا أُوذِيَ فِي اللَّهِ جَعَلَ فِتْنَةَ النَّاسِ كَعَذَابِ اللَّهِ وَلَئِن جَاء نَصْرٌ مِّن رَّبِّكَ لَيَقُولُنَّ إِنَّا كُنَّا مَعَكُمْ أَوَلَيْسَ اللَّهُ بِأَعْلَمَ بِمَا فِي صُدُورِ الْعَالَمِينَ

*«ከሰዎችም በአላህ ኣመንን የሚል ሰው ኣለ፡፡በአላህም (በማመኑ) በተሰቃዬ ጊዜ የሰዎችን ማሰቃየት እንደ አላህ ቅጣት ያደርጋል ከጌታህም እርዳታ ቢመጣ እኛ በእርግጥ ከናንተ ጋር ነበርን ይላሉ፡፡አላህ በዓለማት ሕዝብ ልቦች ውስጥ ያለውን ዐዋቂ ኣይደለምን፡፡» አል ዐንከቡት 10*

ችግርና ፈተናዎችን በትዕግስት ማለፍ፣ ምድርን ከነ አስቸጋሪነቷ የማሸነፍ ትልቅ ጥበብ ነው፡፡

## 3) ብሩህ ተስፋ

ተስፋ ወደ ስኬት መድረሻ መርከብ ናት፡፡ ኢስላምን ከማንኛውም ምድራዊ ትንኮሳዎች ነፃ የሚያወጣ ተስፋ በወጣቱ ልቦና መኖር አለበት፡፡ ፋሽን ተከታይነት ከልቦናች ወጥቶ ቦታ ካጣ ከኡማው ላይም ይወገዳል፡፡ ተስፋ-ቢስነት ከፉና መጥፎ በሽታ ከመሆኑ ጋር ዱንያን ያጨልማታል፡፡ የከሀዲያንን እኩይ ባህሪም ያጋራል፡፡አስተሳሰባችን ኢስላም ነው፡፡ ወደ ርሱው በጥበብ የሰው ልጆችን እንጠራለን፡፡ ፍትህን ለማስፈን፣የሰዎችን ውዴታ ከጅለን ሳይሆን የአላህን ፍቅር ሽተን ስንታገል ነገ ያሰብነው እንደሚሳካ በመተማመን ነው፡፡ ***አዎ የዛሬ እውነታዎች የትላንት ህልሞች ነበሩ፤ የዛሬ ህልሞችም የነገ እውነታዎች ናቸው፡፡***

ወጣቱ ሙስሊም በፊት ከነበሩት ትውልዶች የደከመ ሊሆን አይገባም፡፡ አላህ ይህን የህይወት መንገድ በእጃቸው ምድራዊ ትግበራን ይቸር ዘንድ ሰበብ አድርጓቸው አልፈዋል፡፡ ለዚህም ስሩ የሰደደ እምነት፣ መገታት የሌለው ቋሚ ስራ፣ በአላህ ላይ ሙሉ ተስፋ፣ አላህን በመስዋዕትነት መገናኘትን የምትመኝ ነፍስ ልናዘጋጅ ይገባናል፡፡

## 4) ጥረትና ልፋት

ገንዘብ፣ጊዜንና ህይወትን ሳይሰስቱ ለኢስላም ማዋል ነው፡፡ የሙስሊሙ ወጣት መርህ መሆን ያለበት ሌሎችን ይጠቅም ዘንድ መስጠት፣ሌሎች ያጭዱ ዘንድ መዝራትና ሌሎች ያርፉ ዘንድ መድከም ነው፡፡

ይህ ሲሆን አላህ የኡማውን ዕርዳታ በወጣቱ በእጅ ያደርገዋል፡፡

# 4

# አውንታዊ የኋሊት ጉዞ

ኢስላም ህይወት ነው፡፡ለህይወት የሚያስፈልጓት የቀጣይነቷ ገባሮች ብዙ ናቸው፡፡ስልጣኔ ማለት በግለሰብም ይሁን በማህበረሰብ ደረጃ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ምጥቀት ነው፡፡ኢስላም አንፀባራቂ ታሪካዊ የስልጣኔ ዳራ አለው፡፡ ነገር ግን ዛሬ ያሁሉ የበላይነት ተሽመድምዶ ኡመተል ኢስላም የበይ ተመልካች ሆኗል፡፡ አልመሸም! ያን ታሪክ ዳግም ማምጣት ይቻላል፡፡ ከኡማው የበላይነትን የነጠቁት ምዕራባውያን ቁስን ብቻ ነው፡፡መንፈሱን በተለያዩ የአስተሳሰብ ዘመቻ መሳሪያዎች ቢፈታተኑትም ሙሉ በሙሉ ግን አላራቆቱትም፡፡ታዲያ ከኡመተል ኢስላም ውስጥ ሁለት ዓይነት ፅንፎች የሁሉን አቀፍ ስልጣኔ መሪነታችንን መመለስ እንደማንችል ተስፋ በመቁረጥ ይናገራሉ፡፡

የመጀመሪያዎቹ ዓይነቶች በምዕራቡ ሰላቢ ስልጣኔ ስር ባሪያ የሆኑ እና በራስ መተማመናቸውን የተነጠቁ ናቸው፡፡እነዚህ ፅንፎች ኡማው የብዙ ችግሮች አረም ውስጥ አንዳለ አድርገው ይቆጥራሉ፣ ለዚህም መንስኤው ምዕራባውያን ናቸው ሲሉ ይናገራሉ፡፡

አዎ! በእርግጥ የምዕራቡ ሞራል ገዳይ ስልጣኔ ዓለምን አደናቁሯል፡፡ ቢሆንም ግን ምስጋና ለአላህ ይሁን እና ቀስ በቀስ የህዝብ ቁጥር ስልቻቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተኮማተረች ነው፡፡በተለይ አምራች የሚባለው ክፍል ቁጥሩ አሽቆልቁሎባቸዋል፡፡ ምዕራቡ በወጣት ብዛት 25 የኡማችን የዕውቀት አድማስ እና ፖለቲካዊ ግንዛቤ ደግሞ ንሯል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ የምዕራቡ የባህል ወረራም እያከተመለት መጥቷል፡፡ ኡማው የነርሱን ፋና መከተል መሀይምነት በገዛ እጅ ባርነት እና ኋላቀርነት እንደሆነ ተገንዝቧል፡፡

ሁለተኛዎቹ ዓይነት ሰዎች ደግሞ የምዕራቡ ዓለም ስልጣኔ ያበቃለታል የሚለው እምነት ያልተዋጠላቸው ናቸው፡፡እነኚህ ተብ ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ በወቅቱ ያለውን ምዕራባዊ ባህል እና ወዳቂ ስልጣኔ በአንፀባራቂው የኢስላም ስልጣኔ የመተካት ወኔ የሌላቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን የታሪክ ገፅ እንደሚነግረን ብዙ ስልጣኔዎች ሰማይ ጠቀስ ከሆኑ በኋላ ላይነሱ ወድቀዋል፡፡ ሮምን፣ግሪክን እና ባቢሎንን ማየት ይቻላል፡፡ ይህን ስንል ግን የምዕራቡ ዓለም ስልጣኔ ወድቆ መሪነቱን ኡማችን በአስር ወይም ሀምሳ ዓመት ውስጥ ይቆጣጠራል ማለት ላይሆን ይችላል፡፡

ስልጣኔ አራት አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች ያሹታል፡፡

1) የፖለቲካ ንቃት እና ዘዴ
2) የምጡቅ ስነ-ምግባራት ባህል መዳበር
3) የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ማደግ እና
4) ጥበብ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ለስልጣኔ መፋፋት ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ የኢኮኖሚ ማደግ ስነ- አዕምሮአዊ ገዢዎች ለምሳሌ ሀይማኖት፣ባህል ቋንቋ እና ትምህርት ይገኙበታል፡፡

እንግዲህ የኢስላም ስልጣኔ ከሁሉም ለየት የሚያደርገው ዓለማቀፋዊነቱ ነው፡ ፡ መልዕክተ-ኢስላም ለሰብዓዊ ፍጡራን በሙሉ የተቸረ አምላካዊ ስጦታ ነው፡፡ ባለፉት ክ/ዘመናት የተፅዕኖውን በትር አሳርፏል፡፡ ምናልባት ዛሬም ዳግም ቢያንሰራራ ለሰው ልጆች ላቅ ያለ ጠቀሜታ አለው፡፡ከኢስላማዊው ስልጣኔ በፊት የነበሩት እንዲሁም ከበስተኋላው ብቅ ያሉ ስልጣኔዎች ቢኖሩም አይስተካከሉትም፡፡[12]

## የኢስላም ስልጣኔ እጅግ አስፈላጊ እና መስህብ የሚያደርጉትን ነጥቦች እስቲ እንይ

***ሀ/ መሰረቱ አምላክነትን ለአንዱ ፈጣሪ መስጠት ነው፡፡***

---

[12] ማን ረዋኢዒ ሐዳረቲና –ዶክተር ሞስጠፋ አስ–ሲባዒ

አንድን አምላክ አምልኩ፤ ጣዖታትና ምስሎች አይጠቅሙም ያለ ብቸኛው ስልጣኔ ነው፡፡

فَاعْلَمْ أَنَّهُ لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ وَاسْتَغْفِرْ لِذَنبِكَ وَلِلْمُؤْمِنِينَ وَالْمُؤْمِنَاتِ وَاللَّهُ يَعْلَمُ مُتَقَلَّبَكُمْ وَمَثْوَاكُمْ

***«እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም ዕወቅ፡፡ ስለ ስህተትህም ለምእመናንም ምሕረትን ለምን፡፡ አላህም መዘዋወሪያችሁን ፣ መርጊያችሁንም ያውቃል፡፡» ሙሀመድ 19***

ፍጡራን ፍጡራንን ከማምለክ ወደ ፈጣሪ አጎብዳጅ ይሆኑ ዘንድ የተጣራ ብቸኛ ስልጣኔ ነው፡፡ አምልኮን ለአላህ ብቻ ያደረጉ አህዳውያን ታዲያ በስልጣኔው ህገ-ስርዓት ፣በአጠቃላይ መርሆቻቸው በሰብዓዊነት እና በህይወት መንገድ እሴቶች ላይ አንድነት ይታይባቸዋል፡፡

ለ/ **ዓለማቀፋዊ (universal) እና ሰብዓዊ ፍጡርን በሙሉ ያካተተ ነው፡፡**

የኢስላማዊው ስልጣኔ ዋና ግብ የሠው ልጆች የሁለት ዓለማት ስኬታማነት ነው፡፡ሰው ሰው ስለሆነ ብቻ ክብርን የቸረ ብቸኛ ስልጣኔ ነው፡፡ ሌሎች ስልጣኔዎችን ስናይ በባርነት ቀንበር ከብዙ የህብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ ሰዎችን አንገላትተዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ ሴቶችን ከስሜት ማርኪያነት እና ከውበት በስተጀርባ ከተደበቀ ዓላማ ማሳኪያነት በተጨማሪ ሚና ቢስ አድርገው አልፈዋል፡፡

ቁርአን በሰው ልጆች መሀል ምን ያህል በቀለም ፣ በዘር ሀረግ፣ እና ቋንቋ ልዩነት ቢኖርም አንድ እንዲሆኑ አውጇል፡፡

ٰا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَى وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌالحجرات: ١٣

***‹‹እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡>> አል-ሁጁራት 13***

ኢስላም ይህን ዓለማቀፋዊ አንድነት ሲያውጅ ሁሉም የህሊና ምጥቀት ባለቤት የሆኑ የየትኛውም ዓለም ነዋሪዎች ለዚህች ምድር የአዕምሮ ፍሬ አበርክቶ እንዲያደርጉ ይጋብዛል፡፡ ለምሳሌ ያህል ከሁሉም ሀገር ብቅ ያሉ ነፀብራቆች የሆኑት ሙስሊም ሊቃውንት (scholars) ሻፊዒ ፣ ማሊኪ ፣ ሀነፊ ፤ገዛሊ እና ሌሎችም ለሰው ልጆች በሙሉ የህይወት ስንቅ ያስታጠቁ ጀግኖች ናቸው፡፡ የእነሱ የትውልድ መንደር ህዝብ ብቻ ሳይሆን የሚኮራባቸው ዓለማቀፋዊው የኡማው ስልጣኔ አባል በሙሉ ነው የሚኮራው፡፡

***ሐ/ ከንፁህ ምንጭ ዕውቀትን መቅሰም ያበረታታል፡፡***

ዕውቀት የስልጣኔ መገለጫ ብቻ ሳይሆን ለስልጣኔ መሰላልም ግብዓትም ነው፡ ፡ ኢስላማዊው ስልጣኔ ዕውቀትን ከተግባር ያማከለ ነው፡፡ ሴትንም ይሁን ወንድን በሁሉም የዓለም አቅጣጫ ያሉ አማንያን ላይ ዕውቀት ፍለጋን ግዴታ ያደረገ ብቸኛ ሀይማኖት ኢስላም ብቻ ነው፡፡ በታሪካዊው የኢስላም ስልጣኔ ከባግዳድ ፣ ደማስቆ ፣ ካይሮ እና ኮርዶቫ መስጂዶች ውስጥ የዕውቀት እንፅብራቂ ለመላው ዓለም ይበራ ነበር፡፡ ኢስላማዊው ዕውቀት ገዢን ከተገዢ ፣ ባሪያን ከአሳዳሪ ሳይለይ በእኩልነት የሚሰጥ ሲሆን ፤ ሚስጥር ተብሎ መሪዎች ጋር የሚደበቅ የለም፡፡ኢስላማዊው ስልጣኔ ለየት የሚያደርገው ሌላው ገፅታ ከአንድ ሀይማኖት ስር ያለ ቢሆንም ለሁሉም እምነት ተከታዮች ጠቃሚነቱ ነው፡፡ ታዲያ ሙስሊሙ ወጣት ከውዳቂ የአምልኮት ተግባራት

ርቆ ራሱን ለበላዩ ገዢ ካሰረከበ እና ካሳደረ በኋላ ይህን አቋሙን እንዳጠነከረ መዝለቅ ይጠበቅበታል፡፡ በእምነቱ ጉዳይ ሊደራደር እና ሊፈራ አይገባም፡፡ በእምነት (ዐቂዳ) ጉዳይ ላይ ፈሳሽ ሲያገኙ ፈሳሽ ፤ ጠጣር ሲያዩ ጠጣር ፤ ጋዝ ሲያጋጥም መትነን ወላዋይነት ነው፡፡

ወጣት ሙስሊም በማህበራዊም ይሁን ስነ-ምግባራዊ ንቃቱ የላቀ ሰብዓዊነትን ፤ ሉላዊ እሳቤን ባህሪ መለያው ካደረገ ኢስላማዊው ስልጣኔ ደግሞ ይመለሳል፡፡

ወጣትነት ንፁህ ያልተበከለ አስተሳሰብ ፤ያልደከመ የአዕምሮ ብርታት ስላለው ዕውቀትን መፈለግ ፣ማወቅ መማር እና ማንበብ ደግሞ ለተሻለ ዘመን ተሻጋሪ ኢስላማዊ ስልጣኔ አስተዋፅኦ የላቀ ነው፡፡

## ወጣቱ በመንፈሳዊው ስልጣኔ ዘርፍ ከአሉባልታ እና ደረቅ ክርክር ወደ ታዛዥነት እና ተግባር

ኢስላማዊ መነቃቃት በወጣቱ ላይ ጌጥ ነው፡፡ ነገር ግን ከችኩልነት እና ከትዕግስት ማነስ የጠራ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ወጣትነት ለሁሉም ሁኔታ የተመቸ ስለሆነ ሙስሊሙ ወጣት ያገኘውን ፈረስ ሁሉ አገኘሁ ብሎ ከመጋለብ መጠንቀቅ አለበት፡፡ እነዚህ የአስተሳሰብ ፈረሶች በቁርአን እና ሀዲስ ልጓም በስተቀር ገደል ይከታሉ፡፡ ከፈረሶቹ መሀል

1) የምዕራቡ ዓለም የአስተሳሰብ ዘመቻ ሰለባነት
2) በሙቀት እና ግፊት የተሞሉ አካሄዶች
3) አስመሳይ ስውር ደባዎች እና
4) በቁርአን ፣ ሱና እና በበሳል ሙስሊም ምሁራን ምሪት ስር ያለው ፍኖት ናቸው፡

አሉባልታ ህንፃ አይገነባም፡፡ አዕምሮ አያነቃም፡፡ በሙስሊሞች መሀል መድሀኒት ያልተገኘለት ከባድ በሽታ ሆኗል፡፡ ወደ ምድር ወርዶ ሰዎችን ሊጠቅም የማይችል ፋይዳ ቢስ ተግባር ነው፡፡ ወጣቱ ሙስሊም የኢስላምን ዳግማዊ የስልጣኔ ዘውድ መድፋት የሚመኝ ከሆነ ይህን የአስተሳሰብ መስመር

ዳግም ማየት ፤ ብሎም በምርምርና በዕውቀት መነፅር መዳሰስ አለበት፡፡ ለአዋቂዎች እና ለኢስላማዊ መስክ ምሁራን ላቅ ያለ ክብር በመቸር ፣ የቸገረውን በመጠየቅ ሊያውቅ ይገባል፡፡

የሌሎችን ስህተት አፈንፍኖ በመፈለግ ለሌሎች ማሰራጨት ምድራዊ ቅሌት አኼራዊ እሳት ስለሆነ ወጣቱ ከነዚህ ርካሽ ተግባራት ራሱን ማቀብ አለበት፡፡ ደግሞ ማወቅ ያለብን ጉዳይ ስራን የሚሰራ እንጂ እጁን አጣጥፎ የተቀመጠ አይሳሳትም፡፡ ከተቀማጭ ጥረት አድራጊ በብዙ እጥፍ ያስከነዳል፡፡ በኢስላማዊ የአስተሳሰብ ሚዛን እዚህ ግቡ የማይባሉ ደቃቅ ነገሮችን መሰረታዊ ጉዳዮች ይመስል በነርሱ ላይ ጊዜን ሰጥቶ መነታረክ አዘቅት ውስጥ መግባት ነው፡፡ ክርክር በደረቁ ከሆነ ፋይዳው ልብን ማድረቅ ፣ወቅትን መግደል ብሎም ቁርኝትን እና ቅርርብን ማቆርፈድ ብቻ ሆኖ ይቀራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ በመልካም ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመፅሀፍ ባለቤቶችን (አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን) እንኳ ቢሆን እንዳንከራከር ይከለክለናል፡፡

وَلَا تُجَادِلُوا أَهْلَ الْكِتَابِ إِلَّا بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ العنكبوت: ٤٦

***«የመፅሀፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፡፡»* አል-ዐንከቡት: 46**

ነገር ግን እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ በሙስሊሞች መካከል ፍጥጫ ተፈጥሮ አንዳንዱ ተከራካሪ ነጭን ጥቁር ፣ሀሰትን እውነት ለማድረግ ሲጥር ይስተዋላል፡፡ በዚህ ዓይነት ውጥንቅጥ ውስጥ መሳተፍ ታዲያ ከሚከተለው የቁርአን አንቀፅ መልዕክት ስር ያስጠልላል፡-

وَجَادَلُوا بِالْبَاطِلِ لِيُدْحِضُوا بِهِ الْحَقَّ

***«...... በውሸትም በርሱ እውነት ሊያጠፉ በትተከራከሩ፡፡ጋፊር 5***

ሙስሊሙ ኡማ ቢያንስ አንድ የሚያደርጉት መሰረታዊ የሀይማኖቱ ክፍሎች አሉ፡፡ እነርሱ በቂ ናቸው፡፡ በማይረቡ ነገሮች ተከራክረን እና ተቃቅረን መድረስ ካለብን መስከ ሳንደርስ በአጭር መቅረት የለብንም፡፡

ቀደምት ሙስሊሞች ኢስላማዊ መልዕክትን የበተኑት በአሉባልታ አሊያም ደረቅ ክርክር ሳይሆን በመልካም ስነ-ምግባር ፣ለሰዎች ጥሩን በመመኘት እና ከተንኮላቸው በመያዝ ነበር፡፡ ይህን ሁኔታ ሲያዩ ታዲያ ሰዎች ወደዱዋቸው ፤ ተሻግረው በዚህ መልኩ የቀረፃቸውን የህይወት መንገድ ወደዱት፡፡ ወደ ኀራውም ያለማቅማማት ተቀላቀሉ፡፡

## ተግባር ይጣራል

ተግባር ከንግግር ይበልጥ ይሰማል፡፡ በአፍ ከሚነገሩ አንድ ሺህ ወሬዎች ፤ በተግባር የታየች አንዲት ስራ ለሰዎች ታላቅ ጥሪ ናት፡፡ ንግግር ከተግባር ሲለያይ ደግሞ ከኢስላማዊው ስልጣኔ መሸሽያ መንገድ ነው፡፡

ስለዚህ ለኢስላማዊው ስልጣኔ ወጣቱ በተግባር ሲጣራ እንጂ ስላለፉ አባቶች እጁን አጣጥፎ ዝናቸውን ብቻ እያወራ ቢቀመጥ ትርፉ የተረት አባትነት እንጂ ተሀድሶ አይሆንም፡፡ ይህ ሲባል ግን ታሪኩን አይወቅ ፤ ከሰለፎች አስተምሮ አይውሰድ ለማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም በሸሪዓም ቢሆን በህሊና ፍርድ ታሪኩን ያላወቀ ፤ማንኛውም ላለበት እና የወደፊቱን ማቃናት አይችልም፡፡ ነገር ግን ባለፉ አባቶቹ የዝና ድንኳን ውስጥ የተወሸቀ "የነበርን" ተጠቂ ወጣት ኢስላም አይፈልግም፡፡አዎ ነበርን ዛሬም ነን የሚለውን ጀግና ወጣት ግን ያበረታታል፡፡ ቀዝቅዞ ወደ ድንጋይነት የተቀየረ አመድ ትላንት ፍም ነበርኩ ቢል ምን ፋይዳ አለው?!

በስብሶ የተፈረፈረ አጥንት ትላንት የሚያምር የገላ ስጋን ተሸክሜ ነበር ቢል ምን ሊጠቅመው?!

## ተፈላጊው ተግባር እና ሥራ

ጭንቀቱ እና ልፋቱ ስራው አይደለም፡፡ ነገር ግን ስራውን ምጡቅ ማድረጉ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ወጣቱ በዚህ መልኩ ሊረዳው ይገባል፡፡ ኢስላማዊውን ስራ ሴቱም ፣ ወንዱም ፣ አረጋውያኑም ፣ ወጣቱም ይሰራዋል፡፡ ቢሆንም ግን ከወጣቱ የሚጠበቀው ስራውን በተሻለ ሁኔታ መስራት ነው፡፡ ቅደም ተከተሎችን ተከትለን ሁሉንም የስጣኔዎቻችንን ትዕዛዝ እና ተግባራት ወቅታዊ አድርገን መተግበር አለብን፡፡ የማማራቸው የመስህብነታቸው ጉዳይ አጠያያቂ መሆን የለበትም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በሁሉም ነገር ምጡቅ ስራን ነው የሚወደው፡፡

ይህም ሲባል ግን በሁሉም መስክ ቢሆን ትእግስትን ትልቁ የጉዞ አጋር ማድረግ ግዴታ ነው፡፡ አንዳንዴ ወጣቱ ችኩልነት ይስተዋልበታል፡፡ ባብዛኛው ወጣት ዛሬ የዘራውን ከሳምንት አሊያም ወር በኋላ ማጨድ ያሻል፡፡ በዳዕዋው ዘርፍ በአንድ ጀንበር ተቀይሮ ተጠሪን ማየት ከባድ ነው፡፡ የትምህርቱ ተፅዕኖ ከቀን ወደ ቀን የወንጀልን እና አጉል ትዕቢተኝነት የበረዶ ግግር በጥበብ ሲያቀልጠው እንጂ ምናልባት ተውፊቅን አላህ ካልሰጠን ችግር ነው፡፡

## የእንቅልፍ ጊዜ አከትሟል

ተፈጥሮአዊው እንቅልፍ የአላህ ፀጋ ነው፡፡ ከ24 ሰዓት ውስጥ ጨለማው ክፍል ለሰው ልጅ የእረፍት እና አምልኮ ጊዜ ይሆን ዘንድ አላህ (ሱ.ወ) በጥበቡ ልባስ አድርጎታል፡፡

وَجَعَلْنَا نَوْمَكُمْ سُبَاتًا * وَجَعَلْنَا اللَّيْلَ لِبَاسًا النبأ: ٩ – ١٠

***«እንቅልፋችሁንም ዕረፍት አደረግን፡፡ ለሊቱንም ልባስ አደረግን፡፡» አን-ነበእ 9-10***

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኡማ በተለይ ወጣቱ ክፍል የትልቅ አደራ ተሸካሚ ነው፡፡ ሰማያት ምድር እና ተራሮች አልችል ብለው ያልተቀበሉትን ከባድ አደራ የሰው ልጅ ይከበደውም ይቅለለው ትከሻው ላይ አድርጓል፡፡

إِنَّا عَرَضْنَا الْأَمَانَةَ عَلَى السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَالْجِبَالِ فَأَبَيْنَ أَن يَحْمِلْنَهَا وَأَشْفَقْنَ مِنْهَا وَحَمَلَهَا الْإِنسَانُ إِنَّهُ كَانَ ظَلُومًا جَهُولًا

*‹‹እኛ አደራን በሰማያትና በምድር በተራራዎችም ላይ አቀረብናት መሸከሟንም እንቢ አሉ ፤ ከርሷም ፈሩ ሰውም ተሸከሟት ፣ እርሱ በጣም በደለኛ ተሳሳች ነውና፡፡››* **አልአህዛብ 72**

ምድራዊ ቆይታውን ለአምላኩ ፍላጎት ያሳደረ ወጣት የምን የዝንጋቴ ዝቅጠት ውስጥ ይገባል?! ከእምነቱ ተቃራኒዎች እና ጠላቶቹ ጋር የምን መላላስ?!

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَتَّخِذُوا عَدُوِّي وَعَدُوَّكُمْ أَوْلِيَاء تُلْقُونَ إِلَيْهِم بِالْمَوَدَّةِ وَقَدْ كَفَرُوا بِمَا جَاءكُم مِّنَ الْحَقِّ يُخْرِجُونَ الرَّسُولَ وَإِيَّاكُمْ أَن تُؤْمِنُوا بِاللَّهِ رَبِّكُمْ إِن كُنتُمْ خَرَجْتُمْ جِهَادًا فِي سَبِيلِي وَابْتِغَاء مَرْضَاتِي تُسِرُّونَ إِلَيْهِم بِالْمَوَدَّةِ وَأَنَا أَعْلَمُ بِمَا أَخْفَيْتُمْ وَمَا أَعْلَنتُمْ وَمَن يَفْعَلْهُ مِنكُمْ فَقَدْ ضَلَّ سَوَاء السَّبِيلِ

*‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ጠላቶቼንና ጠላቶቻችሁን ወዳጅ ኣድርጋችሁ ኣትያዙ፡፡ከእውነቱ የመጣላችሁን ሀይማኖት በእርግጥ የካዱ ሲኾኑ ውዴታን ወደነርሱ ታደርሳላችሁ መልዕክተኛውንና እናንተን በአላህ በጌታችሁ ስላመናችሁ (ከመካ) ያወጣሉ በመንገዴ ለመታገልና ውዴታዬን ለመፈለግ የወጣችሁ እንደኾናችሁ (ወዳጆች ኣድርጋችሁ ኣትያዙዋቸው) እኔ የምትደብቁትንና የምትግልጹትን ሁሉ የማውቅ ሲኾን ወደነርሱ በፍቅር*

*ትመሳጠራላችሁ ከናንተም (ይህንን) የሚሰራው ሰው ቀጥተኛውን መንገድ በእርግጥ ተሳሳተ፡፡» አል ሙምተሂናህ 1*

ለተራ እና የጤዛ ዕድሜ ላላቸው አመለካከቶች እና ዕይታዎች አያድርም፡፡ ለምዕራቡ ሰራሽ ስርዓቶች አይን በረከክም፡፡ በየቦታው ያሉ የሙስሊም ወገኖቹ ደም እንቅልፍ ይነሳዋል፡፡ በየቀኑ የሚረግፉ ህፃናት ሁኔታ ያንገበግበዋል፡፡

ጠንቃቃ ፣ ብልህ እና አሳቢ ሙስሊም ወጣት የኢስላም ካስማ ተነቅሎ እየተሰበረ ፤ ድሎትን በመከጀል ከፍራሽ ጋር የሚገናኝ ጎን የለውም፡፡ ከስምጥ ዝንጋቴ ውስጥ ለሌሎች ንቃተ-ህሊና ይተጋል፡፡ በዐቂዳ የሸበረቀ ማህበረሰብ ይናፍቃል፡፡ ጥልቅ የቅዠት ዓለም ውስጥ ገብቶ ከመዋዠቅ ደግሞ ተንቀሳቅሶ ውጤቱን ሊያገኘውም ፤ አሊያም ደግሞ ትውልድ ምርቱን ይሰበስብ ዘንድ ጥሎ ያልፋል፡፡

እንጂ ምርጥ ህዝብ ፣ የምርጥ ነብይ ተከታ ይሆነን እና ልፋት የሚከጀል ዲን ይዘን የዝንጋቴን ምንጣፍ ማንጠፍ ከእኛ ሙስሊም ወጣቶች አይጠበቅም፡፡ ምክንያቱም የዓለም የጎደፈ እና የቆሸሸ እኩይ ገፅታ የመቀየሩ ኃላፊነት የማንም ሳይሆን የኡማው ፅጌረዳዎች በሆኑት ወጣቶች ነው፡፡ ከነፍስ እና ቤተሰብ ጀምሮ እስከ ዓለም ለውጥን በማንገብ ለስልጣኔው መሳካት ወጣቱ ሚናው የጎላ ነው፡፡

## ወጣቱ ከድንበር ማለፍ እና ፅንፈኝነት ወደ ሚዛናዊ ዕይታ

ኢስላማዊ እምነትና አመለካከት ዕንቁ አበይት ባህሪያት አሉት፡፡ አንደኛውና ዋነኛው ሚዛናዊነት ሲሆን ይህ ባህሪ የእምነቱም የኡማውም አብይ መገለጫ እንደሆነ ቁርአን ያስተምራል፡፡

وَكَذَلِكَ جَعَلْنَاكُمْ أُمَّةً وَسَطًا لِّتَكُونُواْ شُهَدَاء عَلَى النَّاسِ وَيَكُونَ الرَّسُولُ عَلَيْكُمْ شَهِيدًا

***«እንደዚሁ እናንተን በሰዎች ላይ መስካሪዎች ልትሆኑና መልዕክተኛውም በናንተ ላይ መስካሪ ይሆን ዘንድ መካከለኛና ሚዛናዊ ህዝብ አደረግናችሁ፡፡» (አል-በቀራ 143)***

ወሰጥያ በሁለት ጠርዞች ወይም ጫፎች መሀል የሚገኝ ማዕከላዊና ፍትሀዊ የአስተሳሰብ አቅጣጫ ነው፡፡ ድንበር ማለፍ እና ፅንፈኝነትን በተመለከተ ነብያዊው አንደበት በሀይማኖት ድንበር ማለፍን (እንዳትቀርቡ) አደራ ፡፡ ከናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦችን ድንበር ማለፍ ነው ያጠፋቸው፡፡ (ሷሂህ አልጃሚዕ) ይላል፡፡

ስለዚህ ወጣቱ ከጠቆረ እና መንገድ ካሳተ ጭፍንነት ራሱን መጠበቅ አለበት፡፡ አንዳንዴ ከአጉል ችኩልነት እና ራስን ከፍ ያለ ግምት በመቸር ሁሉም ጃሂል...... ነባራዊ የህይወት ጉዞ በሙሉ ሰዎች በሙሉ ከሀዲና ሙናፊቆች ብሎም ወንጀለኛ ብሎ እስከማሰብ የሚያደርስ ክፉ በሽታ ነው፡፡ ኢስላም እንደ ተፈጥሮ ሀይማኖትቱ ለሰው ልጆች የህይወት መንገድ ሆኖ ሲደነግግ ፍላጎት እና ሚናቸውን ወደ ተሻለ እርከን ላይ ለማድረስ ነው፡፡ መሰረታዊ የሆኑ ምሰሶዎች ሲኖሩት መተግበሩ ግዴታ ነው፡፡

## ኢስላምን እንደ ጠባብ ጎጆ

ኢስላም ቅዱስ ስፍራ ነው፡፡ አፀዱ የፍሰሀ ምንጭ ጥልቅ ስፋት ያለው የደስታ እልፍኝ ፡፡ ሁሉንም ዓይነት ሰዎች ምንም ያህል በአስተሳሰብ እና እይታ ቢለያዩ በስሩ ያስጠልላል፡፡ ይህ ከልዩ እና ድንቅ ባህሪያቱ ዋነኛው ነው፡፡ በሀይማኖቱ የአስተሳሰብ ምህዋሮች የምልከታ መነፅሮችና የምርምር ውጤቶች

የተለያዩ ናቸው፡፡ ነገሩ ላም ከጋቷ በብዙ የጡት ጉጦች ውስጥ ወተት ነው የሚወጣው፡፡ አንድን አስተሳሰብ በቁርአንና ሀዲስ ጥላ ስር ተገምግሞ ሚዛኑ ከደፋ መቀበል አይከፋም፡፡ መሰረታዊ ባልሆኑ ጉዳዬች ለማለት ነው፡፡ ነገር ግን በዐቂዳ አይነኬ መሰረቶች ላይ ግድፈት የታየበትን ግለሰብ፣ ማህበረሰብ እና ሀገር ፅንፍ ሳያልፍ ዲኑን እንደ ጠባብ መፈናፈኛ የሌላት ጎጆ ሳያስመስሉ ማስተማር ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡

ስለዚህ ሙስሊም ወጣት የአስተሳሰብ መሞከሪያ የላብራቶሪ ዕቃ ከመሆን እና ከጭፍን ወገንተኝነት በፀዳ መልኩ ሀቅን ሊያውቅ ይገባል፡፡ ሀቅ ሰዎችን ይለካል እንጂ ሰዎች ሀቅን አይለኩትም፡፡ምክንያቱም

الْحَقُّ مِن رَّبِّكَ فَلاَ تَكُن مِّنَ الْمُمْتَرِينَ

***«ይህ ከጌታህ ዘንድ የኾነ እውነት ነው፡፡ ከተጠራጣሪዎቹም አትኹን፡፡>> አል-ዒምራን 60***

ዓሊይ ኢብን አቡጧሊብ (ረ.ዐ) «ሀቅን ብቻ ዕወቅ፡፡ ሰዎችን በሀቅ እንጂ፤ በሰዎች ሀቅን አትለካ፡፡ ሀቅን ካወቅክ ሰዎችንም ታውቃለህ፡፡»

ሀቅ ባልደረቦቿ ድንበር አላፊና ፅንፈኞች አይደሉም፡፡ በሀሳብ የተቃረናቸውን ሁሉ በሌላ የሚወርፉ ወገኖች እንኳን ለሀቅ ሊቆሙ ቀርቶ እጅግ ርቀውታል፡፡ ቁርአን በየትኛውም መልኩ ድንበር ማለፍን ከልክሏል፡፡ የመፅሀፍ ባለቤቶችን ይርቁ ዘንድ አስጠንቅቆታል፡፡

ከኢስላም ጥላ ስር ውጭ ያሉ ወገኖችን በዚህ የገሰፀ ሙስሊሙን ኡማስ !

አዎ መካከለኛ ህዝብ ናችሁ ሲል አላህ አሞግሶታል፡፡ ነብያዊ አንደበት ዳግም ላይነሳ ቀብሮታል፡፡ «አጥባቂዎች እና ወገኞች ጠፉ» ሲሉ ዓብደላህ ኢብኑ መስዑድ አስተላልፈዋል፡፡

## መሰረታዊ እሴቶች

መሰረታዊ የኢስላምና ኢማን እሴቶች በአንድ ላይ እንደሚታወቁት አስራ አንድ ናቸው፡፡

1) የምስክርነት ቃላት (ሸሀደተይን)
2) ሶላትን መስገድ
3) ዘካን መስጠት
4) የረመዷን ወር መፆም
5) አቅምና ችሎታ ያለው የአላህን ቤት መጎብኘትና(ሀጅ) የሚሉት የኢስላም መሰረቶች ሲሆኑ እያንዳንዱ ሙስሊም ሊተገብራቸውና በኢስላም ድንበር ለመግባት የሚያሟላቸው ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የኢማን ሲሆኑ

1) በአላህ ማመን
2) በመላእክት ማመን
3) በሰማያዊ መፅሀፍት ማመን
4) በመልዕክተኞች ማመን
5) በመጨረሻው ቀነ-ቀጠሮ ማመን እና
6) በአላህ ውሳኔዎች ደግሞ መልካም ይሁኑ ክፉ አምኖ መቀበል ሲሆኑ፤ እነዚህ ደግሞ የምሉዕ ኢማን እሴቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ከላይ ያየናቸው አስራ አንድ መሰረታዊ እሴቶች አንድን ሰው ሙሉ ሙስሊም ያደርጉታል፡፡

## ታዲያ ክፍተቱ የት ነው?

ከላይ ያየናቸውን መሰረታዊ ነገሮች ችላ በማለት ጥቃቅንና እዚህ ግባ የማይባሉ ቅርንጫፍ ነገሮች ላይ ማተኮር አንዳንድ ወጣቶች ላይ ይስተዋላል፡፡ ይህ ትልቅ ስህተት ከመሆኑ ጋር ቅርንጫፍ ጉዳዩች ላይ ማተኮር የሚከተሉት መዘዞች አሉት፡፡

## ቁርአንና ሀዲስን መጣረስ ነው

ሀያ ሦስት ዓመታትን ፈጅቶ በመልዕክተኛው ላይ አላህ ያወረደውን ተዓምራዊ መፅሀፍ መፃረር ነው፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በመካዊው ዘመናቸው ቁርአን መሰረታዊ የኢስላም መቅኒዎችን ነበር ሲያብራራ የነበረው፡፡ ዐቂዳንና አኽላቅን፤ ተግባርንና ኢኽላስን፡፡ እነዚህን እሴቶች በነፍሶችና አዕምሮዎች ላይ ተከላቸው፡፡ ነብዩም(ሰ.ዐ.ወ) ታዲያ በዚህኛው እርከን የተከተሏቸውን ሰዎች ርዕዮት ስነ-ምግባርና የአካሄድ ድክመት አርቀዋል፡፡ አስተሳሰብና ተግባር ገርተዋል፡፡

የመዲናው ዘመናቸው ግን በአብዛኛው የህግጋት እና ድንጋጌዎች ነበር፡፡ ቁርአን ያመኑ ሰዎችን እያቀማጠለ በመጥራት ከእኩይ አቀበ፤በሰናይ አዘዘ፡፡

ባሉበት የስደት ሕይወት ላይ ሆነው ምድርን የማስተዳደርና ማሳመር ኃላፊነት እንዳለባቸው አስገነዘባቸው፡፡

ይህን ነው እንግዲህ የኢስላም ታሪክ የሚያሳየን፡፡ ቁርአንና ሀዲስ በዚህ መልኩ ከነበሩ ያንን ትውልድ ያስተካከሉት ለምን ዛሬ ታዲያ ከመሰረታዊ ነገሮች ይልቅ ቅርንጫፎቹ ላይ አተኮርን ተነታረክን ተራራቅን፡፡

## ጥቃቅንና ቅርጫፍ ጉዳዮች ማብቂያ የላቸውም፡፡

እጅግ በጣም ብዙ ናቸው፡፡ ማለቂያ የሚባል ነገር የላቸውም፡፡ራሱን በነርሱ የወጠረ በርግጥም ተሞኝቷል፡፡ ወቅትና ጊዜውን አውድሟል፡፡ የአካልን የአስተሳሰብና ነፍሱን ሀይል አባክኗል፡፡ የሰው ልጅ ደግሞ ያለምንም ጥርጥር አቅሙ ደካማ ነው፡፡

በምንም ዓይነት ሚዛን ቅርንጫፍና ጥቃቅን ጉዳዮች መሰረታዊ እሴት አይሆኑም፡፡ ለመሆንም አቅም የላቸውም፡፡ስብዕናዎች በፈጠራ (ቢድዓ) ላይ ተሰማርተው በነርሱ በተነታረኩ ቁጥር የሱናዎችም ፋናነ ያጠፋሉ ፡፡

በወጣትነት ታዲያ ለምን ይህን የአትኩሮት አቅጣጫችን የማናስተካክለው?

## *እነዚህ ቅርንጫፍ ጉዳዮች በአብዛኛው የልዩነት ጥላ ያጠላባቸው ናቸው፡፡*

አጥባቂና አግራሪ ልዩነቶች አሏቸው፡፡ ኺላፍ የሚስተዋልባቸውን ጉዳዮች አግራርተው የሚያልፉ ዓሊሞች እንዳሉ ሁሉ አጠባብቀው የሚሄዱም አይጠፉም፡፡ በተከታይ ህዝብ መሀል ግን ለምን ይሆን መራራቅ፣ መጠላላት መተቻቸትና አለመግባባት የሚፈጠረው?ዓሊሞቹ ከተለያየ የአስተሳሰብ መስመር ይውጡ፡፡ የኢስላም ልጆች ናቸው፡፡ በጥቃቅን ልዩነት የነርሱን ብያኔ ይዞ የሚጓዝና ሌሎችን አፈር የሚደባልቅ ሰው አለ፡፡ ይህ ለምን ሆነ? ሚዛናዊነት ማንን ይጎዳል? የኢስላማዊው ንቃት ልጆች ውስጥ ከፍተኛ ክፍተት በመፍጠር ጥላቻን ማትረፍ የታየ ውጤት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ዲንን ያጠፋል፡፡

ሙጅተሂድ (የመስኩ ተመራማሪና አዋቂ) የተመራመረበትን ጉዳይ ካገኘ ሁለት ምንዳዎች፤ካላገኘ አንድ ምንዳ አለው፡፡ ተከታዩ ህዝብ ግን በተሰጠው የራሴ የሚለው አዋቂ ብያኔ መስመር ያልገባለትን በሙሉ ይጠላል፡፡ ይህ አግባብ አይደለም፡፡የልዩነትን ስርዓት ይፃረራል፡፡ልዩነት ሁሌም ይኖራል፡፡ነገር ግን የልዩነት አንድነትን መገንባት ይቻላል፡፡

የሁሉንም ሀሳብ አንድ ማድረግ ከባድ ነው፡፡ በአጠቃላይ ኡመተል-ኢስላም እጅግ በጣም ሊያስጨንቀውና ሊያስቀድመው የሚገባው ነገር ግዴታና መሰረታዊ የሆኑ እሴቶችን ነው፡፡ በአብዛኛው ዲን ቀመስ ወጣት ላይ ከሚታዩት ግድፈቶች ዋነኛው ስለሆነ ነው ያተኮርንበት፡፡ ቀደምት ሰለፎች እንዲህ ይላሉ፡- *«ሱና (ተጨማሪ) አምልኮዎችን ላለመስራት ግዴታዎቹ ያጨናነቁት ምክንያታዊ ነው፡፡ ተጨማሪ (ሱና) ተግባራት ከግዴታው ያዘናጉት ደግሞ ቂል ነው፡፡»* ለምሳሌ ያህል አንድ ወጣት ሙስሊም ዚክርና፣ ተስቢህ ዱዓና ተልቢያን ጠብቆ ጠዋትና ማታ ሊል ይችላል፡፡ ቀንቶት ደግሞ ሀጅና ዑምራ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን በተመሳሳይ ሁኔታ ይህ ወጣት የወላጆቹን ሀቅ ያጓድላል፡፡ ዝምድናውን ይቆርጣል፡፡ጎረቤቶቹን ይጎረብጣል፡፡ ሌደራውን ያጎድላል፡፡ የሚያገኘው ገንዘብ ከሀራም ነው፡፡ አምታች የሆኑ ጉዳዮች አይርቅም፡፡ሙስና ባህሪው ሆኗል፡፡ ለወለድ ግዴለሽ ነው፡፡ ሙስሊም ወንድሞችን በመጫረት ይጎዳቸዋል፡፡ ይህ ነው እንግዲህ ዲንን በመረዳቱ ሁኔታ ላይ ክፍተት የሚሰኘው፡፡መቅደም የሚገባውን ወደ ጎን ትቶ

የማይቀድመውን ማሽጋሸግ ማለት ይህ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የተጠላ ነው፡፡ ለዚህ ነው ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ለአንዷት ሴት ባሏ መንገድ ሳይወጣ የሱና ፆም መፆምን የጠሉት፡፡ አዎ! ምክንያቱም የባል ሀቅ ከሱና ፆሙ እጅግ ይበልጣል፡፡ የእርሷ ምንነት ባልን ከሀራም ስለሚጠብቀውና ጋሻ ስለሚሆንለት ያለርሱ ፈቃድ መፆም አትችልም፡፡

## የኢስላምን ባህሪ አለመረዳት ነው

ኢስላም ከሌሎች እምነቶችና አስተሳሰቦች አበይት ባህሪያት አሉት፡፡ ባህሪያቱ ከሰው ልጅ ህሊናዊ፣ስነ-ልቦናዊና አካላዊ አወቃቀሩ ጋር የተሳፉ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) የሰውን ልጅ በሚገባ ስለሚያውቀው የሚበጀውን ፍኖት መርጦለታል፡፡

ከነዚህም መሓል ሶስቱን በዋናነት እናነሳቸዋል

### *ሀ) መለኮታዊነት*

መለኮታዊነት የኢስላማዊው ጎዳና የመጀመሪያ መገለጫ ባህሪይ ነው፡፡ የሌሎች ባህሪያቱም መነሻም ይኸው ባህሪ ነው፡፡ "ኢስላም በዓለም ውስጥ ካልተለወጠ እና ካልተበረዘ በሰዎች ከንቱ ሃሳብ ካልተላበሰ ፣ ከስህተታቸው ጋር ካልተቀላቀለ የራዕይ ምንጭ የሚፈልቅ ብቸኛው የህይወት ስርዓት ነው፡፡ ምክንያቱም አሏህ ህጎቹ በሙሉ መሠረት የሆነውን መፅሀፉን ቅዱሱን ቁርዓን የመጠበቁን ሀላፊነት እርሱ ወስዷል፡፡

### *ለ) ሁለንተናዊነት*

"ሁለንተናዊነት ኢስላም ሰዎች ከሚያውቋቸው ሀይማኖቶች ፣ ፍልስናዎች ፣ አመለካከቶች . . . የሚለይበት ባህሪው ነው፡፡ "ሁለንተናዊ" የሚለው ቃል ሊገልፀው በሚችለው ትርጉም እና በሙሉ ጥልቀቱ ልክ ኢስላም ሁለንተናዊ ነው፡፡ ኢስላም አጠቃላይ ነው ዘመንን ፣ ህይወትን እና የሰውን ልጅ ሁለመና ያጠቃልላል፡፡ ይህንን የኢስላም መልእክት ውስጥ ያለውን ሁለንተናዊነት ጥልቀት ሸሂድ ሐሰኑል በና እንዲህ አድርገው አሳምረው ገልፀውታል፡፡ "የኢስላም መልእክት የዘመን ርዝመትን አሻቅቦ ወጥቶ ዘልዓለምን ያካተተ

ነው፡፡ በአግድመት ተጉዞ የህዝቦችን አፅያፊ ያደረሰ ነው፡፡ በጥልቀት ሰርጎም የዱንያም ሆነ የአኼራን ጉዳዮች የጠቀለለ ነው፡፡”

ወደዚህ ሁለንተናዊነት እና የኢስላም አስተምህሮዎች ትስስር ኡስታዝ ሐሰኑል በና ወንድሞቻቸውን ጠርተዋል፡፡ እንዲህ ይላሉ ፡- “ኢስላም ሁለንተናዊ ስርዓት ነው የህይወት ገፅታዎችን በሙሉ ያካትታል፡፡ እርሱ መንግስት ነው ፤ ሀገርም ነው፡፡ እርሱ አስተዳደርም ፤ ህዝብም ነው፡፡ እርሱ ስነምግባርም ሀይልም ነው፡፡ እዝነትም ፍትህም ነው፡፡ እርሱ ስልጣኔም ህግም ነው፡፡ እውቀትም ዳኝነትም ነው፡፡ እርሱ ንዋይም ሀብትም ነው፡፡ ሥራም ሐብት

ነው፡፡ እርሱ ትግልም ጥሪም ነው፡፡ እንዲሁም ሰራዊትም ሃሳብም ነው፡፡ ይህም እውነተኛ እምነት ፣ ትክክለኛ አምልኮ ከመሆኑ ጋር በምንም ሳይነጣጠል ነው፡፡” ሪሳለቱ ተዓሊም ፣ ሺሂድ ሐሰኑል በና፡፡

### ሐ)ሚዛናዊነት

መካከለኛ ስንል ሁለት ተቃራኒዎን የሚያቀራርብ እና የሚያስታርቅ አንዱ ሃሳብ ተቃራኒውን አስወግዶ ብቻውን ተፅእኖ ፈጣሪ እንዳይሆን የሚያዋህድ ማለት ነው፡፡አንዱ የሃሳብ ጫፍ ከሐቁ እና ከመብቱ በላይ ሌላው ጫፍ ላይ ወሰን እንዳያልፍ የሚያደርግ ማለት ነው፡፡ መንፈሳዊነት እና ቁሳዊነትን፣ ግለሰባዊነትና ማህበራዊነትን ፣ ተጨባጫዊነትንና ተምሳሌታዊነትን፣ አይለወጣዊነትንና ተለዋዋጭነትን የመሳሰሉ ተቃራኒ እና ትይዩ ሃሳቦችን ምሳሌ ማንሳት እንችላለን፡፡ ሚዛናዊነት ማለት ለሁሉም የሃሳብ ጫፍ የራሱን ሚና እንዲጫወት የሚያስችል ሥፍራን መተው ነው፡፡ ስለዚህ የራሱ መብት የሆነው በሚመጥነው ያህል ይሰጠዋል፡፡ በትክክለኛ ሚዛን ተለክቶ ያደረገውን ያገኛል፡፡ አይቀነስበትም፡፡ ድንበር ታልፎም አይጋነንም፣አይጓደልበትም ከልኩም አያልፍም፡፡

ከላይ ያሉትን የኢስላም ባህሪያት በጥልቀት የተረዱ ወጣቶች በስድስቱ የኢማንና አምስቱ የኢስላም መሰረቶች ክቡር ስነ-ምግባራት ላይ የግዴታ ተግባራት እና እቀባዎች በማተኮር ኡማውን ወደፊት ባሉ እርከኖች ማነፅ

እንጂ፤ምንም ሀ ሁ በማያውቀው ህብረተሰብ ውስጥ በመግባት ፣ በምንም መልኩ መሰረታዊ ሊሆኑ በማይችሉ ተልካሻ ጉዳዮች

- ጊዜን ማቃጠል
- ህብረትን መበተን
- ዑለማ መስደብና ማንቋሸሽ
- ለራስ ከፍተኛ ግምት መቸር
- ሌላውን በክህደትና ኒፋቅ ቀለም ማጥቆር
- የጠላት መዘባቻ መሆን
- የኢስላምን የበላይነት ስልጣኔ መቅበር

አግባብ ካለመሆኑ ጋር ከበድ ያለ ቅጣት በሁለቱም ዓለማት ያስከትላል፡፡

# 5

# ላለመድረስ

ዕድሜን በአግባቡ ላለመጠቀም ፈተናዎቹ ብዙ ናቸው፡፡ በተለይ ወጣቱን ፈላጊው እጅግ ብዙ ነው ፡፡ እስቲ ፍሬያማ፣ ስኬታማና ጠቃሚ ወጣት ላለማፍራት የተወደሩ እንቅፋቶች ምን እንደሆኑ ለማየት እንሞክር፡፡

## ሀ/ ሱስ

ህሊናን ለሱስ ካስገዙና ካስጎበደዱት የማሰብ ችሎታ ይቀንሳል፡፡ አዕምሮም ባዶ ቅል ይሆናል፡፡ ዛሬ ሱስና ዓይነቶቹ ወጣቱን በመረቡ ስር አስገብተዋል፡፡ እነዚህን ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ግልፅ የሆኑት ሱሶች ማንነትን ይሰልባሉ፡፡ ሀይልን ያሟሽሻሉ፤ ዕቅድ ያወድማሉ፤ ህልም ያጨናግፋሉ፡፡

በመላው ዓለም ላይ ተንሰራፍተዋል፡፡ በያዳንዱ ኪስና ቦርሳ ውስጥ የሱስ ፓኬቶች አሉ፡፡ ሽማግሌውና አዛውንቱ ሸብተውበት ይሞቱበታል፡፡ ወጣቱ ጎልምሶ ይጃጅበታል፡፡ አንዴ ከለመዱት ማንነትን ስለሚቆጣጠርና ለመንቀሳቀስ ስለሚከብድ መተው ያስቸግራል፡፡ ደምን ይዋሀዳል፡፡ ልቦናን ይቆጣጠራል፡፡ ነገር ግን ቆራጥ ሞራል ያለው ስብዕና በቀላሉ መላቀቅ ይችላል፡፡

አስካሪ መጠጥን የለመደ ወጣት ሳይጠጣ መንቀሳቀስ አይችልም፡፡ ቁማርን በአስካሪ መጠጥ ደጅ ያገኘዋል፡፡ የዳንስና ምሽት ክለቦች ደንበኛ ይሆናል፡፡የልቅ ወሲብን ሰፈፍ ይቋደስና በበሽታ ተለክፎ የሞትን ገፈት ቀምሶ ምድራዊ ህይወቱን በዜሮ ይሰናበታል፡፡

ሌላው ደግሞ ወጣቱ ከተጠመደበትና ከተደፈቀበት የሱስ ባህር ውስጥ ከባዱ ጫት መቃም ነው፡፡ ጫት መቃም ከጤናዊ ጉዳቶቹ በተጨማሪ ሞራላዊ ማህበራዊና ሀይማኖታዊ ብሎም ሀገራዊ ተፅዕኖን ያመጣል፡፡ ዜጎች አምራችና ጠቃሚ አይሆኑ ዘንድ ጫት ላይ በመቀመጥ የስራ ሰዓታት ይባክናሉ፡፡ ብዙ የአዕምሮ ችሎታዎች ይቃጠላሉ፡፡ የእብደት፤ መነጫነጭና

ሌሎችን አለማክበር፣ የቤተሰብ ሀቅን አለመጠበቅ፣ ወላጆችን መርሳትና ማህበረሰብን ማስቸገር ጫት መቃም ከሚያመጣቸው ድክመቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ወጣቱ ጫትን እስካልተወና ከሱስ ባርነት ቀንበር ራሱን ነፃ ካላወጣ ለኢስላም እና ለስልጣኔው ዳግም መልስ ሰራለሁ ማለት ዘበት ነው፡፡ ሰራ ቢባልም ተቀምጦ ከሚቅምበት ቦታ የእግሩን ርዝመት ያህልም አይሆን፡፡

በሀሺሽ መደንዘዝና ራስን መሳት የጤንነት ዕብደት ከመሆኑ ጋር ሞትንም በገዛ እጅ ማቅረብ ነው፡፡

## ለ/ አለማወቅ

መሀይምነት የጨለማ ውስጥ ጉዞ ነው፡፡ ነባራዊ ሁኔታን አለመረዳት ከመሀይምነት ክንፎች አንዱ ነው፡፡ ሙስሊሞች የሚገኙበትን ተጨባጭ ሁኔታ ማስተንተን ያቃታቸው በአስተሳሰብ ያልተገሩ ህሊናዎችም በከፊል ጨለምተኞች ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ በጀመዓ አለመማርና አለመስራት የችግሩ ምንጭ ለመሆናቸው ተጠቃሽ መንስኤዎች ናቸው፡፡

## ሐ/ ስሜት (ሸህዋ)

የሰው ልጅ ይበላል፤ ይጠጣል፡፡ አላህም ሲፈጥረው ስሜታዊ አድርጎታል፡፡ ለሰው ልጅ መለያ ባህሪውም ነው፡፡ ወደ ተቃራኒ ፆታ መዘንበል እና ስሜትን ማርካት ይሻል፡፡ ወጣትነት ደግሞ የጉርምስና ክፍለ-እርከን ስለሆነ እጅግ ያስቸግራል፡፡

ለዚህ ነው ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ)

*«እናንተ ወጣቶች ሆይ! ከናንተ ውስጥ ማግባት የቻለ እና የትዳርን ጣጣ ለማሟላት አቅሙ ያለው ያግባ፡፡»* ያሉት

በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ወጣቱ የትዳርን ግርዶሽ ከፍቶ መግባት አልቻለም፡፡ በእርግጥ ለዚህ ጠቢቡ ወዳጃችን (ሰ.ዐ.ወ) *«ያልቻለ ደግሞ ይፁም»* ሲሉ ሁለተኛ መፍትሄያቸውን ገልፀዋል፡፡ ምክንያቱም አሉ ረሱሉ(ሰ.ዐ.ወ) *«እርሱ ፆም ዓይንን ይሰብራል፤ ስሜትን ሊደብ ያሰይዛል፡፡»* አዎ! ለስሜት (ሸህዋ) ከሁለት በአንዱ ገደብና ልጓም ካላበጁለት ገደል ይከታል፡፡ ስብዕናን ያጎድፋል፡፡ህሊናን ያስታል፡፡ ብልግናን ያስፋፋል፡፡ ማህበረሰብን ይበክላል፡፡ በሽታና ደዌ ብሎም አስከፊ ወረርሽኝ ይከሰታል፡፡ ትውልድ ይቋረጣል፡፡ የስነ-ምግባራት ብርሀን ይከስማል፡፡ ለዚህ ታዲያ

ኢስላማዊ ግብረ-ሰናይ ማህበራትና ድርጅቶችን በማቋቋም ለትዳር የደረሱ ወጣቶችን ማጣመር እንደ መፍትሄ ውጤታማ ነው፡፡ የመህርን ዋጋ ጣራ የሚያደርሱ ወጣቱን ከመጠየቅ የሚያበራግጉ ወላጆች ወደ ሴተኛ አዳሪዎች ሊመለከቱ ይገባል፡፡ በስሜት ተነድተው ፀያፍ ተግባር ላይ ለመውደቅ የሚቸኩሉ ወጣቶች በተግባሩ የቀደሟቸውን ሰዎች መጨረሻ ያስተውሉ፡፡ ወጣት ሙስሊም ከሁለቱ አማራጮች ውጪ ሌላ አጥፊ መንገዶችን መራቅ ግዴታው ነው፡፡

## መ/ ዓላማ ቢስ እና ዕቅድ አልባ መሆን

ወጣቱ ይማራል ግን ለምን ለማንና የት ለመድረስ ማወቅ የተሳነው ይመስላል፡፡ ዓላማህ ምንድን ነው ተብሎ ጥያቄ ሲቀርብለት በቂ መልስ መስጠት የማይችል ወጣት በኢስላም ጉያ ስር አይደለም፡፡ በዕቅድ በማይጓዝና ለተፈፃሚነቱ የማይንቀሳቀስ ስብዕና ደካማ ነው፡፡ በነዚህ ዘርፎች ላይ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ጠንካራ አማኝ ከደካማው መልካምና የተሻለ ነው ብለዋል፡፡

## ሠ/ ችኩልነት

በሁሉም ጉዳዮች መፍጠን የውድቀት ድልድይ ነው፡፡ ወጣት ትንሽ ካወቀ የተቀረውን አላዋቂ፣ ከሀዲ፣አስመሳይ ሙሽሪክ ለማለት ሲቸኩል ይስተዋላል፡፡ ይህ አንዱ ዕድሜን ማባከኛ፣ ጊዜን ማቃጠያ እንቅፋት ነው፡፡ ንዴትና ኩርፊያ ሰዎችን ማራቅና ማጠባበቅ ከዚህ ስር ነው፡፡ ይህ ዲን አደም ከጀነት ወጥተውበታል፤ኑህ ለ950 ዓመታት ለፍተውበታል፡፡ ዘከርያ በመጋዝ ተገዝግዘውበታል፡፡ የህያ አንገታቸው ለአንዲት ዝሙተኛ መህርነት ቀርቧል፡፡ ሙሳ ተሰደውለታል፡፡ ዒሳ አርገውበታል፡፡ የኛ ፋንታ ሙሀመድ(ሰ.ዐ.ወ) ደግሞ ተደብድበው ደምተውለታል፤ ታግለው ቆስለውለታል፡፡ ሌት ተቀን ደፉ ቀና ብልውለታል፡፡ በሁሉም ላይ የአላህ ሰላምና እዝነት ይስፈን፡፡ ሁሉም ነብያት ለደረሰባቸው መከራ ሁሉ ታግሰዋል፡፡ ሳይቸኩሉ ከአላህ የሆነን እርዳታ ተጠባብቀዋል፡፡

## ረ/ ስንፍና

ማሰብ፣ማስተንተን፣ማወቅ መስራት፣ማግኘትና መለወጥ እየቻለ ራሱን አልችልም በሚል ስሜት ራሱን የሸበበ ሰነፍ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከጎኑ በኩል ያሉ የለውጥ ፍሬዎችን ምንነትና ማንነት ማስተዋል ያቅተዋል፡፡ ትላንት

በዕውቀቱ እዚህ ግባ የማይባል ሰው ለማወቅ ባደረገው ጥረት የተነሳ አዋቂ ሲሆን ለምን? ሆነ እንጂ እንዴት ሆነ? የሚል ህሊና አልተገጠመለትም፡፡ ይህ የስንፍና ፍሬ ወደ ምቀኝነት ያመራል፡፡ እንዴት አደገ? ምንን መሠረት አደረገ? ብሎ የማይጠይቅ አዕምሮ እውነትም ሰንፏል፡፡ በለውጥ መንገድ ላይ ያሉ ሰዎችን እንደ አርአያ (Role Model) አድርጎ አልያዘም፡፡ ይልቁን ቁጭታምና ስራ ፈትነትን መርጦ የማያልቅ ጥቅም አልባ ደካማ የድር ገመድ ይፈትላል፡፡ አዕምሮ ካላሰቡበት እና ካልሰሩበት ከንቱ ነው፡፡ ሰውየው ራሱን በራሱ፣ በሰዎች ግፊት የስንፍናን ባህል ሊያጎለብት ይችላል፡፡ " አውቆ የተኛን ቢጠሩት አይሰማም" ይሉ ዘንድ ይህ ሰው ሌሎችን ከማድነቅ እና መከጀል በቀር ለራሱ ጥረት አያደርግም፡፡ ወጣቱ ደግሞ ከዚህ ሊርቅ ይገባል፡፡

## ሰ/ ተስፋ መቁረጥ

የሰው ልጅ ያለምግብና ውሃ የተወሰነ ጊዜ መቆየት ይችላል፡፡ ያለ ተስፋ ግን ትንሽም አይቆይም፡፡ በድን ይሆናል፡፡ ብሩህ ተስፋ ከስኬት ፊትለፊት የተዘረጋ ምንጣፍ ነው፡፡ በጥረትና ልፋት ከታጀበ፣ ለውጥን ከሰነቁበት ጥሩ ድልድይ ነው፡፡ ነገን አንድ ሰው ፍሬያማ አድርጎ ይውላት ዘንድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ በተቃራኒው ግን የተስፋን ብርሀን በፅልመት ብዕር መሳል ድንቁርና ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሰውየውን ወዳልተፈለገ የውድቀት ቦይ ውስጥ ይጥለዋል፡፡ ጥረትን አዋህዶ የለውጥ ህልምን ሰንቆ ጉዞ የጀመረ ጋላቢ ፀሀይ ሳትጠልቅ ከስኬት መስክ ላይ ያርፋል፡፡ አንድን ጉዳይ በተደጋጋሚ ሞክሮ ስህተት ቢፈጠር ያሰበው ባይሳካ አሁንም ጥረት ያደርጋል፡፡ ተስፋ መቁረጥ ፍፁም አላስፈላጊ ስለሆነ ከያንዳንዱ ሙስሊም ወጣት ሊፋቅ ይገባል፡፡ ሰናይ ማሰብና ተስፈኝነትን ባህሪ ማድረግ ህሊና ላይ የተገጠመ መብራት ነው ፡፡ ህይወት ትሰምራለች ፡፡ መንገድ ይቀጥላል፡፡ ፍሰሀ ይገኛል ከስኬት መስክ ይደርሳል፡፡

# 6

# አዳኞቹ

ክህደት እና እምነት፤ ከሀዲ እና አማኝ፤ ሀሰት እና አቀንቃኞቹ፤ እውነት እና ረዳቶቹ፤ ሁሉም ተቃራኒ ዕይታዎች የራሳቸው የሆነ ደጋፊ እና አስፈጻሚ አላቸው፡፡ ኢስላም የምድር ላይ ውበት፤ የአላህ (ሱ.ወ) ዕንቁ ፀጋ ነው፡፡ ለሰው ልጆች እና ጂኖች የተበረከተ አንጡራ ሀብት ሲሆን፤የያዙት ከፉላጎታቸው ይገናኛሉ፡፤ የተውት እና የናቁት ደግሞ የውርደትን ካባ ከነ ቆሻሻው ይለብሳሉ፡፡

የምድሪቱ ቫይረሶች (ጽዮናውያን አይሁዶች) የኢስላምን የበላይነት ያውቁታል፡፡ መጪውን ዘመን እንደሚረከብ፤ እነርሱ ምድሪቱን አይመራም የሚል የማይሳካ ፕሮጀክት ነድፈው በመንቀሳቀስ የመጀመሪያ ደረጃ የሀሰት (ፈሳድ) ወታደር ለመሆን በቅተዋል፡፡

በአይሁዶች ፈለግ ስር የወደቁ የሌሎች ዓለማት ነዋሪዎች እና ኢስላም ፍላጎታቸው እየቅል ነው፡፡ እስቲ አጠር አድርገን ኢስላም ምንና ማንን እንዲሁም የክህደት ፍላጎት ምን እንደሆነ ለማየት እንሞክር፡፡

## ክህደት እና ፍላጎቱ

## ሽርክ

ፍጡራን የተፈጠሩለትን ዓላማ ትተው በማጋራት (ሽርክ) ገደል ቁልቁል እንዲምዘገዘጉ ይሻል፡፡አጋሪያን ቢቻላቸው እነርሱ ወዳሉበት ርዕዮት

፤ካልቻሉ ደግሞ ከኢስላም ጋር የተደባለቀ እንክርዳድ እምነት መደባለቅ (ልክ አህባሽን ይመስል)፡፡ ለዚህ ነው የጠንቋይ እና መፅሀፍ ገላጮችን ጊቢ ማድራት አሊያም በኪነ ጥበብ ውስጥ የተደበቀውን ሰይጣናዊ አምልኮ (Satanism) ማስረፅ ነው፡፡ምዕራቡ ዓለም በተለይ አሜሪካና እስራኤል ኢስላማዊውን ዐቂዳ ጦርነት ከፍተውበታል፡፡ በሀገራች እንኳ በሰሜኑ ክፍል የሚገኙ ቀብሮችን (ዶሪሆችን) ልዩ መስህ ይኖራቸው ዘንድ ሚሊዬኖችን መድበው አስገንብተዋል፡፡ ተንኮላቸውን ተረድቶ የተከላከላቸውን ጦር ያዘምቱበታል፡፡ ይህን ዕውነታ ዓለም በደንብ ያውቀዋል፡፡ አምላኬ አላህ ነው ፍፁም አላጋራበትም የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሱና ፈፅሞ አልተውም ያለ ሁሉ ሽብርተኛ ነው፡፡

እነዚህ እርኩሳን በዘመቱባቸው ሀገራት ከጦርነታቸው ጀርባ የሽርክን ሀውልት ለመትከል ባይሳካ ሌሎች የፈሳድ ችግኞችን ተክለው ይወጣሉ፡፡ ፍፁም ሙስሊሞች ደግሞ የኢብራሂምን አርአያ የተከተሉ፣ የሙሀመድን (ሰ.ዐ.ወ) አደራ የሚወጡ ብፁዕ ትውልድ ስለሆነ ፤የሽርክን ቲሸርት ከመልበስ የሸሂድነትን በደም የተነከረ ልብስ መልበስን ይመርጣል፡፡

## እርቃናዊነት

ስጋንና ቆዳን መሸፈን ተፈጥሯዊ ነው ፡፡ ሙስሊም ከምዕራባዊያን እንስሳዊነት ፍፁም የራቀ ነው፡፡ ባህሪያቸው እንደ አሳማ ነው፡፡ ለባለቤቶቻቸው እና ለእናቶቻቸው እንዲሁም ለሴት ልጆቻቸው ፍፁም የማያዝኑ ለውድቀት መንጋጋ አሰማምረው የሚሰጡ አረመኔዎች ናቸው፡፡ ቅናት የሚባል ነገር ፍፁም የላቸውም ታዲያ ይህን እርኩስ ምግባር የወደቀ እይታ በሙስሊም ሀገራት ለመዝራት ሩጫ ጀመሩ፡፡ አልተሳካም፡፡ ይባስ የኡማው እምነት ጠነከረ፡፡ የዛኔ ታዲያ በሽብር እና አክራሪነት በመፈረጅ የእብለት ወታደሮቻቸውን አዘመቱ፡፡ ሙስሊም ሴቶችን ከነሂጃባቸው በደም ነከሯቸው፡፡ በእናቶች ላይ ጨክነው መድፍ ተኮሱ፤ ከደከመ አጥንታቸው ጋር በግንብ ፍርስራሽ ስር ተቀብረው ቀሩ፡፡ይህ ሁሉ የደረሰባቸው ምንም ወንጀል ስለሰሩ አይደለም ሙስሊም ስለሆኑ ብቻ ነው፡፡ ኢስላምን ስለኖሩ

እርቃናዊነትን ስለተቃረኑ ነው፡፡ ሴት ልጅ ራቁቷን ትሄድ ዘንድ ፍላጎታቸው የሆነው ለሌላ ዓላማ ሳይሆን የሙስሊሙን ማንነት ከገላው ለመንጠቅ የፈለጉ ፤ስውር የጠላት (የጽዮናውያን) መልእክተኞች የሂጃብን ፅንሰ- ሀሳብ በተልከሰከሰ ምርምር ለማበላሸት አህባሽ መጥቶ ነበር፡፡ ለዚህ ነው ሙስሊም ሴት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው በሂጃባቸው ላይ ጦርነት የተከፈተባቸው፡፡ ለዚህ ነው በየ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሂጃብ ለብሶ ትምህርት የለም እየተባለ ሙስሊሙን ኋላ ቀር ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ያለው፡፡

በኪነ-ጥበብ ጥቁር ጥላ ስር በእርቃናዊነት ደላላነት በብሩ የሴት ልጅ ገላ እንደ ሸቀጥ ይቸበቸባል፡፡ ለርሷ ክብሯ ዓይናፋርነቷ ነበር፡፡ ነገር ግን በስልጣኔ እና ዘመናዊነት ስም ለአውሬ ተሰጠች ፡፡ ይህን ነው እንግዲህ አውሮፓውያን ለሙስሊም ሀገራት ሴቶች የሚመኙት፡፡ሙስሊም ሀገራት ውስጥ የሴት ልጅ ነፃነት የለም፤ ከወንድ እኩል መብት የላትም እየተባለ ዕፍረት በሌላቸው ሚዲያዎቻቸው የሚነገረው፡፡ እስቲ አስቡት

አንዲት ቆንጆ ሴት አርቲስት በእራፊ ጨርቆች ጡቶቿን እና የግል ክፍሏን ብቻ ሸፍና፤ተልጦ ለመብላት የተዘጋጀ ብርቱካን መስላ መድረክ ላይ ስትወዛወዝ........

"....መድረኩን በሺዎች የሚቆጠሩ ወንዶች ይከታተሉታል፡፡ ሁሉም በሀሳቡ ይቋምጣል፡፡ በመንፈስ ያ ሁሉ ሰው ይቋደሳታል፡፡"

".....የብልግና እና ህገ-ወጥ ዝሙት አፈንፋኞች ተልጦ በተቀመጠ ሙዝ ላይ ዝንቦች አርፈው እነርሱን እንደሚመገቡትና ቆሻሻ ጥለው እንደሚሄዱት፤የዚህች እንስት ዕጣ ፋንታ ያው ነው፡፡ "

".... በዚህ ብቻ ቢያበቃለት ምን ነበር! በየቲቪው መስኮት ትወዛወዛለች......የሚሊየኖች ዓይን ያርፍባታል...." ታዲያ ይህ ስልጣኔ ወይሰ ስይጣኔ አሊያም ዝና ወይስ ዘመናዊ ዚና!፡፡ ነፃነት ወይስ ጭቆና መልሱ ግልፅ ነው፡፡ መበዝበዝ፣ መጨቆን እና የህብረተሰብ መገለገያ ዕቃነት ነው፡፡ በሚሊየኖች ሚቆጠሩ ወጣቶችን ስነ-ልቦና ከአፈር መደባለቅ ነው፡፡ ለዚህ ነው አንድ አሜሪካዊ አሳቢ (analyst) በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሙሀመዳዊያን

ላይ በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮችን ከማዝመት አንዲት እርቃናዊ ሴት ዘፋኝን መድረክ ላይ መስቀል .ያለው

ኢስላም ለዓለም ብልፅና ባፈራቻው ወጣቶች አበርክቶ አይኖረው ዘንድ ለማሰናከል ይህ እና መሰል ዘዴዎችን ተጠቅመዋል፡፡ ይህ ህዝብ የሚያሻው ስነ-ምግባሩን ከእኩይ ወደ ሰናይ የሚያወጡትን ነው፡፡ እርቃናዊነቱ ታዲያ አካላዊ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሆኖ እንዳይቀር፤ እነዚህ የውድቀት መሳሪያዎች እርስ በእርስ የተሳሰሩ ናቸው፡፡ ሙስሊሙ ወጣት ከነዚህ ርካሽ ተግባራት ራሱን ማቀብ አለበት፡፡ በተለይ ሴት ወጣቶች ለማንነታቸው ትኩረት ሰጥተው የእርቃናዊነት ቀንደኛ ተቃዋሚ መሆን አለባቸው፡፡ የምዕራቡ ፍላጎት ርካሽ፣ ውዳቂ እና እርባና ቢስ ነው፡፡ ምን ያህል በስነ-ጥበብ፤ ዕድገት እና ስልጣኔ ስሞች ቢሸብቡትም፡፡

## የስነ-ምግባር ውደቀትን

አይሁዶች አውቆ ጠፍ ህዝቦች ናቸው፡፡ የቁርአንን ኩል መልዕክት ለእውነትነቱ ጥርጣሬ የላቸውም፡፡ ለሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ዓለማቀፋዊ ነብይነት ተውራታቸው በደንብ ነግሯቸዋል፡፡

ቢሆንም ግን በቅናት መንፈስ መልዕክቱን ከመቀበል አፈገፈጉ፤ ለዱንያ ጥፋትን ለምድሪቱ ብክለትን ለአማኞች ውድቀትን ታጥቀው ተነሱ፡፡ ስነ-ምግባርን የግንባታው መሰረት ያደረገ  ብቸኛ እምነት ደግሞ ኢስላም ነው፡፡ መቼም በግልፅ እንደሚታወቀው ጦርነቶች ሁሉ ኢስላም ላይ የታቀዱ ናቸው፡፡ የኢስላምን ሀይል ለማዳከም ከተጠቀሙዋቸው ፕሮጀክቶች አንዱ ስነ-ምግባርን ማውረድ እና ለውድቀት መዳረግ ነው፡፡

## የአስካሪ መጠጥ ዋናተኛ

ወንጀል የተባለን ለመስራት መነሻ ነጥብ ነው፡፡ አስካሪ መጠጥ(ኸምር) የኃጢአቶች ሁሉ እናት ናት ሲሉ ታላቁ ሰው ገልፀውታል፡፡ ቁርአን ደግሞ የሰይጣን የእጅ ስራ ፤ከአምልኮ መዘናጊያ ሲል ከገለፀ በኋላ ከርሱ መራቅ የመድህን መንገድነቱን አስቀምጧል፡፡

የምዕራቡ ዓለም እና ይሁዲዎች ግን ይህን እርኩስ ተግባር ለዓላማቸው ማሳኪያ አድርገውታል፡፡ ትላልቅ የመጠጥ ፋብሪካዎችን በማስገንባት ለእያንዳንዷ ጠብታ ነፍስ የውድቀትን እሳት በጠርሙስ እያዳረሱ ነው፡፡ አስካሪ መጠጥን የሚጠጣ ማንኛውም ግለሰብ በምንም መልኩ ጥቅም የለውም፡፡ይህን ያልተገነዘቡ የሀገራችንም ይሁን የሶስተኛው ዓለም ነዋሪዎች የወንዙ ውስጥ ዋናተኞች ሆነዋል፡፡ የሚያሳዝነው ግን ይህን ሁሉ ዋናተኛ የድራማው አዘጋጆች ከመጋረጃ ጀርባ ተደብቀው አሳዛኙን ውጤት መጠባበቃቸው ነው፡፡

አስካሪ መጠጥን የተጎነጨ ሰው ሰማይ ፣ምድሩ ይገለባበጥበታል፡፡ ሀራሙ ሀላል ዒባዳው ቢድዓ ይሆንበታል፡፡ ነጩ ጥቁር ይሆንበታል፡፡ በሽታን ይሰርቃል፤ ከሰውነት ተራ ወጥቶ በውድቀቱ መባቻ ግን ሲፀፀት ይስተዋላል፡፡ በአስካሪ መጠጥ የተነሳ በሽታ ይመጣል፤ ወደ ሞትም ያሸጋግራል፡፡

የቤተሰብ ህይወት ተበጥብጦ ፤ለሴተኛ አዳሪነት ለማጅራት መችነት እና ዕፅ አዘዋዋሪነት ይወስዳል፡፡

- ማህበረሰብ ህይወቱ አመድ ይለብሳል፤
- አደጋ የበዛበት እና ሁሌ ሞት ያጠላበት ይሆናል፡፡
- ህፃናት ሴቶች ተገደው ይደፈራሉ ፤ግብረሰዶም ይንሰራፋል፡፡
- ሚስቶች ያለ ባል፤ ልጆች ያለ አባት ይቀራሉ፡፡
- ማህበራዊ ህይወት ይበላሻል፤የግለሰብ ክብር ይወርዳል፡፡ ወዘተ…

ምዕራቡ ዓለም በአስካሪ መጠጥ እና መሰል ዕፆች ተጥለቅልቋል፡፡ ሌላው ቀርቶ በሊፍት ውስጥ ሴቶች የመደፈር ጥቃት ሰለባ ይሆናሉ፡፡

በሀገራችን ውስጥ የረሀብ እና የድርቅ እንዲሁም የድህነት መጠን ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የእርዳታ ድርጅቶች ከሚያቀርቡት ምግብ እና መሰል ነገሮች እነዚህ የመጠጥ ፋብሪካዎች ለህ/ሰቡ ፍጆታ የሚያዘጋጁት

የሆድ ውስጥ እሳት ይበልጣል፡፡ በሀገራችን ውስጥ አሁን ቀረ የሚባለው ነገር የመጠጥን ፋብሪካ በየመንደሩ ማቋቋም ነው፡፡

ህብረተሰብን፣ ሀገርን፣ ቤተሰብን እና ማንነትን ለማውደም ከፈለግን ይህን መጠቀም ነው፡፡ ዕድገት የበላይነት ብሎም ብልፅግናን የምንሻ ሙስሊም ወጣቶች ከዚህ እርኩስ ተግባር መራቃችን ለሌሎች ግንዛቤን ማስጨበጣችን አከራሪነት ሊባል ይችላል፡፡ ይህ ሲባል ግን አውቀው ሆን ብለው ቃላት ጠምዛዥ አካት እንደሚያስቡት ጋጠወጥነት አይደለም፡፡

## የአደባባይ ዝሙት

በመዝናኛ እና ኪነ-ጥበብ በተሰኙ ቀለማት ተደብቀው የሴትን ገላ ሸማች ቸብቻቢ ነጋዴ አውሮፓውያን፤ ይህ ብልግናቸውን ከድህነት በታች ለሚኖሩ ሀገራት ነዋሪዎችም አውርሰውታል፡፡

ምዕራቡ እፍረት/ሀያእ/ ከማጣቱ የተነሳ በየአደባባዩ ዝሙትን መተግበር ከተያያዘው ሰነባብቷል፡፡ ዘመንን የሚቆጥሩ ታሪካዊ ወረቀቶች እንኳ አላለፉም፡፡ አሁን ባለንት ዘመን ሳይቀር የዝሙት ማስታወቂያ በየቲቪው ቻናል በየሬዲየው ማሰራጫ እና ህትመት ሚዲያዎች ላይ ይለቀቃሉ፡፡ ዝሙትን ስሩ ኮንዶም ይኸውላችሁ በየመንገዱ እና ክበባቱ ይሰበካል፡፡ ወጣቱ ከ “ ገርል ፍሬንዱ ”ጋር የዚህ የውድቀት በረከት ተቋዳሽ ይሆናል፡፡

የልቅ ወሲብ ፊልሞችን በሰፊው ማለትም በየቲቪው ዩ ቲዩብ (you tube) እና ሌሎች መሰል በህብረተሰቡ ዘንድ ይገኛሉ ተብለው በሚታሰቡ መገናኛ ዘዴዎች ያደርሱታል፡፡ህፃናት በልጅነት ሴሰኝነትን ለምደው በህይወታቸው ያደርሱታል፡፡ህፃናት በልጅነት ሴሰኝትን ለምደው በህይወታቸው ይተገብሩት ዘንድ ታቅዶ በሰፊ ሲሰራ ይስተዋላል፡፡

ዝሙት መንገድነቱ የከፋ እና ፀያፍ ፣ ፊትን የሚያጠቁር ፣ ሲሳይን የሚበትን ብልግና ተግባር ለመሆኑ ሁሉም ይስማማል፡፡ ነገር ግን ዝሙት

ይሰራ ዘንድ መንገዱን በአስካሪ መጠጥ፣ በአደንዛዥ ዕፅ እንዲሁም ሰላቢ ዘፈን የሚያግራሩት ይሁዲዎች......

ከዚህ ተግባር የሚጠቀሙት አንድ ነገርን ብቻ ነው፡፡ እውነትን ስለተቃረኑ ኢስላምን ስለወጉ ብቻ ነው፡፡ ሁሉም ሀይማኖት የዝሙትን አስከፊነት ቢያስተምሩም ኢስላም ግን ቆንጠጥ አድርጎና አበክሮ ነው ከዝሙት መራቅን ያስተማረው፡፡ እስቲ አስቡት

“....ሁለት ወጣቶች ጋብቻን አስበው ሳይሆን ስሜታቸውን አድምጠው ብቻ ተፋቅረው፤ በዝሙት ጀልባ ተሳፍረው ... ወደ ሌላ ዓለም ገብተው... ለህብረተሰብ አደጋ የሆኑ ልጆችን ሲያበረክቱ እና ለማ/ሰብ ችግር ሲሆኑ፡፡”

“...በውሸት ፍቅር ክንፍ ብለው መሀል መንገድ ላይ ለውድቀት ሲዳረጉ ትዳር ውስጥ አይገቡ አቅም የለ፡፡”

“....ሞራል ፤ዕድገት እና ማንሰራራት በሁለቱም በኩል ከታሰበው በታች ይሆናል፡፡ ይህን ተከትሎ ታዲያ ተስፋቢስ መሆን ፣ ስደትን መምረጥ፣ ገላን መሸጥ ይመጣል፡፡”

ምዕራቡ ዓለም ዝሙትን የገቢ ምንጭ አድርጎ ስለያዘው የዕለት ተዕለት ተግባር ነው፡፡በነገራችን ላይ ገንዘብ ወሲብ እና ዝና ግቡ የሆነው የምዕራቡ ዓለም ጤዛ ስልጣኔ በቅርቡ ግብዓተ-መሬቱ ይፈፀማል፡፡ይህን የሚያመላክቱ ብዙ ክስተቶች እየታዩ ነው፡፡

## የሰዶም መንሰራፋት

ነገደ-ሎጥ በዚህ ፀያፍ ተግባር ከምድረ-ገፅ ጠፍቷል፡፡ አላህ እጅግ ከመቆጣቱ የተነሳ የእሳት ዝናብ አውርዶ ከጥቂት አማኞች በስተቀር ፈጅቷቸዋል፡፡

ምዕራቡ ዓለም የሴት ጣዕም ጎምዝዞት እና ሰልችቶት ሌላ ተጨማሪ እርካታ እና ደስታ ፈልጎ ሰዶምን ለምዷል፡፡ ጥቂት የተወሰኑ ሀገራት ይህን

ምግባረ ብልሹነት  በህገ-ሀገራቸው የከለከሉ ቢሆንም የኋላ ኋላ ግን ፈቅደውታል፡፡ ለአብነት ያህል ለወደፊት የውድቀትን ፅዋ የምትቀምሰው አሜሪካ እና ደቡብ አፍሪቃ ይገኙበታል፡፡

በአደንዛዥ ዕፅ የደነደኑ፣ ፍፁም ከሰብዓዊነት የወጡ፤ከእንስሳት በታች የሚያስቡ፣ ተፈጥሮን የተቃረኑ፣ ከማህበረሰብ የተገለሉ፣ ሰውነትን የጠሉ፣ፀያፍ ተመጋቢዎች እና ርህራሄ የሌላቸው ናቸው፡፡

ከሰማያት በላይ ያለውን አምላክ ስራውን ኮነኑት፤ ለሰው የሚበጀውን ፍጡር አጥላሉት፡፤ስለ ምሉዕነቱም ዕውቅና ነሱት፡፡ ለማንነቱ ጀርባ ሰጥተው በቁም መትላትን መረጡ፡፡ ተመሳሳይ ሁለት ፆታዎች አንሶላ ተጋፈፉ፡፡ በሱሱም ተጠመዱ፡፡ ይባስ ብለውም ህጋዊ ይሆንላቸው ዘንድ በጋብቻ ገመድ ተሳሰሩ፡፡ አሜሪካ ውስጥ ብቻ ቆየት ባለ መረጃ 7-8 ሚሊዮን ግብሰዶማውያን ሲኖሩ፤በኒውዮርክ ከተማ ብቻ ደግሞ 25 ሚሊዮን የሚደርሱ ግብረሰዶማውያን አሉ፡፡የሌሎች ዓለማት ዕጣ ፋንታም በነዚህ እርኩሳን ተባዮች የሚወሰን መሆኑ ምዕራቡ በሌላው ዓለም ያሳደረው አሉታዊ ተፅዕኖ በቂ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ሀገራችን ውስጥ በቅርቡ ሰዶማውያን ራሳቸውን በግልፅ ያለ እፍረት ለህዝብ ሲያስተዋውቁ እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡

የአላህ አርሽ የሚንቀጠቀጥበት ይህ ከባድ ወንጀል ለሙስሊም ሀገራት ስሙን  ቀይሮ ሲተገበር ተስተውሏል፡፡ የሴቶችን ህልውና፣ ብሩህ ተስፋ የሚያጠፋ ብልግና ነው፡፡ መመሪያ ተቀርፆለት እና የትንተና ማዕከላት ተዘጋጅተውለት ሲሰራ መስተዋሉ ምዕራቡ ዓለም በተለይ አይሁዶች ምን ያህል የሰውን ልጅ በውድቀት ገደል ውስጥ ለመከተት እንደፈለጉ ያመላክታል፡፡

የአይሁዶች ፍላጎት ከዝሙት አልፎ ኢ-ተፈጥሯዊ ተግባር ተሰርቶ ማየት ነው፡፡ ምኞታቸው ተሟላ፡፡ እንዳሉትም (በታልሙዳቸው) የተቀረው ፍጥረት ለነርሱ አገልጋይ ሆነ፡፡

ወደዚህ እርኩስ ተግባር ሲጋብዙ እነርሱ ሰላማዊ፤ እና እንዲሁም ልማታዊ ናቸው፡፡ ከዚህ ተግባር መራቅን ህዝቡን የሚያስተምሩ ዱዓቶች ደግሞ ፅንፈኛ፣አሸባሪ እና አክራሪ ናቸው፡፡ ይህ ነው እንግዲህ የምዕራቡ ውድቀትና ፍፃሜ፡፡ ግብረ-ሰዶማውያን የምድር ላይ በሽታዎች ናቸው፡፡ አድራጊም ተደራጊም የተባያቸው ማጥፊያ መድህኒታቸው ግድያ ነው፡፡

## ተፈላጊው ትውልድ ይህ ነው

ለክህደት ፣ፈሳድ እና ውድቀት ዘብ የቆሙት፤ለዕድገቱም ጥረት የሚዲርጉት ይሁዲዎች ከነ አጃግሬዎቻቸው የሚፈልጉት ትውልድ የተበከሉ ዐቂዳዎችን አንግቦ ስራ ሳይሰራ በየአድባራቱ ንፍሮ እየቀቀለ ያደረ፤በየቀብሩ ቦታ እየሄደ ሰንደል የሚሰካ እና ዕጣን በስለት የሚያስገባ፤ የሙታን ቀብር ላይ ደም የሚያፈስ እንዲሁም ዕርዳታውን የሚጠይቅ ፤ሰይጣንን በየመፅሀፍ ገላጩ እና ጠንቋይ ቤት የሚያመልክ ማህበረሰብ ማፍራት ነው፡፡

ራቁቷን በቁርጥራጭ ልብሶች ለጣጥፋ በየጎዳናው የምታልፍ እንስትን ፤ከዚያ ወጣቱን፤ ባለትዳሩን እና ጎልማሳውን ሳይቀር በስሜቱ የምትፈታተን ጭራቅ ሴት መውለድ ነው፡፡ ሱሪ ለብሳ፤ ፀጉሯን ብትን አድርጋ የጤነኛ ዕብድ መስላ በየቡና ቤቱ እና መዝናኛ ቦታ ስጋዋን ለበሊታዎች የምትቸበችብ ሴትን ምዕራቡ ይፈልጋል፡፡

ህብረተሰቡ በአስካሪ መጠጥ ድንዝ ብሎ በየታክሲው የአፉ ሽታ ሰውን የሚረብሽ፣ በየመንደሩ ልብሱ ላይ የሚፀዳዳ አስገድዶ ደፋሪ፣ ግብረ ስጋ ግንኙነት ከልጁ ይሁን ሚስቱ አሊያ ከናቱ ጋር ያድርግ የማያውቅ፣ ቤቱን በችግር እና ድህነት ብሎም በረሀብ እየቆላ ገንዘቡን በየቢራ እና ጂኒ ቤቱ የሚዘራ፣ ግዴታውን በአግባቡ የማይወጣ ግለሰብ በገፍ ማምረት እና ለዓለም ማርከት የምዕራቡ ግብ ነው፡፡

ዝሙት በሁሉም ማህበረሰብ ዘንድ ተተግብሮ የዲቃላ ሀብትን ለማካበት፣ በሽታ እና ስንፍና ተስፋፍቶ የሀገራት ከድህነት በታች መሆን፣ ህፃናት ያለ አሳዳጊ አዛውንት ያለ ጧሪ ሜዳ ላይ መውደቃቸውን ምዕራቡ

ይፈልገዋል፡፡ የተቀረው ዓለም የእነርሱን አርአያነት መከተሉን ስለሚያውቁ ልቅ የወሲብ ፊልሞችን ለንግድ ያቀርባሉ፡፡

በቅዱሳን መፅሀፍት የተወገዘውን እንስሳዊ ተግባር ሰዶምን የሚተገብር ትውልድ በምዕራቡ እጅግ ይከጀላል፡፡ ዓይናፋርነት የሌላቸው ምግባረ ብልሹ እና በሞራል፣ በአካል የወረዱ ሰዎችን ማየት የአይሁዶች ግብ ነው፡፡

በአጭሩ አላህ በቁርአን እንደገለፀው አይሁዶች ፍላጎታቸው

وَيَسْعَوْنَ فِي الْأَرْضِ فَسَادًا

**« በምድርም ውስጥ ለማበላሸት ይሮጣሉ፡፡» ማኢዳ 64**

ነገር ግን ለብክለት የሚራመዱበትን እግር የሚያስቡበትን ህሊና ሊያቀጣጥሉት ያሹትን የውድቀት ችቦ አላህ ያጠፋዋል፡፡

كُلَّمَا أَوْقَدُوا نَارًا لِّلْحَرْبِ أَطْفَأَهَا اللَّهُ

**«ለጦር እሳትን ባያያዙ (ባጫሩ) ቁጥር አላህ ያጠፋታል፡፡» አል-ማኢዳ 64**

## ያልተኖረ ወጣትነት

ህይወት እርከኖች አሏት፡፡ እያንዳንዱ እርከን ደግሞ የራሱ የሆነ መገለጫ ውጣ ውረድ እና ገጠመኝ አለው፡፡ ከአንድ ሰው የምድራዊ ህይወቱ ክፍል ውስጥ ወጣትነት ወርቃማው ነው፡፡ ልዩ ብርታት ይስተዋልበታል፡፡ የመስራት፣የመማር የመለወጥ እና ልዩ ስልጣኔ ውስጥ የመግባት ወኔ ይቋጠርበታል፡፡

ሙስሊም ስብዕና በዚህ አፍላ እርከን ላይ ለህይማኖቱ ታማኝ መሆን አለበት፡፡ የጊዜ ብክነትን እና አውደልዳይነትን ፍፁም በመራቅ በዕውቀት እና ተግባር፣ በትግልና እና ውጤት እንቅስቃሴ ላይ ንቁ ተሳታፊ ነው፡፡

ኢስላም የወጣትነትን ጉዳይ አበክሮ መክሯል፡፡ በቁርአን እና ነብያዊ ሀዲሶች ውስጥ ምሳሌዎችን በመጥቀስ፣ተግባራቸውን በማስታወስ፣ ጥንካሬያቸውን በመዘከር ከትውልድ ትውልድ የሚያልፍ ቀጣይ ማስታወሻ አስቀምጧል፡፡

የዋሻው ባለቤቶቸ (አስሀቡል-ከህፍ) ከጣዖታውያን እና አምባገነን እንዲሁም ጋጠ-ወጥ ንጉሳን በእምነታቸው ምክንያት ዋሻ ውስጥ ገብተው ለሦስት ክፍለ-ዘመናት ጥልቅ እንቅልፍ እንደተኙ ይነግረናል፡፡ እነዚህ ሰዎች ወጣቶች እንደነበሩ ይነግረናል፡፡

إِنَّهُمْ فِتْيَةٌ آمَنُوا بِرَبِّهِمْ وَزِدْنَاهُمْ هُدًى

***«እነሱ በጌታቸው ያመኑ ጎበዞች ናቸው፡፡መመሪትንም ጨመርንላቸው፡፡» አል-ከህፍ 13***

ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) በትውፊታቸው እንዲህ ሲሉ ያልተኖረ ወጣትነት ምን ያህል እንደሚያስጠይቅ ተናግረዋል፡፡

"የአንድም ሰው እግር የምፅዓት ቀን ከአራት ጉዳዮች ሳይጠየቅ በፊት ወደ የትም አይንቀሳቀስም፡፡"

1. ዕድሜውን በምን እንዳሳለፈው፣
2. ወጣትነቱን በምን እንዳጠፋው፣
3. ገንዘቡን ከየት እንዳመጣው እና ምን ላይ እንዳዋለው እና
4. ዕውቀቱን ምን እንደሰራበት፡፡

ፋይዳ-ቢስ እና ያልተኖረ ወጣትነት በምድረ-ዓለም ላይ ከሚያጋጥሙ ኪሳራዎች ሁሉ ቁንጮው ነው፡፡

ለነፃነት ያልታገሉበት፣ ለፍትህ ያልቆሙበት ወጣትነት ከጃጁ በኋላ የፀፀት ጉያ ነው፡፡

ይህች ዓለም ወደዚያኛው ዓለም ማለፊያ መንገድ ናት፡፡

## ያልተኖረ ወጣትነት ስንል

በየሀራሙ ቦታ ያለፈ፣ በሱስ እና አደንዛዥ ዕፅ የተቀጨ፣ በከንቱ መንገዶች የበሰበሰ ወጣትነት ዕውነትም አልተኖረም፡፡ በእምነት ነፀብራቅ የተሸለመን ህይወት የማያውቁ ወጣቶች እውነትም አልኖሩትም፡፡ ስለዚህም ነው ህይወት ቁራጮች በወጣቱ ላይ ትኩረትን የሚሰጡት፡፡

ሰውን ከአምላኩ ጋር የሚያራርቁ የድንቁርና ፍልስፍናዎችን እንስሳዊነትን እና መህይምነትን ለመራቅ ወደ ኢስላማዊ የመረጃ ምንጮች ጠጋ ብሎ ኢስላምን ያልተማረ የወጣትነትን ዕንቁ ጊዜ አባክኗል፡፡ አላህ ዘንድም ከተጠያቂነት አያመልጥም፡፡

ዛሬ ዛሬ በሙስሊሙ እና ሀገሩ ውስጥ በተለይ ወጣቱ ክፍል ኢስላም መተግበር እና ማስተማር ሸክም እንደሆነበት ቢነገርም፤ድክመቱ ግን ከወጣቱ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ቤተሰብ፣መንደር እና ማህበረሰብ ውስጥ የተንሰራፋ ነው፡፡ አባቱ ከአልባሌ ሱሶች ምድጃ ላይ ተጥዶ ያየን ልጅ አረጓዴ ጨፌ ላይ ማገት ያዳግት ይሆናል፡፡ እናቷ ለጎረቤት ትኩሳት፣ለባሏ የእግር እሳት የሀሜት ሱሰኛ የሆነችባትን ወጣት ሴት በስነ-ምግባር ምጥቀቷ የተሻለች ሆና ማግኘት ቅዠት ሊሆን ይችላል፡፡

በአስካሪ መጠጥ ሱስ ፅኑ አቋም ያላቸው መንደርተኞች መሀል የበቀሉ ወጣቶችን ከሱስ ነፃ ብለው ማሰብ ቢከብድም አላህ መልካም የሻለት ግን የከሰል ውስጥ ሉል ይሆናል፡፡

ጤንነትን ከፉኛ የሚጎዱ ጪሶች ለምሳሌ ሲጃራ፣ሀሺሽ፣ጋንጃ እና ሺሻ እንደተራ የሚቆጠርበት አካባቢ ላይ ከፍተኛ የወጣትነት ብክነት

የሚጠበቅ ነው፡፡ ነገር ግን ይ እምቡጥ ጊዜ በከንቱ ማለፉ የሁለት ዓለማት ኪሳራን ያስከትላል፡፡

## እውነተኛው የኢስላም ልጅ ይህ ነው

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ለኢስላም የሚበጅ እና ኢስላም የሚበጃቸው ፍሬዎች እነማን እንደሆኑ ለማየት እንሞክራለን፡፡ እውነተኛው የኢስላም ልጅ፡

\-

## 1) የመፈጠሩን ዓላማ ያውቃል

ምድር ላይ የመገኘቱ ሚስጥር ለርሱ አንድ ቁም ነገር ብቻ ነው፡፡ “ዒባዳ” አላህን ማምለክ፡፡ለሌሎች ጣዖታት አያጎነብስም፡፡ምድራዊ ነፀብራቆች ወደ አምላኩ ከመቅረብ የሚያግዱት ግርዶሾች አይደሉም፡፡ሁሉን ዓይነት አምልኮ ለአላህ እንጂ ለማንም ጥቂትን አይቀርስም ፡፡የሚከተለው ቁርአናዊ አንቀጽ መልዕክት ሰርፆታል፡፡

قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ

***«ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል፡፡ » አንዓም 162***

እዚህ ዓለም ውስጥ የተገኘው ለዋዛ አይደለም፡፡ ሙሉ በሙሉ ፊቱን ወደ አላህ ያዞረ ነው፡፡ሶላትን ጠብቆ ይሰግዳል፡፡ለበታቾቹ ለድሆች እና ሚስኪኖች ያስባል፡፡በእዝነት ዓይኑም ያያቸዋል፡፡ ሁሉም መልካም ነገሮች በሙሉ አምልኮ ስለሆኑ ከመስራት አይቦዝንም፡፡ እርቆ ሳይሄድ አብሰልሳይ አዕምሮው የአምላኩን መኖርና ሁሉነ ቻይነት በዙሪያው ያሉ ፍጡራን ይነግሩታል፡፡

## 2) ነፍሱን እና ማንነቱን ለመገንባት ጥረት ያደርጋል

ይህን ንዑስ ርዕስ በሁለት ከፍለን እንየው፡፡ ሙስሊም ስብዕና ውስጣዊውም ይሁን ውጫዊው ገፅታ ለተምሳሌትነት ብቁ ነው፡፡ ነፍሱን እና ማንቱን በመገንባቱ ሂደት ላይ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፡፡

### ሀ. ከስነ-ምባራት ግድፈት ራሱን ያቅባል

ውሸት አይናገርም፡፡ ፍፁም አያጭበረብርም፡፡ ንፁህነን አይዘልፍም፤ አያምታታም፡፡ ለሰዎች የሚጎረብጥ እና የማይመች አይሆንም|፡፡ለሁሉም ቀለል ያለ እና ተግባቢ ነው፡፡ታማኝ ነው፤አይከዳም፤ስሜቱን አይከተልም፡፡ስሜት እና የነፍሱን ፍላጎት ከራዕያዊ መልዕክቶች በተፃራሪ መንገድ መከተል መንፈሳዊ ገደል ውስጥ መግባት እንደሆነ ይገነዘባል፡፡አላህን በግልፅም ይሁን በድብቅ ከመወንጀል ይታቀባል፡፡ አላህ በሰዎች ላይ የወከላቸው ተቆጣጣሪ መላዕክት እንዳሉ ያምናል፡፡

وَإِنَّ عَلَيْكُمْ لَحَافِظِينَ*كِرَامًا كَاتِبِينَ*عْلَمُونَ مَا تَفْعَلُونَ

***‹‹በእናንተ ላይ ተጠባባቂዎች ያሉባችሁ፤ ስትኾኑ፤የተከበሩ ጸሐፊዎች የኾኑ፤ (ተጠባባቂዎች)፡፡ የምትሠሩትን ሁሉ የሚያውቁ፡፡››*** **አል-ኢንፊጧር 10-11**

ጌትዬው ፊት መቆምን እጅግ ይሰጋል፡፡ለዚያ አስፈሪ ዕለትም ራሱን ያዘጋጃል፡፡

وَأَمَّا مَنْ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِ وَنَهَى النَّفْسَ عَنِ الْهَوَى

***‹‹በጌታው ፊት መቆምን የፈራ ሰውማ ነፍሱንም ከዝንባሌዋ የከለከለ .....>> አን-ናዚዓት 40***

ፍትሀዊ ነው፡፡አምባገነኖች እና ጥጋበኞች ከሚሰሩት ግፍ ራሱን ያርቃል፡፡ የሰዎች ስህተት ላይ መውደቅ አያስደስተውም፡፡ለራሱ ከመኖር ይልቅ ለሌሎች ይኖራል፡፡

## ለ. አካላዊ ደህንነቱን ይጠብቃል፡፡

የውጫዊ ገፅታ ማማር እና መስህብነት መኖር እንደ አጉል ባህል በማየት ወደ ኋላ አያፈገፍግም ፡፡አማኝ ሰው ንቁ ነው የሚለውን ነብያዊ ንግግር መሰረት በማድረግ፤የአካል ብቃት ጥንካሬ ይሰራል፡፡ ጥሩ ይመገባል ፤ጥሩ ይለብሳል፡፡ ይህን በማድረጉ በዒባዳ ላይ ንቁ(active) ይሆናል፡፡ በበሽታ እና ደዌ ተረቶ እንዳይወድቅ ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡ብቁ እና መስህብ (attractive)ተክለ-ቁመና ይኖረዋል፡፡ንፅህናን የኢማን ግማሽ አድርጎ በደንብ ስለሚያምንበት ልብሱና ሰውነቱ ንጹህ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ የሰውነቱና ጤናውን ምሉዕነት ይፈልገዋል፡፡ ምክንያቱም ህሊና ሰላም የሚሆነው አካል ደህንነቱ ሲጠበቅ ብቻ ነው፡፡ሁለተኛ ነብዩ (ሰዐወ) ***«ልጆቻችሁን ውሀ ዋና፤ቀስት ውርወራና ፈረስ ግልቢያ አስተምሯቸው» ብለዋል፡፡*** በዚህ ሀዲስ መሰረት ወጣት በአፍላነቱ በስፖርት የዳበረ ተክለ-ቁመና መያዙ ፋይዳ እንዳለው ይረዳል፡፡ ምክንያቱም መደብደብ፤መታሰር፤መቁሰል፤በዳዕዋው መስመር ላይ ያሉ የተለመዱ ነገሮች ናቸው፡፡ ስቃይ ረሀብና እንቅልፍ እጦትን ወይም መሰል ነገሮችን ያቃልላል፡፡

## *3) አርቆ ያስባል፤በሳል መፍትሄዎችን ይፈጥራል*

ኃላፊነት ይሰማዋል፡፡ በተጨባጭ የሚያያቸው የኡማው ዘርፈ-ብዙ ችግሮች መፍትሄ እንደሚያሻቸው ይረዳል፡፡አርቆ ያስባል፡፡አሁን በተጨባጭ ያለበትን ሁኔታ በማጤን መጪ ችግሮች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ በመገመት በቂ ዝግጅት ያደርጋል፡፡

ትከሻውን ርካሽ ስራዎች ለርሱ አርቆ አሳቢነት እንቅፋት እንዳይሆኑ የራሱ የሆነን እርምጃ ይወስዳል፡፡ራሱን በሱስ ጠምዶ፣ከቆነጃጅት ጋር ተቃብጦ ጊዜውን አያባክንም፡፡ ዓላማው ኢስላም ነው፡፡ ግቡ የአላህ ህግ ነው፡፡ውጤቱ ደግሞ የሁለት ዓለም ትርፈኝነት ነው፡፡

## 4) ጊዜውን በአግባቡ ይጠቀማል ውጤታማም ይሆናል

ጊዜ ሰይፍ ነው፤አንተን ሳይቆርጥህ በፊት ቁረጠው፡፡ ወይም በፍጥነት እንደሚጋልብ ፈረስ ነው፡፡ ይህ ወጣት ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም ከቻለ ያለበትን ውጥረት መቀነስ፣ በሕይወት ሩጫ ውስጥ ውጤት ማምጣት እንዲሁም ያለበት ማህበረሰብ ይበልጥ እምነት እንዲጥልበት ደርጋል፡፡ በፕሮግራም መመራት፣ ፕሮግራምን መተግበርና የተደራጀ መሆን ጊዜን ፍሬያማ ያደርጋልሀሰነል-በስሪ እንዳሉት የሰው ልጅ የጊዜ ጥርቅም ነው፡፡ ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም ከባድ ኪሳራ ነው፡፡ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በሀዲሳቸው ላይ አብዛኛው ሰው ብዙ ግምት ያልሰጣቸው ነገሮች ግን ትላልቅ ፀጋዎች ብለው ትርፍ ጊዜን እና ጤንነትን ጠቅሰዋል፡፡ ጊዜ በምንም ሊገመት የማይችል ትልቅ የአላህ ፀጋ ነው፡፡ለሁሉም ሰው በእኩልነት የተሰጠ ስጦታ ነው፡፡ውጤታማ የመሆን ያለመሆን ግን በሰውየው ይወሰናል፡፡ጥቅም አልባ ቦታ ያሳለፈው ለመጥቀም ፋይዳ ላይ ያዋለው ደግሞ አትራፊ ይሆናል፡፡ታዲያ ንቁ ወጣት ጊዜውን አድኖ ይጠቀማል፡፡ጉዳዮቹን በሙሉ በጊዜ የተወሰነ እና የተገደበ (limited) ያደርጋል፡፡

## 5) ለሌሎች ጠቃሚ ነው

ከሰዎች ሁሉ በላጩ ሌሎችን የጠቀመ ነው፡፡ሙስሊም ስብዕና ለሌሎች ብዙ አገልግሎትን (service) ይሰጣል፡፡ይህ ሃይማኖታዊ ግዴታው ነው፡፡ልቦናቸው ደርቆ የታመሙ ሰዎችን በኢስላማዊው ዳዕዋ የህክምና አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ዕውቀትን በማንበብ፣በመማር እና በመስማት ይቀስማል ብለውም አቅመ ደካሞችን እና ወላጅ አልባዎች እንዲሁም አረጋውያንን ይንከባከባል፡፡የወደፊቱን ጊዜ ተረካቢ ታዳጊዎችን ተርቢያ ያደርጋል፡፡ ሙስሊም ሁኔታው እንደ ዝናብ ነው፣ የትም ይዝነብ ይጠቅማል፡፡

## 6) ቤቱን ይገነባል

ከስኬታማ እና ትላልቅ የተፅእኖ አሻራ ካላቸው ሰዎች ጀርባ ሴት አለች፡ ፡ ከሁለቱ መሀል የሚበቅሉ ፍሬዎች ደግሞ ይበልጥ ሀገር ያሳድጋሉ፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) «እናንተ ወጣቶች ሆይ! ከናንተ ውስጥ የትዳርን ጣጣ የሚችል ካለ ያግባ........ ብለዋል፡፡

አርቆ የሚያስብ እና የኡማውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የምታግዘውን እንስት ይፈልጋል፡፡ እርሷም ቤቱን ትጠብቅለታለች፡፡ ልጆቹን በኢስላማዊ አደብ ታሳድግለታለች፡፡ የርሱን ኃላፊነቶች ታግዘዋለች፡፡

## 7) ኡማውን ወደ ተሻለ አቅጣጫ ያመላክታል፡፡

የኢስላማዊው ስልጣኔና ዕድገት በምን መልኩ ዳግም ተመልሶ ሊመጣ እንደሚችል ከብዙ ጥናቶች (researches) በኋላ ለኡማው ይፋ ያደርጋል፡፡ ሁሉም መማር እንዳለበትና የተለያዩ ዘርፎች የኢስላም ፍሬዎች እንደሚያስፈልጓቸው አበክሮ ያስተምራል፡፡ወጣቱ ላይ ይህን አስተሳሰብ ይተክላል፡፡ የስልጣኔን ዘውድ ለንጉሱ ኢስላም ለመድፋት፤ የዕድገትን ጎዳና በኢስላም ምንጣፍ ላይ ለማድረግ የሚታትር፡፡ ድንቅ ወጣት፤ደግ አሳቢ ይህ ነው፡፡

*ዋቢ መጽሐፍት*


1. ቅዱስ ቁርአን
2. ሀዲሰ-ነበዊ
3. ደውሩ ሸባብ ፊ ሃምሊ ሪሳለቲል ኢስላም
4. ሚን ረዋኢዒ ሐዻረቲና- ዶ/ር ሙስጠፋ ሲባዒ
5. ሐታ ያዕለመ-ሸባብ  ዶ/ር ጣሃ ናስር ዑልዋን
6. አስ-ሰህወቱል ኢስላሚያ ሚነል ሙራሀቀቲ ኢለ ሩሽድ-ዶ/ር ዩሱፍ አል ቀርዷዊ
7. ተርቢየቱል ኢስላም ወመድረሰተል-ሐሰነል በና-ዶ/ር ዩሱፍ አል ቀርዷዊ
8. ኢለ ሸባብ ኢማም ሐሰን አል-በና
9. ሰው፣ ግብረገብና ሥነ-ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች- ጠና ደዎ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ